# የእስልምና ሃይማኖት

ቁርኣን እና ከሰዎች ሁሉ ምርጥ የሆኑት ነብይ ሓዲሦች እንደገለፁት

አዘጋጅ፦
ፈሀድ ቢን ሐመድ ኣል ሙባረክ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው።

# መቅድም

ምስጋና ለአላህ የተገባ ነው፤ እናመስግነዋለን፤ በእርሱም እንታገዛለን፤ ምህረትንም እንጠይቀዋለን፤ ከንፍሳችን ተንኮሎች እና ከስራችን ክፋት በአላህ እንጠበቃለን፤ አላህ የመራው እርሱ የተማራ ነው፤ ያጠመመውን የሚያቀናው መሪ አታገኝለትም፤ ከአላህ በስተቀር በእውነት አምልኮት የሚገባው እንደሌለ እመሰክራለሁ፤ ሙሐመድም የአላህ ባሪያ እና መልእክተኛው መሆናቸውንም እመስክራለሁ፣ አላህ በእርሳቸው ላይ የላቀ ውዳሴ እና ሠላም ያውርድባቸው።

በመቀጠልም፦

አሁን ባለንበት ወቅት ስለ እስልምና ሃይማኖት፥ በእምነቱ ወይም በአምልኮቱ ወይም በማህበራዊ ግንኙነትም ይሁን በስርዓቱ ሆነ በሌሎቹ ዘርፍ ያለውን (ሁለንተናዊነት) አቃፊነትን እና አካታችነትን የሚዳስስ ቀላል እና አጭር ጥንቅር አስፈላጊነቱ የጎላ ነው። ጥንቅሩን፥ አንባቢው ስለ እስልምና ሃይማኖት የተሟላ፣ አጠቃላይ እና ግልጽ ግንዛቤ እንዲኖረው፤ ወደ ኢስላም የገባ ሰውም ስለ እስልምና ሃይማኖት፣ ስለ ሕግጋቶቹ፣ ስለ ስርዓቶቹ፣ ስለ ትእዛዛቶቹ እና ክልከላዎቹ ለመረዳት የመጀመሪያ ዋቢ የሚሆነውን የሚያገኝበት እንዲሆን ነው። በመሆኑም ይህ መጽሃፍ ወደ አላህ የሚጣሩ ዱዓቶች እጃቸው ላይ ይሆን እና ወደ ሁሉም ቋንቋዎች ይተረጎምና ስለ ኢስላም ለሚጠይቁ ብሎም ወደ ኢስላም ለሚገቡ ሰዎች በቀላሉ በማበርከት አላህ ለቅኑ የስኬት መንገድ ያበቃው ለስኬቱ ይበቃ ዘንድ፤ ለጠመሙት እና ለሳቱት ደግሞ ማስረጃው ይደርሳቸው ዘንድ በማሰብ ነው።

ይህንን ጥንቅር መጻፍ ከመጀመሬ አስቀድሜ፥ የዚህ መጽሃፍ ዋና ዓላማ እና ግብ ይሳካ ዘንድ፥ ጸሃፊው የሚጓዝበትን መስመር እና ደንቦች ማስቀመጥ የግድ ይላል። ከእነዚህም ደንቦች የሚከተሉትን እንጠቅሳለን፦

ይህ ሃይማኖት መቅረብ ያለበት፥ ከተከበረው ቁርኣን እና ከጠራው ነብያዊ ሐዲስ ማስረጃዎች እና ጥቅሶች ነው እንጅ፥ ከሰው የአገላለጽ ስልት አልያም በውይይት እና በማሳመን መስክ ላይ የፈላስፋዎችን ስልት በመጠቀም አይደለም፤ ይህም በተለያየ ምክንያት ነው፦

ሀ- ከፍ ያለውን የአላህን ቃል በመስማት እና መልእክቱን በሚገባ በመረዳት፥ አላህ ለስኬት ሊያበቃው የሻውን ለስኬት እንዲያበቃው እና እንዲመራው። አልያም አመጸኛ ለሆነ ጠማማ ደግሞ ማስረጃው ይደርሳቸው ዘንድ ነው፥ ከፍ ያለው ጌታ አላህ እንዲህ ብሏል፦ "ከአጋሪዎችም አንዱ ጥገኝነትን ቢጠይቅ፥ የአላህን ቃል ይሰማ ዘንድ አስጠጋው፤ ከዚያም ወደ መጠበቂያው ስፍራ አድርሰው፤ ይህ እነሱ የማያውቁ ሕዝቦች በመሆናቸው ነው።" {አተውባ፥6} ምናልባትም በአብዛኛው ለጉድለት እና ለክፍትት በተጋለጠው በሰው የአገላለጽ ስልት አልያም የፈላስፋዎች ፍልስፍና ማስረጃ ላይረጋገጥ እና መልእክት ላይደርስ ይችላል።

ለ- አላህ ሃይማኖቱን እና ራእዩን እንደወረደ እንድናስተላልፍ ነው ያዘዘን እንጅ፥ የሰዎችን ልብ የምንማርክ መስሎን፥ የፍልስፍና አካሄድን ቀምረን እነሱን ለመምራት እንድንጓዝ አላዘዘንም፤ በመሆኑም የታዘዝንበትን ትተን ባልታዘዝነው ነገር ራሳችን ለምን ይሆን የምንወጥረው?

ሐ- ሌሎች የዳዕዋ ዘዴዎች ለምሳሌ ስለ ተቃዋሚዎች በእምነት፣ በአምልኮ፣ በስነምግባር፣ በሥነ ስርአት፣ በኢኮኖሚክስ ረገድ ያለባቸውን ስህተት በስፋት መናገር እና ለእነሱ ምላሽ መስጠት፤ ወይም የአላህን ህልውና -ግፈኞች ከሚሉት እጅጉን የላቀው- ጌታችን አላህ ህልውና ዙርያ፣ በኦሪትና በወንጌል ውስጥ ወይም በሌሎች እምነቶች ሃይማኖታዊ መፅሀፎች ላይ ስላሉ ግጭቶችና ተቃርኖዎች እንዲሁም ውድቅነት በመሳሰሉት ጉዳዮች አእምሯዊና ምልከታዊ አመክንዮዎችን በመጠቀም ማውራት እና መሰል ዘዴዎች፤ ተቃዋሚዎች ያሉበትን የተሳሳተ አቋምና የተሳሳተ እምነት ብልሹ መሆኑን ለማጋለጥ እንዲሁም -ባለማወቁ የማይጎዳበት ከመሆኑም ጋ- ለሙስሊሙም የብስለት ስንቅ ሊሆኑት ይችላሉ። ይሁን እንጅ ወደ አላህ ለሚደረግ ጥሪ የሚቆምበት መሰረታዊ ዋልታ እና መነሻ (መንደርደሪያ) ተደርጎ ሊያዝ ግን አይችልም።

መ- በእነዚህ ከላይ በተገለጹት ዘዴዎች ዳዕዋ ተደርጎላቸው ወደ እስልምና የገቡ ሰዎችም ያለ ጥርጥር እውነተኛ ሙስሊም ይሆናሉ ማለትም አይደለም። ምክንያቱም ምናልባት አንዳንዱ በተነገረው ውስን ጉዳይ ተመስጦ ወደ እስልምና ገብቶ ነገር ግን ከሃይማኖቱ መሰረቶች ምናልባትም በአንዱ የማያምን ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ በኢስላማዊ የኢኮኖሚ ሲስተም ተመስጦ በመጨረሻው ዓለም ላያምን፤ ወይንም በጂኖችና ሸይጧኖች ህልውና የማያምን ሊሆን እንደሚችለው ማለት ነው።

የዚህ ዓይነት ሰዎች ለእስልምና ከሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ይልቅ የሚያስከትሉት ጉዳት የበዛ ነው።

ረ- ቁርኣን ነፍሶችንና ልቦችን የመቆጣጠር ስልጣን አለው። የትኛዋም ንፁህ ህሊና ለቁርኣን ብቻ ነጻ ከሆነች፥ ጥሪውንም ትቀበለዋለች፤ በኢማንና በተቅዋም ትፋፋለች። ታዲያ በቁርኣንና በሷ መካከል ጋሬጣ መሆኑ ለምን አስፈለገ?!

ይህ ዲን ሲቀርብ አፀፋዊ ምላሾች፣ የተጨባጩ ጫናዎች እና የቀድሞ ዳራዎች መሰል ስሜቶች ጣልቃ መግባት የለባቸውም። ይልቁንም ይህ ሀይማኖት መገለፅ ያለበት ልክ በወረደበት መልኩ ሰዎችን የሚያነጋግርበትን ስልት በመከተል በፅናት ጎዳና ነው መቅረብ ያለበት።

መጽሐፉን ለመያዝም ይሁን በሰዎች መካከል ለመቀባበል ቀላል እንዲሆን የአጻጻፍ ዘይቤን ከማስፋት ይልቅ አጠር ማለቱ በተቻለ መጠን በጽሑፉ ትኩረት ተሰጥቶታል።

እንበልና ይህንን ሥራ አጠናቀን፤ መጽሐፉንም ተርጉመን፤ አሥር ሚሊዮን ቅጂዎችን አሳትመን አሥር ሚሊዮን ሰዎች እጅ ላይ ብንደርስና በዚህ መልኩም በውስጡ ባሉት የቁርኣን አንቀጾችና ሐዲሶች አንድ በመቶው ብቻ ቢያምን ከመቶ ዘጠና ዘጠኙ ደግሞ ክዶ ጀርባውን ቢሰጥ፤ አንዱ በመቶ ብቻውን አላህን ፈርቶ ኢማንና ተቅዋን ፈልጎ ወደ እኛ ቢመጣ፥ ራሱ አስበህዋል የተከበርክ ወንድሜ! ይህ አንዱ ፐርሰንት ማለት እኮ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የእስልምናን ሃይማኖት ተቀላቀሉ ማለት እኮ ነው?! ይህ

ደግሞ ታላቅ ስኬት መሆኑ የማያጠራጥር ነው። አላህም አንተን ሰበብ አድርጎህ አንድን ሰው ቢመራልህ ላንተ ከቀያይ ግመሎች የተሻለ ነው።
ኸረ እንደውም ከእነዚህ ዳዕዋ ከተደረገላቸው ሰዎች አንዳቸውም ባያምኑና ሁሉም ለዚህ ሃይማኖት ጀርባቸውን ቢሰጡ ራሱ እኛ አደራችንን ተወጥተን አላህ የሰጠንንም ኃላፊነትም አድርሰናል።
ወደ አላህ ጥሪ የሚያደርጉ ሰዎች ይበልጥ የሚያሳስባቸው ሰዎችን በዚህ ሃይማኖት ማሳመን ወይም - እንደ ቁርኣን አገላለፅ - ለመመራታቸው መጓጓት አይደለም። {በመመራታቸው ላይ ብትጓጓ (ምንም ልታደርግ አትችልም)። አላህ የሚጠመውን ሰው አያቀናውምና።} [አን_ነሕል፡ 37] ይልቁን የእነሱ ዋነኛ ተልእኳቸው ልክ በልዑልና ኃያል ጌታቸው እንዲህ እንደተባሉት ነብያቸው ﷺ በተከታዩ አንቀፅ የተገለፀው ነው፦ {አንተ መልእክተኛ ሆይ! ከጌታህ ወዳንተ የተወረደውን አድርስ። ባትሠራም መልክቱን አላደረስክም። አላህም ከሰዎች ይጠብቅሃል።} [አል-ማኢዳህ: 67]
ሁላችንም የአላህን ዲን ለመላው ሰው በማድረስ የምንተባበር፤ እንዲሁም የመልካም ነገር ቁልፎችና ወደዛም ተጣሪዎች፣ የክፋትንም በር በፊት ለፊቱ የሚዘጉ መዝጊያዎች እንዲያደርገን፥ ከፍ ያለውን እና የላቀውን አላህን እንማፀነዋለን። አላህ ይበልጡን ያውቃል፤ የአላህ ሰላትና ሰላም በነብዩ ሙሐመድ ላይ ይስፈን።

## ውድ አንባቢ ሆይ፡-

ይህ እጅ ላይ የሚገኘው መጽሐፍ ቀለል ባለና ሁሉንም ገፅታዎች (እምነቱን - አዳቦቹን - ህግጋትን - ሁሉንም ትምህርቶቹን) ባካተተ መልኩ ከእስልምና ሀይማኖት ጋር ያስተዋውቆታል።
በርካታ ዋና ዋና ነገሮች ግምት ውስጥ ለማስገባት ሞክሬያለሁ፦
አንደኛ: ሃይማኖቱ የተመሰረተበትን መሰረተ-ሃይማኖቱ ላይ ማተኮር።
ሁለተኛ፡- በተቻለ መጠን አጠር ማድረግ።
ሶስተኛ፦ አንባቢው በቀጥታ የእስልምና ዋና ምንጮች ፊት ለፊት ሆኖ መመሪያውንና አስተምህሮቱን ይጎነጭ ዘንድ፥ እስልምናን ከመነሻ ምንጮቹ (ከተከበረው ቁርኣን እና ከመልእክተኛው የአላህ ሰላት እና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን ሀዲስ) በማቅረብ።
ውድ አንባቢ ልክ መፅሀፉን እንዳጠናቀቅክ ራስህን ስለ እስልምና ሀይማኖት ግልጽ የሆነ ምልከታ ኖሮህ ታገኘዋለህ። ከዚያም በሂደት ስለዚህ ሀይማኖት ያለህን የእውቀት ድልብ ታሳድግበታለህ።
ይህ በእጅዎ የሚገኘው መጽሐፍ በዋነኛነት የእስልምናን ሀይማኖት ለመቀበል እና እምነቱን፣ ሥርዓቱን እና ፍርዱን መማር ለሚፈልጉ ሰዎች በግምባር ቀደምነት ብሎም ከዛም በላይ ላሉ በረካታ ማህበረሰብ አንገብጋቢ ነው።
በተጨማሪም ስለ ሀይማኖቶች ለማወቅ ፍላጎት ላላቸው በተለይም በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች ስለተቀበሏቸው ሀይማኖቶች ማወቅ ለሚፈልጉ እንዲሁም ለእስልምና ጥሩ ቀረቤታ ላላቸውና በእስልምና አንዳንድ ነገሮች አድናቂዎች እና ምናልባትም ባለማወቃቸው የእስልምና ጠላቶችና ኢስላም ጠል ለሆኑ ለእስልምና ጠላቶች እና ተቃዋሚዎቹ ታሳቢ አድርጎ የተዘጋጀ ነው።
በዚህ መጽሐፍ ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ታሳቢ ከተደረጉ መካከል የእስልምናን ሀይማኖት ለሰዎች ለማስረዳት የሚፈልጉ ሙስሊሞችም ተጠቃሽ ናቸው። ይህ መጽሐፍ ጥረታቸውን የሚያሳጥርላቸው እና ስራቸውንም የሚያቀልላቸው ይሆናል።
እናም ውድ አንባቢ ሆይ! ስለ እስልምና ሀይማኖት መነሻ የሚሆን ጠቅላላ እውቀት ከሌለህ በዚህ መፅሃፍ ውስጥ የተካተቱትን ትርጉሞች ለማወቅ ከፍተኛ ትኩረት እና ጥንቃቄ የተሞላበት ንባብ እንደሚያስፈልግህ ተረዳ። እንዲህ ስለተባልክ ደሞ አትሰላች። ለጥያቄዎችህ መልስ የሚሰጡ ብዙ ኢስላማዊ ድረ-ገጾች ስላሉልህ ማለት ነው።

# 1- የተውሒድ ቃል (ላ ኢላሃ ኢለላህ)

የእስልምና ሀይማኖት መሰረታዊው ህገ መርህ ቃለ-ተውሒድ (ላ ኢላሃ ኢለላህ) ነው። ይህ ጠንካራ መሰረት ከሌለ ከፍ ያለው የእስልምና ህንፃ ሊገነባ አይችልም። ወደ እስልምና ሀይማኖት የሚገባ ሰው በእርሱ አምኖበት በሁሉም ትርጉሞቹ እና ፍቺው አምኖበት ሊናገረው የሚገባ የመጀመሪያው ቃል ነው። ታዲያ "ላ ኢላሃ ኢለላህ" ማለት ምን ማለት ነው?
"ላኢላሃ ኢለሏህ" ማለት፦
ከአላህ በቀር ምንም ፈጣሪ የለም።
በዚህ ዓለም ውስጥ ከአላህ በቀር ባለቤትም ሆነ አስተናባሪ ምንም የለም።
ከአላህ በቀር አምልኮ የሚገባው አምላክ የለም።
ይህንን ሰፊ፣ ውብ፣ አምሳያ የለሽ የሆነውን ዩኒቨርስ የፈጠረው አላህ ነው። ይህች ሰማይ ካላት ድንቅ ከዋክብት እና በየምህዋራቸው በተራቀቀ ስርአት እና አስደናቂ እንቅስቃሴ የሚዞሩ ፕላኔቶች ጋ አላህ ብቻ ነው የሚይዛቸው። ይህች ምድር ተራሮችዋና ሸለቆዎችዋ፣ ኮረብቶችና ወንዞቿ፣ ዛፎቿና እርሻዎቿ፣ አየሯና ውኃዋ፣ የብሷና ባሕሯ፣ ሌሊትና ቀኗ፣ በውስጧ ከያዘቻቸው ነዋሪዎቿና የሚመላለስባትም ሁሉ አላህ ያላንዳች የፈጠራቸውና ያስገኛቸው የአላህ ፍጡራን ናቸው።
የላቀው አላህ በተከበረው ቁርኣን እንዲህ ብሏል፦ {ፀሐይም ለእርሷ ወደ ሆነው መርጊያ ትሮጣለች። ይህ የአሸናፊው የዐዋቂው አምላክ ውሳኔ ነው።} {ጨረቃንም የመስፈሪያዎች ባለቤት ሲኾን እንደ ዘንባባ አሮጌ ቀንዘል እስኪኾን ድረስ (መኼዱን) ለካነው።} {ፀሐይ ጨረቃን ልትደርስበት አይገባትም። ሌሊትም ቀንን (ያለ ጊዜው) ቀዳሚ አይኾንም። ሁሉም በመዞሪያቸው ውስጥ ይዋኛሉ።} [ያሲን፡ 38_40] {ምድርንም ዘረጋናት። በእርሷም ውስጥ ጋራዎችን ጣልንባት። በውስጧም ከሚያስደስት ዓይነት ሁሉ አበቀልን።} {(ይህንን ያደረግነው) ተመላሽ ለኾነ ባሪያ ሁሉ ለማሳየትና ለማስገንዘብ ነው።} {ከሰማይም ብሩክን ውሃ አወረድን። በእርሱም አትክልቶችንና የሚታጨድን (አዝመራ) ፍሬ አበቀልን።} {ዘምባባንም ረዣዥም ለእርሷ የተደራረበ እንቡጥ ያላት ስትኾን (አበቀልን).} [ቃፍ፡ 7_10]
ይህ ሁሉ ጥራት ይገባውና የልዑል ኃያሉ አላህ አፈጣጠር ነው። ምድርን መርጊያ አደረጋት፤ የመሬት ስበትንም ለህይወት በሚመጥን መልኩ አደረገላት፤ እላፊ ሄዶ በእርሷ ላይ ለመንቀሳቀስ አስቸጋሪ በሚሆንበት መልኩም ሳይሆን በውስጧ የያዘቻቸው ሕይወት ያላቸው ነገሮች እስኪበሩ ቀንሶም ሳይሆን የተመጠነ የመሬት ስበት አደረገላቸው። ሁሉም ነገር እርሱ ዘንድ በልክ ነው።

ከእርሱ ውጭ ህይወት የማትቆምበት የሆነውን ንጹሕ ውሃን ከሰማይ አወረደ። {ሕያው የሆነንም ነገር ሁሉ ከውሃ ፈጠርን።} [አል-አንቢያእ፡ 30] በውኃውም እፅዋትና ፍራፍሬን አወጣ፤ እንስሳትንና ሰዎችንም አጠጣ፤ ምድሪቱንም ጡብቃ እንድታኖር አድርጎ አመቻቻትና ለምንጭነትና ወንዝነትም ገራት።
በዛውም ማራኪ ውበት ያላቸው ዛፎች፣ አበቦች፣ ጽጌረዳዎችን እና አትክልቶችን አበቀለ። ያ ሁሉንም ፍፁም አድርጎ የፈጠረው አምላክ የሰውን ፍጥረት ከጭቃ ጀመረው።
የመጀመርያው ሰው ሆነው የተፈጠሩት የሰው ልጆች ሁሉ አባት አደም ዓለይሂ ሰላም ሲሆኑ፥ ከጭቃ ነው የተፈጠሩት። ከዚያም አስተካከላቸው፣ ቀረፃቸውና ከነፍስም እስትንፋስን እፍ አለባቸው። ከዛም ጥንዳቸውን ከጎናቸው ፈጠረ። ከዚያም ዘራቸውን ከተንጣለለ ከደከመ ውኃ አደረገ።
የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {በእርግጥም ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው።} {ከዚያም በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ የፍትወት ጠብታ አደረግነው።} {ከዚያም ጠብታዋን (በአርባ ቀን) የረጋ ደም አድርገን ፈጠርን። የረጋውንም ደም ቁራጭ ሥጋ አድርገን ፈጠርን። ቁራጯንም ሥጋ አጥንቶች አድርገን ፈጠርን። አጥንቶቹንም ሥጋን አለበስናቸው። ከዚያም (ነፍስን በመዝራት) ሌላ ፍጥረትን አድርገን አስገኘነው። ከሚቀርጹትም ሁሉ በላጭ የሆነው አላህ ላቀ።} [አል-ሙእሚኑን: 12-14] የላቀው አላህ እንዲህም ይላል፦ {(በማኅፀኖች) የምታፈሱትን አያችሁን?} {እናንተ ትፈጥሩታላችሁን? ወይስ እኛ ፈጣሪዎቹ ነን?} {እኛ ሞትን (ጊዜውን) በመካከላችሁ ወሰንን። እኛም ተሸናፊዎች አይደለንም።} {ብጤዎቻችሁን (መሰላችሁን)በመለወጥና በዚያ በማታውቁትም (ቅርጽ) እናንተን በመፍጠር ላይ (አንሸነፍም)።} [አል_ዋቂዓህ፡ 58_61] እስኪ አላህ አንተን የፈጠረበትን የአፈጣጠር ስርአት አስተውል። አይደለም የመቆጣጠር ችሎታው ሊኖርህ ቀርቶ ስለ አሠራራቸው ራሱ ጥቂቱን እንጅ በማታውቀው መልኩ ባለ ረቂቅ መሳሪያዎች እና የተዋጣለት ስርዓቶችን ያቀፈ ድንቅ ሆኖ ታገኝዋለህ። ይህ የምግብ ውህደት ስርዓትን እስኪ ተመልከተው፥ እጅግ የተሟላ ስርዓት ነው። ምግቡን በቀላሉ ፈጭቶ ለማዋሀድ እንዲመች በትናንሽ ቁርጥራጮች መቆራረጡ ከአፍ ይጀመራል። ከዚያም ጉሮሮ ጉርሻውን ወደ ማንቁርት ይወረውረውና ሀብለ ድምፅ (እንጥል) የምግብ በርን ከፍቶ የመተንፈሻ ቱቦን ከዘጋው በኋላ ጉርሻው በምግብ ቱቦ በኩል ወደ አንጀት ይመዝገዘጋል። በአንጀትም ውስጥ የምግብ ውህደት ሂደቱ ይቀጥላል። ምግቡም ወደ ፈሳሽነት ይለወጣል። ከዚያም በሆድ ውስጥ ያለው መግቢያ ቀዳዳ ይከፈትለትና የምግብ ውህደቱ የምግብ ጥሬ እቃው ለሰውነት የሚበጅ ወደሆነ ንጥረ ነገር ተለውጦ ሌላውን የሰውነት አካል ተስማሚ ይሆን ዘንድ ወደ ሴሎችም ያመራል። ከዚያም የምግብ ውህደቱ ወደሚጠናቀቅበት ወደ ትንሹ አንጀት ያመራል። በዚህም ሁኔታ ምግቡ በአንጀት ውስጥ በሚገኘው ፀምረ አንጀት በመመጠጥ ከደም ዝውውር ጋር አብሮ ሊዘዋወር የሚመች ይሆናል። ይህ በተወሳሰቡ ደም ወሳጅ ቧንቧዎች ውስጥ ለሚዘረጋው የደም ዝውውር የተቀናጀ ስልት ነው። እነሱን ብትለያቸውና ብትነጣጥላቸው ርዝመታቸው ወደ ሺዎች ኪሎ ሜትር የሚደርስ ነው። ልብ ከሚባል ማዕከላዊ የደም ቱቦ ጣቢያ ጋር የተገናኘ ነው። ይህም ጣቢያ ደሙን በደም ወሳጅ ቧንቧዎች በኩል ለማጓጓዝ የማይታክት የማይሰለች ነው።
ሌላ ደሞ የመተንፈሻ ስልት አለ። አራተኛም ነርቭ አለ፤ አምስተኛው ደግሞ የትርፍ ነገር ማውጫ አለ፤ እና ስድስተኛው፤ ሰባተኛው … አስረኛው እና በየእለቱ ይበልጥ እያወቅን የምንሄዳቸው ነገሮች ሁሉ አሉ። ይህም ሆኖ በውስጣችን ከምናውቀው ይልቅ የማናውቀው ይበዛል። ይህንን የሰው ልጅ እንዲህ በተራቀቀ መልኩ ከአላህ በቀር ማን ፈጠረው?!
ስለዚህም ነው ከኃጢአት ሁሉ የከፋው አላህ ፈጥሮህ ሳለ፥ ከአላህ ጋ ተጋሪ ማድረግህ የሆነው።
እስኪ በክፍት ልቦና እና ግልጽ (ቅን) በሆነ መንፈስ ሆነህ ዐይንን የሚያሳውር ቀለም ሳይኖረው ከየቦታው ሁሉ እየሳብክ ስለምትተነፍሰው አየር አስተውል፤ ለጥቂት ደቂቃዎች ቢቋረጥብህ ህይወትህም ቀጥ ብላ ትቆማለች ማለት እኮ ነው። ይህ የምትጠጣው ውሃ፣ ያ የምትበላው ምግብ፣ ይህ የምትወደው ሰው፣ የምትራመድባት ምድር፣ የምትመለከተው ሰማይ፣ ዓይንህ የሚያየውና የማያየው ትልቅም ይሁን ትንሽ ፍጡራን ሁሉ፣ ሁሉም ፈጣሪና አዋቂ ከሆነው አላህ ፍጥረታት ናቸው።
ስለ አላህ ፍጥረታት ማሰላሰል፥ የአላህን ታላቅነትን እና ኃያልነትን ያስገነዝበናል። እጅግ ከሚደንቁ ሞኞች፣ የድንቁርና እና የጥመት ሰዎች መካከል ይህንን እጅግ ልዩ፣ ታላቅ፣ የተቀናጀ እና ፍፁም የሆነ እንዲሁም አስደናቂ ጥበብና የላቀ ችሎታን አስረጅ የሆነ ፍጥረትን እየተመለከተ፥ ያላንዳች (አምሳያና አጋዥ) በፈጠራት ፈጣሪዋ የማያምን ከሃዲ ነው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {ወይስ ያለ አንዳች (ፈጣሪ) ተፈጠሩን? ወይስ እነርሱ ፈጣሪዎች ናቸውን?} {ወይስ ሰማያትንና ምድርን ፈጠሩን? አይደለም አያረጋግጡም።} [አጥ-ጡር 35-36]
የትኛዋም ጤናማ አእምሮ መማር ሳያስፈልጋት የላቀውን ከፍ ያለውን አላህን ታወቀዋለች። ገና ከአፈጣጠሯ ጀምሮ ወደ እርሱ መቅጣጫትን እና መመለስን ፈጠሮላታል። ነገር ግን ከእርሱም የሚያጠማትና የሚያርቃት ነገር ይገጥማታል።
ስለዚህም እኮ ነው ጥፋት፣ ወረርሽኝ ወይም ከባድ ጭንቅና መከራ ሲገጥማት፣ እንዲሁም በምድርም ሆነ በባህር ላይ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ ሲጋረጣባት፣ ካለችበት ጭንቅ ለመገላገል፣ እርዳታን ለማግኘትና ለመትረፍ በቀጥታ መጠጊያዋን ወደ አላህ ነው የምታደርገው። እናም የላቀው አላህም ተጨንቀው ለሚማፀኑት መልስ ይሰጣል፤ ክፉትንም ያስወግዳል።
ይህ ታላቅ ፈጣሪ ከሁሉ የሚበልጥ ታላቅ ነው። እንደውም ፍጡራኑን ከእርሱ ጋ ፈጽሞ ማነፃፀር አይገባም፤ እርሱ ታላቅነቱ ወሰን የሌለውና ማንም በእውቀት ሊያካብበው የማይችል ታላቅ ነው። ከፍጥረታቱም በላይ ከሰማያትም በላይ መሆኑ መገለጫው ነው። {የእርሱ አምሳያ ምንም የለም እርሱ ሰሚ ተመልካች ነው።} [አሽ ሹራ፡ 11] ከፍጥረታቱ ምንም አምሳያ የለውም፤ በአእምሮህ ውል ያለብህ ሁሉ ምንም ይሁን አላህ እንደዚያ አለመሆኑን እወቅ። የላቀው (አላህ) ከሰማያት በላይ ሆኖ ያየናል እኛ ግን አናየውም። {ዓይኖች አያገኙትም፤ (አያዩትም)። እርሱም ዓይኖችን ያያል። እርሱም ርኅራኄው ረቂቁ ውስጠ ዐዋቂው ነው።} [አል_አንዓም፡ 103] ይልቁንም ህዋሶቻችንም ይሁን ችሎታችን በዚህ ዓለም እርሱን ለማየት አቅሙ የላቸውም። ይህንንም ከአላህ መልዕክተኞች መካከል አንዱ የሆኑት ሙሳ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) አላህን በአጥ-ጡር ተራራ ላይ ሆኖ ሲያናግራቸው አላህን ለማየት ጠይቀው ነበር፦ “ጌታዬ ሆይ ወደ አንተ እንድመለከት አሳየኝ” አሉ። ከዚያም የላቀው አላህ እንዲህ አላቸው፦ {(አላህም)፦ «በፍጹም አታየኝም ግን ወደ ተራራው ተመልከት። በስፍራውም ቢረጋ በእርግጥ ታየኛለህ» አለው። ጌታው ለተራራው በተገለጸ ጊዜ እንኩትኩት አደረገው። ሙሳም ራሱን ስቶ ወደቀ። በአንሰራራም ጊዜ «የላቅከው ጌታ። ወዳንተ ተመለስኩ። እኔም (በወቅቱ) የምእምናን መጀመሪያ ነኝ» አለ።} [አል_አዕራፍ፡ 143] አላህ ለተራራው በመገለጡ፥ ታላቁና ከፍ ያለው ግኡዙ ተራራ ተንኮታኩቷል ተሰነጣጥቋል፤ ታዲያ ሰው እንዴት ነው በደካማ አቅሙ ማየት የሚችለው። የላቀው አላህ

ከመገለጫ ባህሪያቱ መካከል አንዱ እርሱ ነገሩን ሁሉ ማድረግ ቻይ መሆኑ ነው። {አላህም በሰማያትም ሆነ በምድር ውስጥ ምንም ነገር የሚያቅተው አይደለም።} [ፋጢር፡ 44] ሕይወትና ሞት በእጁ ነው። ፍጡራን ሁሉ ከርሱ ፈላጊ ናቸው፤ እርሱ ከፍጡራኑ የተብቃቃ ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {እናንተ ሰዎች ሆይ! እናንተ (ሁል ጊዜ) ወደ አላህ ከጃዮች ናችሁ። አላህም እርሱ ተብቃቂው ምስጉኑ ነው።} [ፋጢር፡ 15] የላቀው አላህ ከባህሪያቱም መካከል ሁሉንም ነገር ያካበበ እውቀቱ ይገኝበታል። {የሩቅ ነገርም መክፈቻዎች እርሱ ዘንድ ናቸው። ከእርሱ በቀር ማንም አያውቃቸውም። በየብስና በባሕር ያለውንም ሁሉ ያውቃል። ከቅጠልም አንዲትም አትረግፍም የሚያውቃት ቢኾን እንጅ። ከቅንጣትም በመሬት ጨለማዎች ውስጥ የለም ከእርጥብም ከደረቅም አንድም የለም ግልጽ በኾነው መጽሐፍ ውስጥ (የተመዘገበ) ቢኾን እንጅ።} [አል-አንዓም: 59] እንደበታችን የሚናገረውንና አካሎቻችን የሚሠሩትን ብሎም ልቦናዎቻችን የሚደብቁትን ሁሉ ያውቃል። {(አላህ) የዓይኖችን ክዳት ልቦችም የሚደብቁትን ሁሉ ያውቃል።} [ጋፊር፡ 19] የላቀው አላህ ስለኛ ሁሉን ነገር ያውቃል። ሁኔታዎቻችንንም ጠንቅቆ የሚያውቅ፤ በምድርም በሰማይም ምንም ነገር የማይሰወርበት፤ የማይዘነጋ፣ የማይረሳና የማይተኛ ነው። {አላህ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም። ሕያው ራሱን ቻይ ነው። ማንገላጀትም እንቅልፍም አይዘውም። በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው። ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢኾን እንጅ የሚያማልድ ማነው? (ስለ ፍጡሮች) ከፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል። በሻውም ነገር እንጂ ከዕውቀቱ በምንም ነገር አያካብቡም (አያውቁም)። መንበሩ ሰማያትንና ምድርን ሰፋ። ጥበቃቸውም አያቅተውም። እርሱም የሁሉ በላይ ታላቅ ነው።} [አል-በቀራህ: 255]

እንከን ወይም ነውር የሌለበት የተሟላ ፍጹምነት ባህሪ ባለቤት ነው።

እጅግ የተዋቡ ስሞች እና ምሉዕ ባህሪያት አሉት። የበላይ የሆነው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {ለአላህም መልካም ስሞች አሉት። (ስትጸልዩ) በእርሷም ጥሩት። እነዚያንም ስሞቹን የሚያጣምሙትን ተውዋቸው። ይሠሩት የነበሩትን ነገር በእርግጥ ይምመነዳሉ።} [አል_አዕራፍ፡ 180]

የላቀው አላህ በግዛቱ (በንግስናው) ምንም ተጋሪ፣ አቻ ረዳት የለውም።

የላቀው (አላህ) ባለቤትና ልጅ ከመያዝም የላቀ ነው። ይልቁንም እርሱ ከዚህ ሁሉ የተብቃቃ ነው። የበላይ የሆነው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {«እርሱ አላህ አንድ ነው።በል} {«አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው።} {«አልወለደም፤ አልተወለደምም።} {«ለእርሱም አንድም ብጤ (አቻ እና መሳይ) የለውም።»} [አል-ኢኽላስ 1-4] የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {«አልረሕማንም ልጅን ያዘ (ወለደ)» አሉ።} {ከባድ መጥፎን ነገር በእርግጥ አመጣችሁ።} {ከእርሱ (ከንግግራቸው) ሰማያት ሊቀደዱ፣ ምድርም ልትሰነጠቅ፣ ጋራዎችም ተንደው ሊወድቁ ይቃረባሉ።} {ለአልረሕማን ልጅ አልለው ስለአሉ።} {ለአልረሕማን ልጅን መያዝ አይገባውም።} {በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ (በትንሣኤ ቀን) ለአልራሕማን ባሪያ ኾነው የሚመጡ እንጂ ሌላ አይደሉም።} [መርየም 88-93]

የላቀው (አላህ) በግርማ ሞገስ (ታላቅነት)፣ በውበት፣ በኃያልነት፣ በታላቅነት፣ በኩራት፣ በንግሥናና በመለኮት የሚገለጽ የላቀ ጌታ ነው።

የልግስና፣ የይቅር ባይነት፣ የእዝነት እና የቸርነት ባህሪያትም አሉት፤ እርሱ እዝነቱ ሁሉንም ነገር ያካተተ እጅግ መሐሪ ነው።

(አዛኝ) ርህራሄውም ቁጣውን የሚቀድም ርኅሩኅ ነው።

ልግስናው ገደብ የለሽ የሆነ ለጋስ፤ ካዝናውም ማለቂያ የሌለው ጌታ ነው።

ስሞቹ ሁሉ መልካምና ያማሩ ናቸው፤ ለአላህ ብቻ ካልሆነ በቀር ለሌላ የማይገቡ የሙሉዕነትና የፍፁምነት መገለጫ የሆኑት ባህሪያትንም ያመለክታሉ።

ጥራት የተገባውን አላህ፥ ባህሪያቱን ማወቅ፥ ልቦና ለእርሱ ያላትን ፍቅር፣ ማላቅ፣ ፍርሃትንና አክብሮትን ይጨምራል።

ስለዚህም "ላ ኢላሃ ኢለላህ" የሚለው ቃል ፍቺው ከአምልኮት የቱንም ቢሆን ከአላህ ውጭ ላለ አካል ስለማይሰጥ ከአላህ በቀር በእውነት አምልኮ የሚገባው የለም ነው። የአምላክነት እና የፍፁምነት ባህሪያት ያለው እርሱ ነውና፤ ፈጣሪ፣ሲሳይ ለጋሽ፣ ፀጋ የሚሰጥ፣ ሕይወት ሰጪ፣ ሕይወት የሚነሳው፣ ለፍጡራኖቹ በጎ የሚውል እርሱው በመሆኑ ለአምልኮ የሚገባው ተጋሪ የሌለው ብቸኛ እርሱው ነው።

የአላህን መመለክ ያልፈለገ ወይም ከአላህ ሌላ የሚገዛ ሰው ሽርክንና ክህደትን ፈፅሟል።

ስለዚህም ሱጁድ መውረድ፣ ማጎብደድ፣ መዋረድ እና ሰላት ለአላህ ካልሆነ በቀር ለሌላ አይሆንም።

ወደ አላህ ካልሆነ በቀር የድረሱልኝ ዱዓ አይደረግም፤ ወደ አላህ እንጂ በዱዓእ አይዞርም፤ ከአላህም ካልሆነ በቀር ጉዳዮችን (እንዲፈጽምልን) አይከጀልም፤ መቃረቢያን፣ መታዘዝንና አምልኮንም ወደ አላህም ካልሆነ በቀር ላማንም አይደረግም። «ስግደቴ፣ መገዛቴም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው» በል። «ለእርሱ ተጋሪ የለውም። በዚህም (በማላቅ) ታዘዝኩ። እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ» (በል)። [አል_አንዓም፥162_163]

## ለ- አላህ ለምን ፈጠረን?

የዚህ ትልቅ ጥያቄ መልስ እጅግ በጣም አንገብጋቢ ነው። ይሁን እንጂ መልሱን ከወሕይ (ከመለኮታዊ መገለጥ) ማግኘት ግድ ነው። ምክንያቱም የፈጠረን አላህ ነውና እኛን የፈጠረበትን ዓላማ የሚነግረንም እርሱ ነውና። ልዑሉ አላህ እንዲህ ብሎናል፦ "ጋኔንንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም።" [አዝ-ዛሪያት፥56] ስለዚህም ባሪያነት (አምልኮ) ተቆጥረው የማይዘለቁትን ፍጡራን ሁሉ የሚያካልል መገለጫ ነው። የተከበሩት ፍጥረታትም (መላእክት) ይሁኑ ሌሎቹም እስከ ብርቅዬ ድንቅ ፍጡራኖችም ጭምር ህይወታቸውን ለአምልኮና የዓለማቱ ጌታ አላህን ለማወደስ የተመቻቹ ሆነው ነው የተፈጠሩት። {ሰባቱ ሰማያትና ምድርም በውስጣቸውም ያለው ሁሉ እርሱን ያልቃሉ። ከነገርም ሁሉ ከማመስገን ጋር የሚያልቀው እንጂ አንድም የለም። ግን ማላቃቸውን አታውቁትም። እርሱ ታጋሽ መሓሪ ነው።} [አል_ኢስራእ፥ 44] ልክ የሰው ልጆች ለእስትንፋስ እንደተገሩት ሁሉ መላእክቶችም አላህን ለማወደስ የተገሩ ናቸው። ነገር ግን የሰው ልጅ ለፈጣሪው ያለው ተገዥነት በውዴታ እንጂ በግዴታ ላይ የተመሰረተ አይደለም። (ውዴታ እና ግዴታ) {እርሱ ያ የፈጠራችሁ ነው፤ ከእናንተም ከሓዲ አልለ፤ ከእናንተም አማኝ አልለ፤ አላህም የምትሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነው።} [አተ_ተጋቡን፥ 2] {አላህ በሰማያት ያለው ሁሉ፣ በምድርም ያለው ሁሉ፣ ፀሐይና ጨረቃም፣ ከዋክብትም፣ ተራራዎችም፣ ዛፎችም፣ ተንቀሳቃሾችም ከሰዎች ብዙዎችም፣ ለርሱ የሚሰግዱለት መሆኑን አታውቁምን ብዙውም በርሱ ላይ ቅጣት ተረጋገጠበት። አላህ የሚያዋርደውም ሰው ለእርሱ ምንም አክባሪ የለውም። አላህ የሻውን ይሠራልና።}

[አል_ሓጅ፥18] አላህ የፈጠረን እርሱን እንድናመልከው እና ይህንን አምልኮ በማሳካቱ ረገድ ያለንን ስኬታማነት ሊፈትነንም ነው። በዚህም መሰረት አላህን የሚያመልክ፣ የሚወድ፣ የሚግገዛ፣ ትእዛዙንም የሚፈጽም እና ከተከለከለው የሚርቅ ሰው የአላህን "ሪዷ" (ወዶ መቀበሉን)፣ እዝነቱን እና ውዴታውንም ያገኛል፤ በመልካሙም ይመነዳዋል። የፈጠረውንና ሲሳይ የሚለግሰውን ጌታ ተመላኪነት ያልተቀበለ፤ ከአምልኮም የሚኮራ፤ ለአላህ ትእዛዛትና ክልከላ ማኅበደድን ያልተቀበለ የአላህን ቁጣና በቀል እንዲሁም አሳማሚ ቅጣቱን ነው የሚያተርፈው። ጥራት ይገባውና የላቀው አላህ በከንቱ አልፈጠረንም በከንቱም አልተወንም። እጅግ ድንቁርናቸውና ክፉነታቸው ከበረታባቸው ሰዎች መካከል አንዱ ወደዚህ ዓለም ወጥቶ የመስማት፣ የማየትና የማመዛዘን ችሎታም ተሰጥቶት ከዚያም ጊዜያቶችን ቆይቱ ወደ ዱኒያ የመጣበትን ምክንያትም ይሁን ወደ የትስ እንደሚሄድ ሳያውቅ የሞተ ነው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {«የፈጠርናችሁ ለከንቱ መኾኑን እናንተም ወደኛ የማትመለሱ መኾናችሁን ጠረጠራችሁን» (ለከንቱ የፈጠርናችሁ መሰላችሁን)} [አል-ሙእሚኑን: 115]

አላህ ዘንድ ከኛ መካከል በእርሱ ያመነ፣ መመኪያው አላህን ያደረገ፣ ወደርሱም የተፋረደ፣ የወደደ፣ ጥልቅ ክብርንም የሰጠ፣ በአምልኮ ወደ እርሱ እየተቃረበ በሁሉም ቦታ የአላህን ደስታ የሚፈልግ የሆነ ሰው እና ፈጥሮ የቀረፀውን ጌታውን የሚክድ፣ በአንቀፆቹ እና በሃይማኖቱም የሚያስተባብል ለአላህ ማኅበደድንም የማይቀበል የሆነ ሰው እኩል አይደለም።

የመጀመሪያው መከበርን፣ መልካም ምንዳን፣ መወደድን እና ስራው ተቀባይነትን የሚያገኝ ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ በቀልን፣ ቁጣን እና ቅጣትን ነው የሚያገኘው።

ሰዎች ሞተው ከተቀበሩ በኋላ አላህ ከመቃብራቸው አስነስቶ ከነሱ መካከል በጎ ያደረገውን በጀነት ፀጋው ውስጥ ደስታን እና ክብርን የሚያጎናፅፍበት እና አላህን ያመፀውን ትዕቢተኛ ደግሞ በጀሀነም የቅጣቱ ሀገር የሚቀጣበት ነው።

እስኪ የበጎ አድራጊ ክብር እና መልካም ምንዳ ታላቅነትን አስበው ይህ ሽልማት እና ክብር ከአለም ከተብቃቃውና ቸር ከሆነው አምላክ ሲሆን ያም ልግስና እና እዝነቱ ገደብ የለሽ እንዲሁም ሀብቱም ከማያልቀው ጌታ መሆኑን ደሞ አስበህዋል?! ይህም መልካም ምንዳ የማያልቅ እና የማያቋርጥ የፀጋ ጥግ ይሆናል (ይህን ደግሞ ወደ ኋላ የምናወራበት ይሆናል)።

ልክ እንደዚሁ ካፊር የሚጠብቀውን ብርቱና ከባድ የስቃይ ቅጣትም ማሰብ ይኖርብሀል። ይህም ሁሉን አሸናፊ፣ ታላቅና ኩሩ ከሆነው ኩራትና ኃያልነቱ ገደብ የሌለው ከሆነው አምላክ የመጣ ቅጣት ነው።

# 2- ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ ናቸው።

በመሐመድ ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም መልእክተኝነት ማመን - ከእስልምና መሠረታዊ ምሰሶዎች ሁለተኛው ክፍል እና ዲነል ኢስላምም የተገነባበት ዋነኛው መሠረት ነው።

የትኛውም ግለሰብ ሙስሊም የሚሆነው በሁለቱ የምስክርነት ቃላቶች ሸሃዳ ከሰጠ ነው። ይኸውም ከአላህ በስተቀር ሌላ በእውነት የሚመለክ አምላክ እንደሌለ እና ሙሐመድም የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን በመመስከር ነው።

## ሀ- የመልእክተኛው ትርጉም ምንድን ነው? ሙሐመድስ ማን ናቸው? ከእርሳቸውስ ሌላ መልክተኞች አሉን?

በእነዚህ ገፆች ውስጥ ለመመለስ የምንሞክረውም ይህንኑ ነው።

የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) በንግግራቸው እውነተኝነት እና በመልካም ስነ-ምግባራቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ ሲሆን፤ አላህ ከሰዎች መካከል የመረጣቸው እና ከሃይማኖታዊ ትእዛዛት ወይም ከሩቅ ምስጢር ጉዳዮች የሻውን ገልጦላቸው ለሰዎች ለማድረስ በተልእኮ የሚመርጣቸው ናቸው። በመሆኑም ለሰዎች የተላኩ የአላህ መልእክተኛ ሰው ናቸውና እንደማንኛውም ሰው ናቸው፤ ሰዎች እንደሚበሉት ይበላሉ፣ እንደሚጠጡት ይጠጣሉ፣ የሰው ልጅ የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ያስፈልጋቸዋል። ከእነርሱ የሚለዩት ታዲያ ከአላህ ዘንድ በሚመጣላቸው ወሕይ (የሚገለጥላቸው መለኮታዊ ራእይ) ነው። ይኸውም ስለ ሩቅ ምስጢርም ይሁን ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ያሳውቃቸውን ለሰዎች ያደርሳሉ። በተጨማሪም አላህ ለእርሳቸው በከባድ ኃጢዓት ላይ ከመውደቅ እንዲሁም የአላህን መልእክት ለሰዎች ከማስተላለፍ በሚጥስ ጉዳይ ላይ ከመውደቅ ባለው ጥበቃም ይለያቸዋል።

ከሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) በፊት የነበሩትንና ከቀደሙት መልእክተኞች ታሪኮች መካከል ጥቂቶቹን እናቀርባለን። የመልእክተኞች ተልእኮ አንድ መሆኑንና ይኸውም አላህን በብቸኝነት እንድናመልከው የተደረገ ጥሪ መሆኑ ግልፅ እንዲሆንልን ይረዳናል። ስለ ሰው ልጆች አጀማመር ታሪክ እና ሰይጣን የሰው ልጆች አባት ለሆኑት አደምና ለዝርዮቹ ያለውን ጠላትነት በመቃኘት እንጀምራለን።

## ለ - ከመልክተኞች የመጀመሪያው የሆኑት አባታችን አደም (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)፦

አላህ አባታችንን አደም (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ከሸክላ ፈጥሯቸው ከዚያም ከነፍሱ (አላህ ከፈጠራቸው ነፍሶች መካከል አንዱን) እፍ አለባቸው። ልእለ ኋያሉ አላህ እንዲህ ብሏል፦ {በእርግጥም ፈጠርናችሁ። ከዚያም ቀረጽናችሁ። ከዚያም ለመላእክቶች «ለአዳም ስገዱ» አልን። ወዲያውም ሰገዱ። ኢብሊስ (ዲያብሎስ) ሲቀር ከሰጋጆቹ አልሆነም።} {(አላህ) «ባዘዝኩህ ጊዜ ከመስገድ ምን ከለከለህ» አለው። «እኔ ከርሱ የበለጥኩ ነኝ። ከእሳት ፈጠርከኝ። እርሱን ግን ከጭቃ ፈጠርከው» አለ።} {ከእርሷ ውረድ፤ በእርሷ ውስጥ ልትኮራ አይገባህምና። ውጣም አንተ ከወራዶቹ ነህና አለው።} {«እስከሚቀሰቀሱበት ቀን ድረስ አቆየኝ» አለ።} {አንተ ከሚቆዩት ነህም አለው።} [አል_አዕራፍ፡ 10_15

አላህ ጊዜ እንዲሰጠውና በቅጣትም እንዳያጣድፈው እንዲሁም ከምቀኝነቱና ከጥላቻውም አንፃር አዳምንና ዝርያውንም እንዲፈትናቸው እንዲፈቅድለት አላህን ተማፀነ። ከዚያም አላህ ለፈለገው ጥበብ ሲል ቅን ከሆኑ የአላህ ባርያዎች በስተቀር ሰይጣን በአደምና በዘሮቹ ላይ የማጥመም ሴራውን እንዲያደርግ ፈቀደ። አላህም አደምንና ልጆቹን ሰይጣንን እንዳያመልኩ ለፈተናውም እጅ እንዳይሰጡ ከሴራውም ለመከለል ወደ አላህ እንዲጠጉ አዘዛቸው። ሰይጣንም በአደምና በሚስታቸው ሐዋእ (አላህ ከጎኑ የጎድን አጥንት ከፈጠራት አካሉ) ላይ የመጀመሪያ ፈተናውን ጀመረ። ጥራት ይገባውና የላቀው አላህ በቁርአን እንዳወሳው ማለት ነው።

{«አዳም ሆይ! አንተም ሚስትህም በገነት ተቀመጡ። ከሻችሁትም ስፍራ ብሉ። ግን ይህችን ዛፍ አትቅረቡ። (ራሳቸውን) ከሚበድሉት ትኾናላችሁና» (አላቸው)።} {ሰይጣንም ከነውራቸው የተሸሸገውን ለእነርሱ ሊገልጽባቸው በድብቅ ንግግር ጎተጎታቸው። «ጌታችሁም መልኣኮች እንዳትኾኑ ወይም ከዘላለም ነዋሪዎች እንዳትኾኑ እንጂ ከዚህች ዛፍ አልከለከላችሁም» አላቸው።} {«እኔ ለእናንተ በእርግጥ ከሚመክሩዋችሁ ነኝ» ሲልም አማለላቸው።} {በማታለልም አዋረዳቸው። ከዛፊቱም በቀመሱ ጊዜ ኀፍረተ ገላቸው ለሁለቱም ተገለጠችላቸው። ከገነት ቅጠልም በላያቸው ላይ ይደርቱ ጀመር። ጌታቸውም «ከዚህ ዛፍ አልከለከልኋችሁምን ሰይጣንም ለእናንተ ግልጽ ጠላት ነው አላልኋችሁምን» ሲል ጠራቸው።} {«ጌታችን ሆይ! ነፍሶቻችንን በደልን። ለእኛ ባትምር ባታዝንልንም በእርግጥ ከከሳሪዎቹ እንኾናለን» አሉ።} {(አላህ) « ከፊላችሁ ለከፊሉ ጠላት ሲኾን ውረዱ። ለእናንተም በምድር ላይ እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ መርጊያና መጠቀሚያ አላችሁ» አላቸው።} {«በእርሷ ላይ ትኖራላችሁ። በእርሷም ላይ ትሞታላችሁ። ከእርሷም ውስጥ ትወጣላችሁ» አላቸው።} {የአዳም ልጆች ሆይ! ኀፍረተ ገላችሁን የሚሸሽግን ልብስ ጌጥንም በእርግጥ በናንተ ላይ አወረድን። አላህን የመፍራትም ልብስ ይህ የተሻለ ነው። ይህ ከአላህ ታምራቶች ነው። ይገሠጹ ዘንድ (አወረደላቸው)።} {የአዳም ልጆች ሆይ! ሰይጣን አባትና እናታችሁን ኀፍረተ ገላቸውን ሊያሳያቸው ልብሶቻቸውን ከነሱ የገፈፋቸው ሲኾን ከገነት እንዳወጣቸው ሁሉ እናንተን አይሞክራችሁ። እነሆ እርሱ ከነሰራዊቱ ከማታዩዋቸው ስፍራ ያዩዋችኋልና። እኛ ሰይጣናትን ለእነዚያ ለማያምኑት ወዳጆች አድርገናል።} [አል_አዕራፍ፡ 19_27]

አደም (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ወደ ምድር ወርደው ልጆችንና ዘርን ከተለገሱ በኋላ ሞቱ። ከዚያም ዘራቸው ከትውልድ ትውልድ እየበዙ ሲሄዱ ለሰይጣን ፈተና ተዳረጉና መለያየት፣ የደጋግ አባቶቻቸውን ቀብር አምልኮ በመካከላቸው ተንሰራፋ፤ በአላህ ከማመን በአላህ ወደ ማጋራት ተዘዋወሩ፤ አላህም ነብዩሏህ ኑሕ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) መልዕክተኛ አድርጎ ላከ።

## ሐ- ኑሕ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)፡-

በእርሳቸውና በአደም መካከል አሥር ክፍለ ዘመናት ነበሩ። አላህም ኑሕን ወደ ጠመሙትና ከአላህ ውጭ ጣኦታትን ማምለክ ወደ ጀመሩት ህዝቦቸው ላካቸው። ግኡዝ አካላትን፣ ድንጋይን፣ መቃብሮችንም ያመልኩ ነበር። እጅግ ገናና ከሆኑ ጣኦቶቻቸው መካከል ወድ፣ ሱዋዕ፣ የጉስ፣ የዑቅ እና ነስር የሚባሉ ነበሩ። አላህም ለአላህ ብቻ አምልኮ እንዲያደርጉ ያዟቸው ዘንድ ኑሕ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ላካቸው። ልክ የላቀው አላህ በተከታዩ የቁርአን አናቅፅ እንደነገረን ማለት ነው፦ {ኑሕን ወደ ወገኖቹ በእርግጥ ላክነው። አላቸውም፡- «ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ። ለእናንተ ከርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም። እኔ በእናንተ ላይ የከባድ ቀንን ቅጣት እፈራላችኋለሁ።»} [አልአዕራፍ 59] ህዝባቸውን አላህን ብቻ እንዲያመልኩ ጥሪ በማድረጉ ላይ ለረጅም ጊዜ ቀጠሉ። ይሁን እንጅ ከእርሳቸው ጋር ጥቂት ብቻ ነበሩ ያመኑት። ስለዚህም ኑሕ ጌታቸውን እንዲህ ሲሉ ተጣሩ፦ {(ስለ ተቃወሙትም) «አለ ጌታዬ ሆይ! እኔ ሌሊትም ቀንም ሕዝቦቼን ጠራሁ።} {«ጥሪየም መሸሽን እንጅ ሌላ አልጨመረላቸውም።} {«እኔም ለእነርሱ ትምር ዘንድ (ወደ እምነት) በጠራኋቸው ቁጥር ጣቶቻቸውን በጆሮዎቻቸው ውስጥ አደረጉ። ልብሶቻቸውንም ተከናነቡ። (በመጥፎ ሥራቸው ላይ) ዘወተሩም። (ያለ ልክ) መኩራትንም ኮሩ።} {«ከዚያም እኔ በጩኸት ጠራኋቸው።} {«ከዚያም እኔ ለእነርሱ ገለጽኩ። ለእነርሱም መመስጠርን መሰጠርኩ} {«አልኳቸውም፡- ጌታችሁን ምሕረትን ለምኑት። እርሱ በጣም መሐሪ ነውና።} {«በእናንተ ላይ ዝናምን ተከታታይ አድርጎ ይልካል።} {«በገንዘቦችና በልጆችም ይለግሳላችኋል። ለእናንተም አትክልቶችን ያደርግላችኋል። ለእናንተም ወንዞችን ያደርግላችኋል።»} {ለአላህ ልቅናን የማትሹት ለእናንተ ምን አላችሁ?} {በልዩ ልዩ ኹኔታዎች በእርግጥ የፈጠራችሁ ሲኾን።} [ኑሕ፡ 5_14] ከዚህ ሁሉ ያልተቋረጠ እና አስደናቂ ጥሪ፤ ህዝባቸውንም ለመምራት ካላቸው ከፍተኛ ጉጉት ጋር ለጥሪያቸው ምላሽ የሰጡት ግን በክህደት፣ በመሳለቅ እና በእብደት በመወረፍ ብቻ ነበር። የዛኔ እንዲህ በማለት አላህ ዋሕዩን አወረደለት፦ {ወደ ኑሕም እነሆ «ከሕዝቦችህ በእርግጥ ካመኑት በስተቀር (ወደፊት) አያምኑም። ይሠሩትም በነበሩት (ክህደት) አትዘን ማለት ተወረደ።»} [ሁድ፡ 36] ያመኑትን ተከታዮቻቸውን ሁሉ የሚጭኑበት መርከብ እንዲሠሩ ትእዛዝን አስተላለፈላቸው። {ከወገኖቹም መሪዎቹ በእርሱ አጠገብ ባለፉ ቁጥር ከእርሱ እየተሳለቁ መርከቢቱን ይሠራል። «ከእኛ ብትሳለቁ እኛም እንደተሳለቃችሁብን ከናንተ እንሳለቅባችኋለን» አላቸው።} {«የሚያዋርደው ቅጣት የሚመጣበትን በእርሱም ላይ ዘውታሪ ቅጣት የሚሰፍርበት ሰው (ማን እንደ ሆነ) ወደፊት ታውቃላችሁ» (አላቸው)።} {ትእዛዛችንም በመጣና እቶኑም በገነፈለ ጊዜ «በእርሷ ውስጥ ከየዓይነቱ ሁሉ ሁለት ሁለት (ወንድና ሴት) ፤ ቤተሰቦችህንም ቃል ያለፈበት ብቻ ሲቀር ያመነንም ሰው ሁሉ ጫን» አልነው። ከእርሱም ጋር ጥቂቶች እንጂ አላመኑም።} {«መሄዷም መቆሚያም በአላህ ስም ነው እያላችሁም በውስጧ ተሳፈሩ. ጌታ መሓሪ አዛኝ ነውና» አላቸው.} {እርሷም እንደ ተራራዎች በሆነ ማዕበል ውስጥ በእነርሱ (ይዛቸው) የምትንሻለል ስትሆን (በአላህ ስም ተቀመጡባት)። ኑሕም ልጁን ከመርከቢቱ የራቀ ሆኖ ሳለ «ልጄ ሆይ! ከኛ ጋር ተሳፈር ከከሓዲዎቹም አትሁን» ሲል ጠራው።} {(ልጁም) «ከውሃው ወደሚጠብቀኝ ተራራ እጠጋለሁ» አለ። (አባቱም)፡- «ዛሬ ከአላህ ትዕዛዝ ምንም ጠባቂ የለም (እርሱ) ያዘነለት ካልሆነ በቀር» አለው። ማዕበሉም በመካከላቸው ጋረደ። ከሰጣሚዎቹም ሆነ።} {ተባለም፡- «ምድር ሆይ! ውሃሽን ዋጪ። ሰማይም ሆይ (ዝናብሽን) ያዝ። ውሃውም ሰረገ። ቅጣቱም ተፈጸመ። ጁዲይ በሚባልም ተራራ ላይ (መርከቢቱ) ተደላደለች። ለከሓዲዎችም ሰዎች ጥፋት ተገባቸው (ጠፉ)» ተባለ።} {ኑሕም ጌታውን ጠራ። አለም «ጌታዬ ሆይ! ልጄ ከቤተሰቤ ነው። ኪዳንህም እውነት ነው። አንተም ከፈራጆች ሁሉ ይበልጥ ዐዋቂ ነህ።»} {(አላህም) «ኑሕ ሆይ! እርሱ ከቤተሰብህ አይደለም፤ እርሱ መልካም ያልሆነ ሥራ ነው፤ በርሱ ዕውቀት የሌለህንም ነገር አትጠይቀኝ፤ እኔ ከሚሳሳቱት ሰዎች እንዳትሆን እገስጽሀለሁ» አለ።} {«ጌታዬ ሆይ! በእርሱ ለእኔ ዕውቀት የሌለኝን ነገር የምጠይቅህ ከመሆን እኔ ባንተ እጠበቃለሁ። ለእኔም ባትምረኝና ባታዝንልኝ ከከሳሪዎቹ እሆናለሁ» አለ።} {«ኑሕ ሆይ! ከእኛ በሆነ ሰላም ባንተ ላይና አንተም ጋር ባሉት ሕዝቦች (ትውልድ) ላይ በሆኑ በረከቶችም የተጎናጸፍክ ሆነህ ውረድ። (ከእነሱው ዘሮች የሆኑ) ሕዝቦችም በቅርቢቱ ዓለም በእርግጥ እናስመቻቸዋለን። ከዚያም ከኛ የሆነ አሳማሚ ቅጣት ይነካቸዋል» ተባለ።} [ሁድ፡ 38_48]

## መ - ነቢዩ ሁድ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)

ከዚያም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ አላህ አሕቃፍ በምትባል አካባቢ ወደሚኖሩ ዓድ ነገድ ማህበረሰብ -ጠምመው ከአላህ ውጭ ማምለክ በጀመሩ ጊዜ - ከእነሱ የሆኑትን ሁድ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) መልእክተኛ አድርጎ ላከላቸው።

ይህንንም በማስመልከት የላቀው አላህ በሚከተለው መልኩ ነግሮናል፦ {ወደ ዓድም ወንድማቸውን ሁድን ላክን። «ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ። ከእርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም። (የአላህን ቅጣት) አትፈሩምን» አላቸው።} {ከሕዝቦቹ እነዚያ የካዱት መሪዎች «እኛ በሞኝነት ላይ ኾነህ በእርግጥ እናይሃለን። እኛም ከውሸተኞቹ ነህ ብለን እንጠረጥርሃለን» አሉት።} {(እርሱም) አላቸው «ወገኖቼ ሆይ! እኔ ሞኝነት የለብኝም። ግን እኔ ከዓለማት ጌታ የተላክሁ ነኝ።»} {«የጌታዬን መልክቶች አደርስላችኋለሁ። እኔም ለእናንተ ታማኝ መካሪ ነኝ።»} {«ከጌታችሁ የኾነ ግሣጼ ከእናንተው ውስጥ ባንድ ሰው ላይ ያስጠነቀቃችሁ ዘንድ ቢመጣባችሁ ትደነቃላችሁን ከኑሕም ሕዝቦች በኋላ ምትኮች ባደረጋችሁና በፍጠረትም ግዙፍነትን በጨመረላችሁ ጊዜ አስታውሱ። የሻችሁትንም ታገኙ ዘንድ የአላህን ጸጋዎች አስታውሱ።»} {«አላህን ብቻውን እንድንገዛ አባቶቻችንም ይገዙት የነበረውን (አማልክት) እንድንተው መጣህብን ከውነተኞች ከኾንክ የምታስፈራራብንን (ቅጣት) አምጣብን» አሉ።} {«ከጌታችሁ የኾነ ቅጣትና ቁጣ በእናንተ ላይ በእውነት ተረጋገጠ። እናንተና አባቶቻችሁም (አማልክት ብላችሁ) በጠራችኋቸው ስሞች አላህ በእርሷ ምንም ማስረጃ ያላወረደባት ስትኾን ትከራከሩኛላችሁን ተጠባበቁም እኔ ከእናንተ ጋር ከተጠባባቂዎቹ ነኝና» አለ።} {እርሱንና እነዚያንም አብረውት የነበሩትን ከእኛ በኾነው ችሮታ (ከቅጣት) አዳንናቸው። የእነዚያንም በተአምራታችን ያስተባበሉትንና አማኞች ያልነበሩትን መሠረት ቆረጥን።} [አል-አዕራፍ፡ 65-72]

አላህም በእነሱ ላይ ለስምንት ቀናት ውስጥ በጌታዋም ፍቃድ ሁሉንም ነገር በምታጠፋ በሆነች የምትንሿሿ ብርቱ ነፋስን ላከባቸው፤ ነብዩሏህ ሁድ(የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እና እነዚያን ከእርሳቸው ጋር ያመኑትን አላህ አዳናቸው።

## ረ - ነቢዩ ሷሊሕ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)

ከዚያም የተወሰኑ ጊዜያቶች አለፉና ከአረብ ባህረ ገብ በስተ ሰሜን በኩል ባለ አካባቢ የሰሙድ ማህበረሰብ ተነሥተው እነዚያ ከእነሱ በፊት የነበሩት እንደጠመሙት እነርሱም ከመመሪያው ጠመሙ። አላህም ከእነሱ መካከል የሆነ (ሷሊህ) (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የተባሉ መልእክተኛን ወደ እነርሱ ላከላቸው፤ እውነተኛ የአላህ መልዕክተኝነታቸውን በሚያመለክቱ ተአምራትም አጠናከራቸው፤ ይኸውም ከፍጡራን ጋር አምሳያ የሌላት በሆነችው ታላቅ ግመል ነበር። ጥራት ይገባውና የላቀው አላህ በዚህ መልኩ ታሪኩን ነግሮናል፦ {ወደ ሰሙድም ወንድማቸውን ሷሊህን ላክን። አላቸው «ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ። ከእርሱ ሌላ ለእናንተ ምንም አምላክ የላችሁም። (እውነተኛ ለመኾኔ) ከጌታችሁ የኾነች ምልክት በእርግጥ መጥታላችኋለች። ይህች ለእናንተ ተዓምር ስትኾን የአላህ ግመል ናትና ተዋት። በአላህ ምድር ውስጥ ትብላ፤ (ትጠጣም)። በክፉ አትንኳትም። አሳማሚ ቅጣት ይይዛችኋልና።»} {«ከዓድም በኋላ ምትኮች ባደረጋችሁና በምድሪቱም ላይ ባስቀመጣችሁ ጊዜ አስታውሱ። ከሜዳዎቿ (ሸክላ) ሕንጻዎችን ትገነባላችሁ። ከተራራዎችም ቤቶችን ትጠርባላችሁ። ስለዚህ የአላህን ጸጋዎች አስታውሱ። በምድርም ውስጥ አጥፊዎች ኾናችሁ አታበላሹ።»} {ከወገኖቹ እነዚያ የኮሩት መሪዎች ለእነዚያ ለተሸነፉት ከነሱ ላመኑት፦ «ሷሊህ ከጌታው መላኩን ታውቃላችሁን» አሏቸው። « (አዎን)፦ እኛ እርሱ በተላከበት ነገር አማኞች ነን» አሉ።} {እነዚያ የኮሩት፦ «እኛ በዚያ እናንተ በርሱ ባመናችሁበት ከሓዲዎች ነን» አሉ።} {ወዲያውም ግመሊቱን ወጓት። ከጌታቸውም ትዕዛዝ ወጡ። አሉም፦ «ሷሊህ ሆይ! ከመልክተኞቹ እንደኾንክ የምታስፈራራብንን (ቅጣት) አምጣብን።»} {ወዲያውም የምድር መንቀጥቀጥ (ጩኸትም) ያዘቻቸው። በቤቶቻቸውም ውስጥ ተንከፍርረው አነጉ።} {(ሷሊህ) ከእነርሱም ዞረ። (እንዲህም) አለ «ወገኖቼ ሆይ! የጌታዬን መልክት በእርግጥ አደረስኩላችሁ። ለእናንተም መከርኳችሁ። ግን መካሪዎችን አትወዱም።»} [አል-አዕራፍ፡ 73-79] ከዚህም በኋላ አላህ ብዙ መልክተኞችን ወደ ምድር ሕዝቦች ላከ። በውስጧ አስጠንቃቂ መልዕክተኛ ያላሳለፈች ሕዝብም አልነበረችም። አላህ ስለ ጥቂቶቹ የነገረን ቢሆንም ያልነገረን ብዙዎችም አሉ። ሁሉም ታዲያ አንድ መልእክት ብቻ ነው ለህዝባቸው ያስተላለፉት፤ ይኸውም ሰዎች ተጋሪ ሳያደርጉለት በብቸኝነት አላህን እንዲያመልኩ እና ከአላህ ውጪ ያለ አምልኮን እርግፍ አድርገው እንዲተዉ ማዘዝ ነው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡ {በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ «አላህን ተገዙ፤ ጣዖትንም ራቁ» በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል። ከእነሱም ውስጥ አላህ ያቀናው ሰው አልለ። ከእነሱም ውስጥ በእርሱ ላይ ጥመት የተረጋገጠበት ሰው አልለ። በምድርም ላይ ኺዱ፤ የአስተባባዮችም መጨረሻ እንዴት እንደ ነበረ ተመልከቱ።} [አን-ነሕል 36]

## ሰ - ነቢዩ ኢብራሂም (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)

ከዚያም አላህ ኢብራሂምን (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ህዝቦቹ ጠምመው ከዋክብትንና ጣዖታትን የሚያመልኩ በሆኑበት ጊዜ ወደ እነርሱ መልዕክተኛ ሆነው ተላኩ። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {ለኢብራሂምም ከዚያ በፊት ቅን መንገዱን በእርግጥ ሰጠነው። እኛም በእርሱ (ተገቢነት) ዐዋቂዎች ነበርን።} {ለአባቱና ለሕዝቦቹ «ይህቺ ቅርጻ ቅርጽ ያቺ እናንተ ለእርሷ ተገዢዎች የኾናችሁት ምንድን ናት» ባለ ጊዜ (መራነው)።} {«አባቶቻችንን ለእርሷ ተገዢዎች ኾነው አገኘን» አሉት።} {«እናንተም አባቶቻችሁም በእርግጥ በግልጽ ስህተት ውስጥ ነበራችሁ» አላቸው።} {«በምሩ መጣህልን ወይንስ አንተ ከሚቀልዱት ነህ» አሉት።} {«አይደለም ጌታችሁ የሰማያትና የምድር ጌታ ያ የፈጠራቸው ነው። እኔም በዚህ ላይ ከመስካሪዎቹ ነኝ» አለ።} {«በአላህም እምላለሁ ዟሪዎች ኾናችሁ ከሄዳችሁ በኋላ ጣዖቶቻችሁን ተንኮል እሠራባቸዋለሁ» (አለ)።} {(ዘወር ሲሉ) ስብርብሮችም አደረጋቸው። ለእነሱ የኾነ አንድ ታላቅ (ጣዖት) ብቻ ሲቀር ወደርሱ ይመለሱ ዘንድ (እርሱን ተወው)።} {«በአማልክቶቻችን ይህንን የሠራ ማነው እርሱ በእርግጥ ከበደለኞች ነው» አሉ።} {«ኢብራሂም የሚባል ጎበዝ (በመጥፎ) ሲያነሳቸው ሰምተናል» ተባባሉ።} {«ይመሰክሩበት ዘንድ በሰዎቹ ዓይን (ፊት) ላይ አምጡት» አሉ።} {«ኢብራሂም ሆይ! በአማልክቶቻችን ይህንን የሠራህ አንተ ነህን» አሉት።} {«አይደለም ይህ ታላቃቸው ሠራው። ይናገሩም እንደ ኾነ ጠይቋቸው» አለ።} {ወደ ነፍሶቻቸውም ተመለሱ። «እናንተ (በመጠየቃችሁ) በዳዮቹ እናንተው ናችሁም» ተባባሉ።} {ከዚያም በራሶቻቸው ላይ ተገለበጡ። «እነዚህ የሚናገሩ አለመኾናቸውን በእርግጥ ዐውቀሃል፤» (አሉ)።} {«ታዲያ ለእናንተ ምንም የማይጠቅማችሁንና የማይጎዳችሁን ነገር ከአላህ ሌላ ትገዛላችሁን» አላቸው።} {«ፎህ! ለእናንተ ከአላህ ሌላ ለምትገዙትም ነገር፤ አታውቁምን» (አለ)።} {«ሠሪዎች እንደ ኾናችሁ አቃጥሉት። አማልክቶቻችሁንም እርዱ» አሉ። (በእሳት ላይ ጣሉትም)።} {«እሳት ሆይ! በኢብራሂም ላይ ቀዝቃዛ፤ ሰላምም ሁኚ» አልን።} {በእርሱም ተንኮልን አሰቡ። በጣም ከሳሪዎችም አደረግናቸው።} [አል-አንቢያእ፡ 50-70] ከዚያም ኢብራሂም (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እና ልጃቸው ኢስማኢል ከፍልስጤም ወደ መካ ተሰደዱ። አላህም እርሳቸውንና ልጃቸውን ኢስማዒልን ካዕባን እንዲገነቡ አዘዛቸው፤ ሰዎችንም ወደዛው ሓጅ እንዲያደርጉ እና አላህንም

እዛው እንዲያመልኩ ጋበዘ። {ወደ ኢብራሂምና ወደ ኢስማዒልም ቤቱን ለዘዋሪዎቹና ለተቀማጮቹም ለአጎንባሾች ሰጋጆቹም አጥሩ ስንል ቃል ኪዳን ያዝን።} [አል-በቀራህ: 125]

## ሸ - ነቢዩ ሉጥ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)

ከዚያም በኋላ አላህ ሉጥን ወደ ወገኖቹ ላከ እነርሱም ከአላህ ውጭም የሚያመልኩ በመካከላቸውም ዝሙትን የሚፈጽሙ ክፉ ሰዎች ነበሩ። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {ሉጥንም ለሕዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውስ)። «አስቀያሚን ሥራ ትሠራላችሁን በእርሷ ከዓለማት አንድም አልቀደማችሁም።»} {«እናንተ ከሴቶች ሌላ ወንዶችን በመከጀል በእርግጥ ትመጡባቸዋላችሁ። በእውነቱ እናንተ ወሰንን አላፊዎች ሕዝቦች ናችሁ።»} {የሕዝቦቹም መልስ « (ሎጥንና ተከታዮቹን) ከከተማችሁ አውጧቸው። እነሱ የሚጥራሩ ሰዎች ናቸውና» ማለት እንጂ ሌላ አልነበረም።} [አል-አዕራፍ: 80-82] አላህ እርሳቸውንና ቤተሰባቸውን ከከሀዲዎች ወገን ከሆነችው ሚስቱ በስተቀር አዳናቸው። ይኸውም አላህ እርሳቸውንና ቤተሰባቸውን ከመንደሩ እንዲወጡ በማዘዝ ነው። የአላህ ትእዛዝ በመጣማ ጊዜ የላይኛውን ዘቅዝቆ ወደ ታች ገለበጠው፤ ተከታታይ የሆነን የሸክላ ድንጋይም አዘነበባቸው።

## ቀ - ነቢዩ ሹዐይብ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)

ከዚያም አላህ ሰዎቹ ከጠመሙና በመካከላቸውም መጥፎ ስነምግባር፣ በሰዎች ላይ ግፈኝነት፣ በልኬት (ስፍር) እና ሚዛን ላይ ማዘባት ከተንሰራፋ በኋላ ለመድየን ህዝቦች ወንድማቸው ሹዓይብን ላከላቸው። ስለ እነሱም አላህ እንዲህ ሲል ነግሮናል፦ {ወደ መድየንም (ምድያን) ወንድማቸውን ሹዓይብን (ላክን)፤ አላቸው፦ «ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ። ከእርሱ በቀር ምንም አምላክ የላችሁም። ከጌታችሁ ዘንድ ግልጽ ማስረጃ በእርግጥ መጥታላችኋለች። ስፍርንና ሚዛንን ሙሉ። ሰዎችንም እንዳቸውን (ገንዘቦቻቸውን) አታጉድሉባቸው። በምድርም ውስጥ ከተበጀች በኋላ አታበላሹ። ይህ ምእምናን እንደኾናችሁ ለእናንተ የተሻለ ነው።»} {« (ሰዎችን) የምታስፈራሩና ከአላህም መንገድ በእርሱ ያመኑትን የምታግዱ መጥመሟንም የምትፈልጉዋት ኾናችሁ በየመንገዱ አትቀመጡ። ጥቂቶችም በነበራችሁና ባበዛችሁ ጊዜ አስታውሱ። የአጥፊዎችም መጨረሻ እንዴት እንደነበረ ተመልከቱ።»} {«ከእናንተም በዚያ እኔ በእርሱ በተላክሁበት ያመኑ ጭፍሮችና ያላመኑ ጭፍሮችም ቢኖሩ በመካከላችን አላህ እስከሚፈርድ ታገሱ። እርሱም ከፈራጆች ሁሉ በላጭ ነው።»} {ከሕዝቦቹ እነዚያ የኮሩት መሪዎች፦ «ሹዓይብ ሆይ! አንተንና እነዚያን ከአንተ ጋር ያመኑትን ከከተማችን በእርግጥ እናስወጣችኋለን። ወይም ወደ ሃይማኖታችን መመለስ አለባችሁ አሉ። የጠላንም ብንኾን» አላቸው።} {«አላህ ከእርሷ ከአዳነን በኋላ ወደ ሃይማኖታችሁ ብንመለስ በአላህ ላይ በእርግጥ ውሸትን ቀጠፍን። አላህ ጌታችን ካልሻም በስተቀር ለእኛ ወደእርሷ ልንመለስ አይገባንም። ጌታችን ዕውቀቱ ሁሉን ነገር ሰፋ። በአላህ ላይ ተጠጋን። ጌታችን ሆይ! በኛና በወገኖቻችን መካከል በውነት ፍረድ። አንተም ከፈራጆቹ ሁሉ በላጭ ነህ» (አለ)።} {ከወገኖቹም እነዚያ የካዱት መሪዎች «ሹዓይብን ብትከተሉ እናንተ ያን ጊዜ ከሳሪዎች ናችሁ» አሉ።} {ወዲያውም የምድር መንቀጥቀጥ (ጩኸትም) ያዘቻቸው። በቤቶቻቸውም ውስጥ ተንከፍርረው አነጉ።} {እነዚያ ሹዓይብን ያስተባበሉት በእርሷ እንዳልነበሩባት ኾኑ። እነዚ ሹዓይብን ያስተባበሉት እነርሱ ከሳሪዎች ኾኑ።} {ከእነርሱም (ትቷቸው) ዞረ፦ «ወገኖቼ ሆይ! የጌታዬን መልክቶች በእርግጥ አደረስኩላችሁ። ለእናንተም መከርኩ። ታዲያ በከሓዲዎች ሰዎች ላይ እንዴት አዝናለሁ።» አለም።} [አል-አዕራፍ፡ 85-93]

## በ - ነቢዩ ሙሳ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)

ያን ጊዜ አምላክ ነኝ ባይ የሆነው ፊርዓውን የተባለ ጨካኝና ትዕቢተኛ፤ ሰዎች እንዲሰግዱለት የሚያዝ፤ ያሻውን እያረደ ያሻውን የሚጨቁን ንጉስ ተነሳ። ጥራት ይገባውና የላቀው አላህም ስለ እርሱ እንዲህ ሲል ነግሮናል፦ {ፊርዖን በምድር ላይ ተንበጣረረ። ነዋሪዎቿንም የተከፋፈሉ ጓዶች አደረጋቸው። ከእነርሱ ጭፍሮችን ያዳክማል። ወንዶች ልጆቻቸውን በብዛት ያርዳል። ሴቶቻቸውንም ይተዋል፤ እርሱ ከሚያበላሹት ሰዎች ነበርና።} {በእነዚያም በምድር ውስጥ በተጨቆኑ ላይ ልንለግስ፣ መሪዎችም ልናደርጋቸው ወራሾችም ልናደርጋቸው እንሻለን።} {ለእነርሱም በምድር ላይ ልናስመች ፈርዖንንና ሃማንንም ሰራዊቶቻቸውንም ከእነሱ ይፈሩት የነበሩትን ነገር ልናሳያቸው (እንሻለን)።} {ወደ ሙሳም እናት «አጥቢው፣ በርሱም ላይ በፈራሽ ጊዜ በባሕሩ ውስጥ ጣይው አትፈሪም፣ አትዘኝም፣ እኛ ወዳንቺ መላሾቹና ከመልክተኞቹም አድራጊዎቹ ነንና» ማለትን አመለከትን።} {የፊርዖን ቤተሰቦችም (መጨረሻው) ለእነርሱ ጠላት ሐዘንም ይሆን ዘንድ አነሱት። ፊርዖንና ሃማንም ሰራዊቶቻቸውም ሀጢአተኞች ነበሩ።} {የፊርዖንም ሚስት «ለእኔ የዓይኔ መርጊያ ነው። ለአንተም አትግደሉት ሊጠቅመን ወይም ልጅ አድርገን ልንይዘው ይከጀላልና» አለች። እነርሱም (ፍጻሜውን) የማያውቁ ሆነው (አነሱት)።} {የሙሳም እናት ልብ ባዶ ሆነ። ከምእምናን ትሆን ዘንድ በልቧ ላይ ባላጠነከርን ኖሮ ልትገልጸው ቀርባ ነበር።} {ለእኅቱም ተከታተይው አለቻት። እርሱንም እነሱ የማያውቁ ሲሆኑ በሩቅ ሆና አየችው።} {(ወደናቱ ከመመለሱ) በፊትም አጥቢዎችን (መጥባትን) በእርሱ ላይ እርም አደረግን። (እኅቱ) «ለእናንተ የሚያሳድጉላችሁን እነርሱም ለእርሱ ቅን አገልጋዮች የሆኑን ቤተሰቦች ላመልክታችሁን» አለችም።} {ወደእናቱም ዓይንዋ እንድትረጋ፣ እንዳታዝንም፣ የአላህም የተስፋ ቃል እርግጥ መሆኑን እንድታውቅ መለስነው። ግን አብዛኞቻቸው አያውቁም።} {ብርታቱንም በደረሰና በተስተካከለ ጊዜ ጥበብንና ዕውቀትን ሰጠነው። እንዲሁም መልካም ሠሪዎችን እንመነዳለን።} {ከተማይቱንም ሰዎቿ በዝንጋቴ ጊዜ ላይ ሆነው ሳሉ ገባ። በእርሷም ውስጥ የሚጋደሉን ሁለት ሰዎችን አገኘ። ይህ ከወገኑ ነው፤ ይህም ከጠላቱ ነው። ያም ከወገኑ የሆነው ሰው በዚያ ከጠላቱ በሆነው ሰው ላይ እርዳታን ጠየቀው። ሙሳም በጡጫ መታው። ገደለውም። ይህ ከሰይጣን ሥራ ነው። እርሱ ግልጽ አሳሳች ጠላት ነውና አለ።} {«ጌታዬ ሆይ! እኔ ነፍሴን በደልኩ። ለእኔም ማር አለ።» ለእርሱም ምሕረት አደረገለት እርሱ መሓሪ አዛኝ ነውና።} {«ጌታዬ ሆይ! በእኔ ላይ በመለገስህ ይሁንብኝ (ከስህተቴ እጸጸታለሁ)፤ ለአመጸኞችም ፈጽሞ ረዳት አልሆንም አለ።} {በከተማይቱም ውስጥ ፈሪ የሚጠባበቅ ሆኖ አደረ። በድንገትም ያ ትላንት እርዳታን የጠየቀው ሰው በጩኸት እርዳታን ይጠይቀዋል። ሙሳ ለርሱ «አንተ በእርግጥ ግልጽ ጠማማ ነህ» አለው።} {(ሙሳ) ያንን እርሱ ለሁለቱም ጠላት የሆነውን ሰው በኃይል ሊይዘው በፈለገም ጊዜ «ሙሳ ሆይ! በትላንትናው ቀን ነፍስን እንደ ገደልክ ልትገድለኝ ትፈልጋለህን በምድር ለይ ጨካኝ መሆንን እንጅ ሌላ አትፈልግም። ከመልካም ሠሪዎችም መሆንን አትፈልግም» አለው።} {ከከተማይቱም ዳርቻ አንድ ሰው እየሮጠ መጣ። «ሙሳ ሆይ! ሹማምንቶቹ ሊገድሉህ ባንተ ይመካከራሉና ውጣ። እኔ ላንተ ከመካሪዎች ነኝና» አለው።} {የፈራና የሚጠባበቅ ሆኖም ከእርሷ ወጣ። «ጌታዬ ሆይ! ከበደለኞቹ ሕዝቦች አድነኝ» አለ።} {ወደ መድየን አቅጣጫ ፊቱን ባዞረ ጊዜም «ጌታዬ ቀጥተኛውን መንገድ ሊመራኝ እከጅላለሁ» አለ።} {ወደ መድየንም ውሃ በመጣ

ጊዜ በእርሱ ላይ ከሰዎች ጭፍሮችን (መንጋዎቻቸውን) የሚያጠጡ ሆነው አገኘ። ከእነርሱ በታችም (ከውሃው መንጎቻቸውን) የሚከለክሉን ሁለት ሴቶች አገኘ። «ነገራችሁ ምንድን ነው» አላቸው። «እረኞቹ ሁሉ (መንጋዎቻቸውን) እስከሚመልሱ አናጠጣም። አባታችንም ትልቅ ሽማግሌ ነው» አሉት።} {ለሁለቱም አጠጣላቸው። ከዚያም ወደ ጥላው ዘወር አለ። «ጌታዬ ሆይ! እኔ ከመልካም ነገር ወደኔ ለምታወርደው ፈላጊ ነኝ» አለ።} {ከሁለቱ አንደኛይቱም ከሐፍረት ጋር የምትኼድ ሆና መጣችው። «አባቴ ለእኛ ያጠጣህልንን ዋጋ ሊሰጥህ ይጠራሃል» አለችው። ወደእርሱ በመጣና ወሬውን በእርሱ ላይ በተረከለትም ጊዜ «አትፍራ ከበደለኞቹ ሕዝቦች ድነሃል» አለው።} {ከሁለቱ አንደኛይቱም «አባቴ ሆይ ቅጠረው። ከቀጠርከው ሰው ሁሉ በላጩ ብርቱው ታማኙ ነውና» አለችው።} {«ስምንትን ዓመታት ልታገለግለኝ እኔ ከእነዚህ ሁለት ሴቶቸ ልጆቼ አንዲቱን ላጋባህ እሻለሁ። ዐስርን ብትሞላም ከአንተ ነው። ባንተ ላይ ማስቸገርንም አልሻም። አላህ የሻ እንደ ኾነ ከመልካሞቹ ሰዎች ኾኜ ታገኘኛለህ» አለው።} {(ሙሳም) «ይህ (ውለታ) በእኔና ባንተ መካከል (ረጊ) ነው። ከሁለቱ ጊዜያቶች ማንኛውንም ብፈጽም በእኔ ላይ ወሰን ማለፍ የለም። አላህም በምንለነው ላይ ምስክር» ነው አለ።} {ሙሳም ጊዜውን በጨረሰና ከቤተሰቦቹ ጋር በኼደ ጊዜ ከጡር ተራራ ጎን እሳትን አየ። ለቤተሰቡ (እዚህ) «ቆዩ እኔ እሳትን አየሁ። ከእርሷ ወሬን ወይም ትሞቁ ዘንድ ከእሳት ትንታግን አመጣላችኋለሁ» አለ።} {በመጣትም ጊዜ ከሸለቆው ቀኝ ዳርቻ ከዛፊቱ በኩል በተባረከችው ስፍራ ውስጥ «ሙሳ ሆይ! እኔ የዓለማት ጌታ አላህ እኔ ነኝ» በማለት ተጠራ።} {«በትርህንም ጣል» (ተባለ)። እንደ ትንሽ እባብ ስትስለከለክ ባያትም ጊዜ ወደ ኋላ ዞሮ ሸሸ፤ አልተመለሰምም። «ሙሳ ሆይ! ተመለስ አትፍራም፤ አንተ ከጥብቆቹ ነህና» (ተባለም)።} {«እጅህን በአንገትጌህ ውስጥ አግባ። ያለ ነውር ነጭ ሆና ትወጣለችና። ክንፍህንም ከፍርሃት (ለመዳን) ወዳንተ አጣብቅ። እነዚህም ከጌታህ የሆኑ ወደ ፈርዖንና ወደ መኳንንቶቹ የሚደርሱ ሁለት አስረጅዎች ናቸው። እነርሱ አመጸኞች ሕዝቦች ነበሩና።»} {(ሙሳ) አለ «ጌታዬ ሆይ! እኔ ከእነርሱ ነፍስን ገድያለሁ። ስለዚህ እንዳይገድሉኝ እፈራለሁ።} {«ወንድሜም ሃሩን እርሱ ምላሱ ከእኔ የተባ ነው። እውነተኛነቴንም የሚያረጋግጥልኝ ረዳት ኾኖ ከእኔ ጋር ላከው። እኔ ሊያስተባብሉኝ እፈራለሁና።»} {(አላህም) «ጡንቻህን በወንድምህ በእርግጥ እናበረታለን። ለሁለታችሁም ስልጣንን እናደርጋለን። ወደእናንተም (በመጥፎ) አይደርሱም። በተዓምራቶቻችን (ኺዱ)። እናንተና የተከተላችሁም ሁሉ አሸናፊዎች ናችሁ» አላቸው።} [አልቀሶስ፡ 4-35]
ሙሳና ወንድሙ ሃሩንም ወደ ፊርዓውን - ትዕቢተኛው ንጉሥ - ሄደው የዓለማቱ ጌታ አላህን እንዲገዛ ጥሪ (ዳዕዋ) አደረጉለት። {ፊርዖን አለ «(ላከኝ የምትለው) የዓለማትም ጌታ ምንድነው»} {(ሙሳ) «የሰማያትና የምድር በመካከላቸውም ያለው ሁሉ ጌታ ነው። የምታረጋግጡ ብትኾኑ (ነገሩ ይህ ነው)፤» አለው።} {(ፊርዖንም) በዙሪያው ላሉት ሰዎች «አትሰሙምን» አለ።} {(ሙሳ) «ጌታችሁና የመጀመሪያዎቹ አባቶቻችሁም ጌታ ነው» አለው።} {(ፊርዖን) «ያ ወደእናንተ የተላከው መልክተኛችሁ በእርግጥ ዕብድ ነው» አለ።} {(ሙሳ) «የምሥራቅና የምዕራብ በመካከላቸውም ያለው ነገር ሁሉ ጌታ ነው። ታውቁ እንደኾናችሁ (እመኑበት)» አለው።} {(ፊርዖን) «ከእኔ ሌላ አምላክን ብትይዝ በውነቱ ከእስረኞቹ አደርግሃለሁ» አለ።} {(ሙሳ) «በግልጽ አስረጅ ብመጣህም እንኳ» አለው።} {«እንግዲያውስ ከእውነተኞች እንደኾንክ (አስረጁን) አምጣው» አለ።} {በትሩንም ጣለ። እርስዋም ወዲያውኑ ግልጽ እባብ ኾነች።} {እጁንም አወጣ። እርሷም ወዲያውኑ ለተመልካቾች ነጭ ኾነች።} {(ፊርዖን) በዙሪያው ላሉት መማክርት «ይህ በእርግጥ ዐዋቂ ድግምተኛ ነው» አለ።} {«ከምድራችሁ በድግምቱ ሊያወጣችሁ ይፈልጋልና ምንን ታዛላችሁ» (አላቸው)።} {አሉት «እርሱን ወንድሙንም አቆይና በየከተሞቹ ሰብሳቢዎችን ላክ።} {«በጣም ዐዋቂ ድግምተኞችን ሁሉ ያመጡልሃልና።»} {ድግምተኞቹም በታወቀ ቀን ቀጠሮ ተሰበሰቡ።} {ለሰዎቹም «እናንተ ተሰብስባችኋልን» ተባለ።} {«ድግምተኞቹን እነሱ አሸናፊዎች ቢኾኑ እንከተል ዘንድ» (ተባለ)።} {«ድግምተኞቹም በመጡ ጊዜ ለፈርዖን እኛ አሸናፊዎች ብንሆን ለእኛ በእርግጥ ዋጋ አለን» አሉት።} {«አዎን፤ እናንተም ያን ጊዜ ከባለሟሎቹ ትኾናላችሁ» አላቸው።} {ሙሳ «ለእነርሱ እናንተ የምትጥሉትን ጣሉ» አላቸው።} {ገመዶቻቸውንና በትሮቻቸውንም ጣሉ። «በፈርዖንም ክብር ይኹንብን። እኛ በእርግጥ አሸናፊዎቹ እኛ ነን» አሉ።} {ሙሳም በትሩን ጣለ። ወዲያውም እርሷ የሚያስመስሉትን ሁሉ ትውጣለች።} {ድግምተኞቹም ሰጋጆች ኾነው ወደቁ።} {አሉ፡- «በዓለማት ጌታ አመንን።»} {«በሙሳና በሃሩን ጌታ።»} {(ፈርዖንም) «ለእናንተ ሳልፈቅድላችሁ በፊት ለእርሱ አመናችሁን እርሱ ያ ድግምትን ያስተማራችሁ ታላቃችሁ ነው። ወደፊትም (የሚያገኛችሁን) በእርግጥ ታውቃላችሁ። እጆቻችሁንና እግሮቻችሁን (ቀኝና ግራን) በማናጋት እቆረርጣለሁ። ሁላችሁንም እሰቅላችኋለሁም» አለ።} {(እነርሱም) አሉ «ጉዳት የለብንም። እኛ ወደ ጌታችን ተመላሾች ነን።} {«እኛ የምእምናን መጀመሪያ በመኾናችን ጌታችን ኀጢአቶቻችንን ለእኛ ሊምር እንከጅላለን።»} {ወደ ሙሳም «ባሮቼን ይዘህ ሌሊት ኺድ። እናንተ የሚከተሉዋችሁ ናችሁና» ስንል ላክን።} {ፊርዖንም በየከተሞቹ ሰብሳቢዎችን (እንዲህ ሲል) ላከ።} {«እነዚህ ጥቂቶች ጭፈሮች ናቸው።} {«እነርሱም ለእኛ አስቆጪዎች ናቸው።} {«እኛም ብዙዎች ጥንቁቆች ነን፤» (አለ)።} {አወጣናቸውም። ከአትክልቶችና ከምንጮች።} {ከድልቦችም ከመልካም መቀመጫዎችም።} {እንደዚሁ ለእስራኤል ልጆች አወረስናትም።} {ፀሐይዋ ስትወጣም ተከተሉዋቸው።} {ሁለቱ ጭፍሮችም በተያዩ ጊዜ የሙሳ ጓዶች «እኛ(የፈርዖን ሰዎች) የሚደርሱብን ነን» አሉ።} {(ሙሳ) «ተዉዉ! ጌታዬ ከእኔ ጋር ነው። በእርግጥ ይመራኛል» አለ።} {ወደ ሙሳም «ባሕሩን በበትርህ ምታው» ስንል ላክንበት። (መታውና) ተከፈለም። ክፍሉም ሁሉ እንደ ታላቅ ጋራ ኾነ።} {እዚያም ዘንድ ሌሎችን አቀረብን።} {ሙሳንም ከእርሱ ገር ያሉትንም ሰዎች ሁሉንም አዳን።} {ከዚያም ሌሎቹን አሰጠምን።} {በዚህ ውስጥ ታላቅ ታምር አለበት። አብዛኞቻቸውም አማኞች አልነበሩም።} {ጌታህም እርሱ በእርግጥ አሸናፊ አዛኝ ነው።} [አሽ_ሹዓራእ፡ 23_67] ፊርዓውንም መስመጡን ባወቀ ጊዜ፡- የእስራኤል ልጆች ካመኑበት አምላክ በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ አምኛለሁ። አለ። የላቀው አላህ እንዲህ ነግሮናል፦ {ከአሁን በፊት በእርግጥ ያመጽክ ከአጥፊዎችም የነበርክ ስትሆን አሁን (አመንኩ ትላለህ)} {ዛሬማ ከኋላህ ላሉት ተዓምር ትሆን ዘንድ በድን ሆነህ (ከባሕሩ) እናወጣሃለን (ተባለ)። ከሰዎችም ብዙዎቹ ከተዓምራታችን በእርግጥ ዘንጊዎች ናቸው።} (ዩኑስ፡ 91-92)
አላህም ያች ምሥራቋንም ምዕራቧንም በረካ ያደረገባትን አገር ለነዚያ ለተጨቆኑት (ለሙሴ ሕዝቦች) አወረሳት። ለፊርዓውንና ለህዝቦቹም ይሰሩት የነበረውን (ህንፃ) ዳስ ያደርጉት የነበረውንም አጠፋ።
ከዚህም በኋላ አላህ ለሙሳ በውስጧ ሰዎችን አላህ ወደሚወደውና ወደሚቀበለው የሚያመላክት መመሪያና ብርሃን ያለባት፤ የእስራኤል ዝርዮች (የሙሳ ህዝቦች) ሊከተሉት ግዴታ የሆነባቸው የሐላልና የሐራም ማብራርያ አድርጎ የተውራትን መጽሐፍ አወረደ።

ከዚያም ሙሳ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሞቱና አላህም ከእርሳቸው በኋላ ለህዝባቸው - ለእስራኤል ልጆች - አንዱ በጠፋ ቁጥር በሌላኛው ነብይ እየተተካ ወደ ትክክለኛው መንገድ የሚመሩ ብዙ ነብያቶችን ላከ።
አላህ እንደ ዳውድ፣ ሱለይማን፣ አዩብና ዘከሪያ ያሉትን ጥቂቶቹን የተረከልን ሲሆን ከነብያቶች ያልተረከልን ብዙዎችም አሉ። ከዚያም እነዚህን ተከታታይ ነብያት ከውልደቱ ጀምሮ ወደ ሰማይ እስካረገበት ጊዜ ድረስ ሕይወታቸው በብዙ ተአምራት በተሞላው በዒሳ ብን መርየም (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) አጠናቀቀ።
አላህ ለሙሳ በትውልዶች የገለጠው ተውራት የሙሳ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ተከታዮች ነን በሚሉ ሙሳም ከእነሱ የጠሩ በሆኑት አይሁዶች እጅ መዛባትና መበረዝ ተጋረጠበት። በእጃቸው ያለው ተውራት ደግሞ ከአላህ ዘንድ የተወረደው ተውራት ተደርጎ አይቆጠርም፤ በውስጡ ለአላህ የማይገቡ ነገራቶችን አስገብተዋል፤ አላህንም በእንከን፣ ባለማወቅና በድክመት ባህሪያት ገልፀውታልና - አላህ እነርሱ ከሚሉት የላቀ ጥራት ይገባውና - ልዕለ ኋያሉ አላህ እነርሱን እንዲህ ሲል ነው የገለፃቸው፦ {ለነዚያም መጽሐፉን በእጆቻቸው ለሚጽፉና ከዚያም በርሱ ጥቂትን ዋጋ ሊገዙበት «ይህ ከአላህ ዘንድ ነው» ለሚሉ ወዮላቸው። ለነርሱም ከዚያ እጆቻቸው ከጻፉት ወዮላቸው። ለነሱም ከዚያ ከሚያፈሩት (ኃጢኣት) ወዮላቸው።} [አል-በቀራህ፡ 79]

## ተ - ነቢዩ ዒሳ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)

ንጽሕት የሆነችው የዒምራን ልጅ ድንግል መርየም ከሙሳ በኋላ በተላኩት ቅዱሳት መፃህፍት ያሉ መመርያዎችን በሚገባ የምትከተል ጥሩ የአላህ ባርያ እንዲሁም አላህ ከአለማት የመረጣቸው ቤተሰቦችም አባል ነበረች። ጥራት ይገባውና የላቀው አላህ በሚከተለው መልኩ እንዳለን፦ {አላህ አደምን፣ ኑሕንም፣ የኢብራሂምንም ቤተሰብ፣ የዒምራንንም ቤተሰብ በዓለማት ላይ መረጠ።} [አሊ-ዒምራን 33] መላእክትም አላህ የመረጣት eንደሆነች አብስረዋታል፦ {መላእክትም ያሉትን (አስታውስ)። «መርየም ሆይ! አላህ በእርግጥ መረጠሽ። አነጻሽም። በዓለማት ሴቶችም ላይ መረጠሽ።»} {«መርየም ሆይ! ለጌታሽ ታዘዢ። ስገጂም። ከአጎንባሾቹም ጋር አጎንብሺ።»} [አሊ-ዒምራን 42_43] ከዚያም ጥራት ይገባውና የላቀው አላህ ዒሳን በማህፀኗ ውስጥ ያለ አባት እንዴት እንደፈጠረውም በሚከተለው ቃሉ አሳወቀን፦ {በመጽሐፉ ውስጥ መርየምንም ከቤተሰቧ ወደ ምሥራቃዊ ስፍራ በተለየች ጊዜ (የሆነውን ታሪኳን) አውሳ።} {ከእነሱም መጋረጃን አደረገች። መንፈሳችንምም (ጂብሪልን) ወደርሷ ላክን። ለእርሷም ትክክለኛ ሰው ሆኖ ተመሰለላት።} {«እኔ ከአንተ በአልረሕማን እጠበቃለሁ። ጌታህን ፈሪ እንደ ሆንክ (አትቅረበኝ)» አለች።} {«እኔ ንጹሕን ልጅ ለአንቺ ልሰጥሽ የጌታሽ መልክተኛ ነኝ» አላት።} {«(በጋብቻ) ሰው ያልነካኝ ሆኜ አመንዝራም ሳልሆን ለእኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል!» አለች።} {አላት «(ነገሩ) እንደዚህሽ ነው።» ጌታሽ «እርሱ በእኔ ላይ ገር ነው። ለሰዎችም ታምር ከእኛም ችሮታ ልናደርገው (ይህንን ሠራን) የተፈረደም ነገር ነው» አለ፤ (ነፋባትም)።} {ወዲያውኑም አረገዘችው። በእርሱም (በሆዷ ይዛው) ወደ ሩቅ ስፍራ ገለል አለች።} {ምጡም ወደ ዘንባባይቱ ግንድ አስጠጋት። «ዋ ምኞቴ! ምነው ከዚህ በፊት በሞትኩ። ተረስቼም የቀረሁ በሆንኩ» አለች።} {ከበታቿም እንዲህ ሲል ጠራት «አትዘኚ። ጌታሽ ከበታችሽ ትንሽን ወንዝ በእርግጥ አድርጓል።} {«የዘምባባይቱንም ግንድ ወዳንቺ ወዝውዥት ባንቺ ላይ የበሰለን የተምር እሸት ታረግፍልሻለችና።} {«ብይም፣ ጠጭም፣ ተደሰችም። እኔ ለአልረሕማን ዝምታን ተስያለሁ፤ ዛሬም ሰውን በፍጹም አላነጋግርም» በይ።} {በእርሱም የተሸከመቺው ሆና ወደ ዘመዶቿ መጣች። «መርየም ሆይ! ከባድን ነገር በእርግጥ ሠራሽ» አሏት።} {«የሃሩን እኅት ሆይ! አባትሽ መጥፎ ሰው አልነበረም። እናትሽም አመንዝራ አልነበረችም» አሏት።} {ወደርሱም ጠቀሰች። «በአንቀልባ ያለን ሕጻን እንዴት እናናግራለን!» አሉ።} {(ሕፃኑም) አለ «እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ። መጽሐፍን ሰጥቶኛል ነቢይም አድርጎኛል።»} {«በየትም ስፍራ ብሆን ብሩክ አድርጎኛል። በሕይወትም እስካለሁ ሶላትን በመስገድ ዘካንም በመስጠት አዞኛል።»} {«ለእናቴም ታዛዥ (አድርጎኛል)። ትዕቢተኛ እምቢተኛም አላደረገኝም።} {«ሰላምም በእኔ ላይ ነው። በተወለድሁ ቀን፣ በምሞትበትም ቀን፣ ሕያው ኾኜ በምቀሰቀስበትም ቀን።»} {ይህ የመርየም ልጅ ዒሳ ነው። ያ በርሱ የሚጠራጠሩበት እውነተኛ ቃል ነው።} {ለአላህ ልጅን መያዝ አይገባውም። (ከጉድለት ሁሉ) ጠራ። ነገርን በሻ ጊዜ ለርሱ የሚለው «ኹን» ነው ወዲያውም ይኾናል።} {(ዒሳ አለ) «አላህም ጌታዬ ጌታችሁም ነውና ተገዙት። ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው።»} [መርየም፡ 16-36] ከዚያም ነብዩሏህ ዒሳ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሰዎችን አላህን እንዲያመልኩ ጥሪ (ዳዕዋ) ሲያደርጉላቸው ብዙዎች ጀርባቸውን ቢሰጡም ጥሪያቸውን የተቀበሉም ግን ነበሩ። እርሳቸውም አምላኬ አምላካችሁ አላህን አምልኩ የሚለው ዳዕዋቸውን ቀጠሉ፤ ይሁን እንጂ ብዙዎቹ ዳዕዋውን አስተባበሉ፤ ጭራሽ አሴሩባቸውና እስከመግደል ሙከራም ደረሱ! የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {ዒሳ ሆይ! እኔ ወሳጂህ ወደ እኔም አንሺህ ነኝ። ከነዚያም ከካዱት ሰዎች አጥሪህ ነኝ} [አሊ-ዒምራን 55] በዚህም አላህ ዒሳን እያሳደዷቸው ከነበሩት መካከል በአንዱ ላይ የዒሳን ምስል ጣለበትና የመርየም ልጅ ዒሳን እያሰቡ ባልንጀራቸውን ቀፈደዱትም ሰቅለው ገደሉትም። የአላህ መልዕክተኛ ዒሳን ግን አላህ ወደ ሰማይ አንስቷቸዋልና አልደረሱባቸውም። በዚህ መልኩ ሆኖ ሙሉ ለሙሉ ዱኒያን ለቀው ከማረጋቸው በፊት ሃይማኖቱን የሚያሰራጭ አሕመድ የተባለን አፅናኝ መልዕክተኛ አላህ እንደሚልክ ለባልደረቦቹ ነግሯቸው ነበር። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {የመርየም ልጅ ዒሳም፦ «የእስራኤል ልጆች ሆይ! እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከእኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ በኾነው የማበስር ስኾን ወደእናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ» ባለ ጊዜ (አስታውስ)። በግልጽ ተዓምራቶች በመጣቸውም ጊዜ «ይህ ግልጽ ድግምት ነው» አሉ።} [አስ_ሶፍ፡ 6] ከዚያም የዒሳ ተከታዮችን እስከመከፋፈል ያደረሳቸው ጊዜ መጣች። በዚህም ዒሳን የአላህ -ጥራት ይገባውና- ልጅ ነው የሚል አንጃ እስከመፈጠር ደረሰ። የዒሳ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ያለ አባት መወለድም ለዚህ ጥመታቸው መታለያ ሆናቸው። የላቀው አላህ ይህን በማስመልከት በተከታዩ ቃሉ እንዲህ ብሏል፦ {አላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ እንደ አዳም ብጤ ነው። ከዐፈር ፈጠረው። ከዚያም ለርሱ (ሰው) «ሁን» አለው፤ ሆነም።} [አሊ-ዒምራን 59] የዒሳ ዓለይሂ ሰላም ያለ አባት መፈጠር ከአዳም ያለ አባትም ያለ እናትም ከመፈጠር በላይ የሚደንቅ አይደለም። ስለዚህም ነበር የላቀው አላህ በቁርኣን ውስጥ ለእስራኤል ልጆች ከዚህ የክህደት ቃል ሊርቁ ዘንድ እንዲህ በማለት ያነጋገራቸው፦ {እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ። በአላህም ላይ እውነትን እንጅ አትናገሩ። የመርየም ልጅ አልመሲሕ ዒሳ የአላህ መልክተኛ ወደ መርየም የጣላት «የኹን» ቃሉም ከእርሱ የኾነ መንፈስም ብቻ ነው። በአላህና በመልክተኞቹም እመኑ። « (አማልክት) ሦስት ናቸው» አትበሉም። ተከልከሉ፤ ለእናንተ የተሻለ ይኾናልና። አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው። ለእርሱ ልጅ ያለው ከመኾን የጠራ ነው። በሰማያትና በምድር ያለ ሁሉ የርሱ ነው። መመኪያም በአላህ በቃ።} {አልመሲሕ (ኢየሱስ) ለአላህ ባሪያ ከመኾን ፈጽሞ አይጠየፍም። ቀራቢዎች የኾኑት መላእክትም (አይጠየፉም)። እርሱን ከመገዛት

የሚጠየፍና የሚኮራም ሰው (አላህ) ሁሉንም ወደ እርሱ በእርግጥ ይሰበስባቸዋል።} {እነዚያማ ያመኑት መልካሞችንም የሠሩት ምንዳዎቻቸውን ይሞላላቸዋል። ከችሮታውም ይጨምርላቸዋል። እነዚያን የተጠየፉትንና የኮሩትንማ አሳማሚን ቅጣት ይቀጣቸዋል። ከአላህም ሌላ ለእነሱ ዝምድንና ረዳትን አያገኙም።} [አን_ኒሳእ፡ 171_173] አላህ የቂያማ እለት ዒሳ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ በማለት ያነጋግራቸዋል፦ {አላህም፦ «የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! አንተ ለሰዎቹ፦ እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብላሃልን» በሚለው ጊዜ (አስታውስ)። «ጥራት ይገባህ፤ ለእኔ ተገቢዬ ያልኾነን ነገር ማለት ለኔ አይገባኝም። ብዬው እንደ ኾነም በእርግጥ ዐውቀኸዋል። በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ። ግን አንተ ዘንድ ያለውን አላውቅም። አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም ዐዋቂ አንተ ብቻ ነህና» ይላል።} {«በእርሱ ያዘዝከኝን ቃል ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ ማለትን እንጂ ለነርሱ ሌላ አላልኩም። በውስጣቸውም እስካለሁ ድረስ በነርሱ ላይ ተጣባበቂ ነበርኩ። በተሞላኸኝም ጊዜ (ባነሳኸኝ ጊዜ) አንተ በነሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርክ። አንተም በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ ነህ።»} {«ብትቀጣቸው እነርሱ ባሮችህ ናቸው። ለነርሱ ብትምርም አንተ አሸናፊው ጥበበኛው ነህ።» (ይላል)።} {አላህም ይላል፦ «ይህ እውነተኞችን እውነታቸው የሚጠቅምበት ቀን ነው። ለእነርሱ በሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው በውስጣቸው ሁልጊዜ ዘውታሪዎች ሲኾኑ የሚኖሩባቸው ገነቶች አሉዋቸው። አላህ ከእነሱ ወደደ፤ እነርሱም ከእርሱ ወደዱ፤ ይህ ታላቅ ዕድል ነው።»} [አል-ማኢዳህ 116-119]

በመሆኑም የመርየም ልጅ ዒሳ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው ከሰየሙትና ራሳቸውን የነብዩ ዒሳ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ተከታዮች አድርገው ከሚቆጥሩት በሚልዮን የሚቆጠሩ ሰዎች የጠሩ ናቸው።

# 3. ሙሐመድ ﷺ የአላህ መልእክተኛ (የነቢያትና የመልዕክተኞች መደምደሚያ)

ዒሳ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ወደ ሰማይ ካረጉ በኋላ ወደ ስድስት መቶ ዓመታት ያህል ገደማ ረዥም ጊዜ አለፈና የሰዎችም ከቅኑ ጎዳና ማፈንገጥ ባሰ፤ ክህደት፣ ጥመትና ጣኦት አምልኮም ተሰራጨ። ስለዚህ አላህ ሙሐመድን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) በመካ አል ሙከረማህ (በተከበረችው መካ) በሂጃዝ ምድር በምራቻና በእውነተኛ ሃይማኖት ላካቸው። አላህን ብቻውን ያለ አጋር ማምለክ፣ ነብይነታቸውንና መልእክታቸውን የሚያመለክቱ ምልክቶችንና ተአምራትን ሰጣቸው፣ በእርሱም የመልክተኛነት ማህተም፣ ሃይማኖቱንም የሃይማኖቶች ማኅተም በማድረግ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ እና ቂያማም እስክትቆም ድረስ ከመቀየርና ከመለወጥ ይጠብቀዋል። ሙሐመድ ማነው? ሕዝቦቹስ እነማን ናቸው? እንዴትስ ተላኩ? ከነብይነት ተአምራቶቻቸው መካከልስ ምን ምን አሉ? የእርሳቸው የሕይወት ታሪክ ዝርዝርስ ምንድነው? አምላክ ፈቅዶ በእነዚህ አጭር ገጾች ላይ እነዚህን ለማብራራት እንሞክራለን።

## ዘራቸው እና ማህበራዊ ክብራቸው (ደረጃቸው)

እርሳቸው ሙሐመድ ቢን ዐብደሏህ ቢን ዐብዱል ሙጦሊብ ቢን ሃሺም ቢን ዓብዱል መናፍ ቢን ቁሶይ ቢን ኪላብ፤ የኢስማዒል ቢን ኢብራሂም (የአላህ ሰላም በእነርሱ ላይ ይሁን) ዘር፤ ከቁረይሽ ጎሣ ሲሆኑ ቁረይሽ ደግሞ ከዐረብ ነው። በ571 እ. ኤ. አ. በመካ ከተማ ተወለዱ። አባታቸው ገና በማህፀን ውስጥ እያሉ የሞተባቸው ሲሆን በአያታቸው ዐብዱል ሙጦሊብ እንክብካቤ ሥር ወላጅ አልባ ሆነው ኖሩ። ከዚያም አያታቸውም ሲሞቱ በአጎታቸው አቡ ጧሊብ እንክብካቤ ስር ሆነው አደጉ።

## ለ. ባሕርያቸው

ከፍ ብለን ለማየት እንደሞከርነው በአላህ የተመረጠ ነቢይ ከማንነት፣ ከእውነተኝነትና በጎ ስነምግባር አኳያ ከፍተኛ ስብእናን የተላበሰ ሊሆን ይገባዋል። እርሳቸውም ቢሆኑ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እውነተኛና ታማኝ፣ በመልካም ስነምግባር ያሸበረቁ፣ ልሳናቸው ጣፋጭና አንደበተ ርቱእ፣ የቅርቡም የሩቁም የሚወዳቸው፣ በማህበረሰባቸውም ዘንድ ማእረግ ያላቸው የተከበሩ፣ ታማኙ የሚል እንጅ በሌላ ቅፅል ስም የማይጠሯቸው፣ ለጉዞ ሲወጡም ሰዎች አደራ የሚጥሉባቸው ታላቅ ሰው ሆነው ነው ያደጉት።

ያላቸውን መልካም ቁመና በተመለከተ አይን አይታ የማትጠግባቸው፤ ነጭ ፊት ያላቸው፤ በሁለት ዓይናቸው መካከል ሰፊ ክፍተት ያላቸው፤ የዓይን ቅንድባቸው ረዥም፤ ፀጉራቸው ጥቁር፤ ትከሻቸው ሰፊ፤ በወንዶች መካከል ያላቸው ቁመናም ረዥምም አጭርም የማይባሉ ወደ ረዥምነት ያደሉ የተስተካከለ በአይን ታይቶ የማይጠገብ ያማረ ተክለ ሰውነት ነበራቸው። ከባልደረቦቻቸው አንዱ የገለፃቸውም እንዲህ ብሎ ነበር፦ "የአላህን መልእክተኛን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የየመን ልብስ ለብሰው አይቻቸው ነበር። ከርሳቸው የተሻለ ውብ በፍፁም አይቼ አላውቅም።" ማንበብና መጻፍ አይችሉም ነበር፣ ማንበብና መጻፍ የማይችል ማሕበረሰብ ውስጥ ከመካከላቸው ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ጥቂት ናቸው፤ ነገር ግን ብልህ፣ ጠንካራ ትውስታ፣ ፈጣን ማስተዋል ያላቸው ነበሩ።

## ሐ- ቁረይሾች እና ዐረቦች

ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲሁም ማህበረሰባቸው በተከበረችው የመካ ከተማ በሓረም ዙርያ አላህ ነብዩ ኢብራሂምንና ልጃቸው ኢስማዒልን (የአላህ ሰላም በእነርሱ ላይ ይሁን) ሊገነቡት ዘንድ ባዘዛቸው በተከበረው ካዕባ አጠገብ ነበር የሚኖሩት።

ነገር ግን ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ከኢብራሂም ሃይማኖት (አላህን በብቸኝነት ከማምለክ) በማፈንገጥ - እነርሱም በዙሪያቸው የነበሩት ነገዶችም - በካዕባ ዙሪያ የድንጋይ፣ የዛፍና የወርቅ ጣዖታትን አበጅተው የተቀደሱ አድርገውም በመቁጠር የመጥቀምና የመጉዳት ችሎታው እንዳላቸው እስከማሰብ ደረጃም ደረሱ! ለእርሷም የአምልኮ ስርዓቶችንም ቀነጨቡላት። ከነዚህም ውስጥ በጣም ዝነኛ የሆነው የሁበል ጣኦት ሲሆን ይህ ጣኦት እጅግ ትልቁና ታላቅ ብለው የሚያስቡትም ይህንኑ ነበር። ከመካ ውጭ ያሉ ሌሎች ጣዖታትና ዛፎች በተመለከተ እንደ ላት፣ ዑዛና መናት ያሉት ቅዱስነትን ያላብሷቸዋል። በዙሪያቸው ካሉት አከባቢዎች ጋር የነበራቸው ሕይወት ምንም እንኳን እንደ ጀግንነት፣ እንግዳ አክባሪነትና የንግግር ሓቀኝነት መሰል መልካም ስነ ምግባሮች

ቢኖሯቸውም በትዕቢት፣ ኩራትና ሌሎችን በመናቅ የተሞላ ነበር። በሌሎች ላይ ጥቃት በመሰንዘርና ዱቄት በሚያደርግ ጦርነትም የተሞላ ነበር።

## መ- የነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ተልዕኮ

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እድሜያቸው አርባ ዓመት ሲደርስና ከመካ ውጪ በሞቃታማ ምሽት በሒራእ ዋሻ ውስጥ በነበሩበት አጋጣሚ ከሰማይ የመጀመሪያው መለኮታዊ ራዕይ ከአላህ ዘንድ መጣላቸው (ወሕዩን አወረደላቸው)። መላኢካው ጂብሪል ወደ እርሳቸው መጣና ጨመቅ አድርጎ ይዞ "ኢቅራእ (አንብብ)" አላቸው፤ እርሳቸውም "እኔ አንባቢ አይደለሁም" አሉ፤ ከዚያም አሁንም ለሁለተኛ ጊዜ ጭንቅ ጥብብ እስኪላቸው ድረስ ጨመቅ አድርጎ ይዞ "ኢቅራእ (አንብብ)" አላቸው፤ እርሳቸውም "እኔ አንባቢ አይደለሁም" አሉ፤ ከዚያም ለሶስተኛ ጊዜ በጣም እስኪጨናነቁ ድረስ ጨመቅ አድርጎ ያዛቸውና "ኢቅራእ (አንብብ)" አላቸው፤ የዚህኔ እሳቸውም "ምንድን ነው የምቀራው/የማነበው?" አሉት። እሱም እንዲህ በማለት ቀጠለ፦ {አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም።} {ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)።} {አንብብ፤ ጌታህ በጣም ቸር ሲኾን፤} {ያ በብዕር ያስተማረ።} {ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲኾን።} [አልዓለቅ፡ 1_5]

ከዚያም መላኢካው ትቷቸው ሄደ። ነቢዩም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ፈርተውና ርደው ወደ ባልተቤታቸውና ወደ ቤታቸው ተመለሱ። ለባልተቤታቸው ኸዲጃም እንዲህ አሏት፦ "በራሴ ላይ ሰግቻለሁና አልብሺኝ" ባለቤታቸውም እንዲህ አለቻቸው- "በፍጹም አላህ የሚያሳፍርህ አይነት ሰው አይደለህም! አንተኮ ዝምድናን የምትቀጥል፣ የተጨነቀን የምታግዝ፣ አስፈላጊ በሆነበት ሁሉ የምትረዳ ሰው ነህ።

ከዚያም ጂብሪል አላህ በፈጠረበት ተፈጥሯዊ አኳኋኑ ሆኖ አድማሱን ሞልቶ ወደርሳቸው መጣና እንዲህ አላቸው፦ "ሙሐመድ ሆይ! እኔ ጂብሪል ነኝ፤ አንተ (ደግሞ) የአላህ መልክተኛ ነህ።"

ከዚያም ከሰማይ ተከታታይ የሆነ ወሕይ (መለኮታዊ ራዕይ) ህዝቡን ያለምንም ተጋሪ በብቸኝነት እንዲያመልኩ እና ከሽርክና ከክህደት እንዲጠነቀቁ የሚያዝ መመርያ ይወርድ ጀመር። ነብዩም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ህዝባቸው ወደ እስልምና ሃይማኖት እንዲገቡ አንድ በአንድ እና በቅርበታችው ልክ እያስቀደመ ዳዕዋ (ጥሪ) ማድረጋቸውን ቀጠሉ። ዳዕዋውን የተቀበሉት የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ባልተቤታቸው ኸዲጃ ቢንት ኹወይሊድ፣ ጓደኛቸው አቡበከር አስ-ሲዲቅና የአጎታቸው ልጅ ዓሊይ ቢን አቢ ጧሊብ ናቸው። አላህ እንዲህ ብሏል፦

ከዚያም ሕዝቡ ዳዕዋቸውን እየሰማ ሲመጣ ይጋፈጧቸው፣ ያሴሩባቸውና ይተናኮሏቸው ጀመር። አንድ ቀን ጠዋት ወደ ህዝቡ ወጥተው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ህዝቡን መሰብሰብ የፈለገ ሰው በተለምዶ የሚለውን ቃል ተጠቅመው እንዲህ አሉ "ዋ ሶባሓህ!" ብለው ተጣሩ። ህዝቡም ጥሪያቸውን እንደሰማ የሚሉትን ለመስማት ተከታትለው ተሰባሰቡ። የዛኔ እንዲህ አሏቸው፦ "እስኪ አሁን እኔ ጠላት ማልዶባችኃል ወይም መሽጎ አድፗል ብላችሁ ታምኑኛላችሁ?" ህዝቡም እንዲህ በማለት መለሰላቸው፦ "ዋሽተህን የማታውቀውን! እንዴት አናምንህም?" የዛኔ ቀጠል አድርገው "በሉ እንግዲህ እኔ ብርቱ ከሆነ ቅጣት አስቀድሜ የማስጠነቅቃችሁ ሰው ነኝ" አሏቸው። አጎቱ አቡ ለሀብ - ከአጎቶቹ አንዱ የሆነውና እርሱም ባልተቤቱም ለመልዕክተኛውና ለዲነል ኢስላም ጥልቅ ጥላቻ ያላቸው የሆኑት- "አፈር ብላ! ለዚህ ነው እንዴ የሰበሰብከን!" አላቸው። በዚህም የላቀው አላህ በመልዕክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ላይ እንዲህ የሚለውን የቁርአን አንቀፆች አወረደ፦ {የአቡ ለሀብ ሁለት እጆች ከሰሩ (ጠፉ፤ እርሱ) ከሰረም።} {ከእርሱ ገንዘቡና ያም ያፈራው ሁሉ ምንም አልጠቀመውም።} {የመንቀልቀል ባለቤት የኾነችን እሳት በእርግጥ ይገባል።} {ሚስቱም (ትገባለች)፤ እንጨት ተሸካሚ ስትኾን።} {በአንገትዋ ላይ ከጭረት የኾነ ገመድ ያለባት ስትኾን።} [አልመሰድ፡ 1_5]

ከዚያም ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ወደ ኢስላም የሚያደርጉትን ጥሪ ቀጠሉ። ‹‹ላ ኢላሃ ኢለሏህ በሉና ነፃ ትወጣላችሁ» ይሏቸዋል። እነርሱም «አማልክቶችንም ሁሉ አንድ አምላክ አደረጋቸው፤ ይህማ እጅግ የሚደንቅ ነገር ነው።›› አሉ። ካሉበት የጥመት ጎዳና ወጥተው ወደ ቀናው ጎዳና እንዲመጡ ጥሪ የሚያደርጉ አንቀጾችም ከአላህ ዘንድ መወረዳቸውን ቀጠሉ። በውስጣቸው ካሉት ጥሪዎችም የሚከተሉት የአላህ ቃል መጥቀስ ይቻላል፦ {በላቸው «እናንተ በዚያ ምድርን በሁለት ቀኖች ውስጥ በፈጠረው አምላክ በእርግጥ ትክዳላችሁን? ለእርሱም ባለንጣዎችን ታደርጋላችሁን? ያ (ይህንን የሠራው) የዓለማት ጌታ ነው።} {በእርሷም ከበላይዋ የረጉ ጋራዎችን አደረገ። በእርሷም በረከትን አደረገ። በውስጧም ምግቦችዋን (ካለፉት ሁለት ቀኖች ጋር) በአራት ቀናት ውሰጥ ለጠያቂዎች ትክክል ሲኾኑ ወሰነ።} {ከዚያም ወደ ሰማይ እርሷ ጭስ ኾና ሳለች አሰበ። ለእርሷም ለምድርም «ወዳችሁም ኾነ ወይም ጠልታችሁ ኑ» አላቸው። «ታዛዦች ኾነን መጣን» አሉ።} {በሁለት ቀኖችም ውስጥ ሰባት ሰማያት አደረጋቸው። በሰማይቱም ሁሉ ነገሯን አዘጋጀ። ቅርቢቱንም ሰማይ በመብራቶች አጌጥን። (ከሰይጣናት) መጠበቅንም ጠበቅናት። ይህ የአሸናፊው የዐዋቂው (ጌታ) ውሳኔ ነው።} {(ከእምነት) እንቢ «ቢሉም እንደ ዓድና ሰሙድ መቅሰፍት ብጤ የኾነን መቅሰፍት አስጠነቅቃችኋለሁ» በላቸው።} [ፉሲለት፡9_13]

ነገር ግን እነዚህ አንቀጾች እና ያ ጥሪ እውነትን ከመቀበል ይልቅ ትምክህታቸውንና ትዕቢታቸውን ብቻ ነው የጨመረላቸው። ከዛም አልፈው ወደ እስልምና ሀይማኖት የገባውን ሁሉ በተለይም የሚከላከልላቸው ወገን የሌላቸው ደካሞች የሆኑትን ሁሉ በብርቱ ማሰቃየቱን ተያያዙት። በዚህም አንዱን ሰሐባ ትልቅ ቋጥኝ በደረቱ ላይ እያስቀመጡበት፤ በዛ ከፍተኛ ሙቀት ባለው ሀገር በየገበያው እየጎተቱት ወይ በሙሐመድ ሃይማኖት ካድ አለበለዚያ ይህንን ስቃይ ወደህ ተቀበል ይሉታል። በዚህ የስቃይ ቅጣት ጥናት የሞተው እስኪሞት ድረስ ገፉበት።

የአላህ መልእክተኛን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) በተመለከተ በሚወዳቸውና ከለላ በሚያደርግላቸው አጎታቸው አቡ ጧሊብ ስር ነበሩ። አጎታቸው ባለግርማና ከቁረይሽ ከበርቴዎች አንዱ ቢሆንም ወደ እስልምና ግን አልገቡም።

ቁረይሾች የነቢዩን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ዳዕዋ ለማጉላላት የሞከሩ ሲሆን ገንዘብ፣ ንግስናና ሌሎች ፈተናዎችንም አቀረቡላቸውና በዚህም አንድ ነገርን ብቻ እንደ ቅድመ መስፈርት አቀረቡላቸው፤ ይኸውም ከአላህ ውጭ የሚያመልኳቸውን አማልክት ከማምለክ እንዲታቀቡ የሚያዝ የሆነውን "አዲሱ" ሃይማኖት የሚያደርጉትን ጥሪ እንዲያቆሙ የሚል ነበር። በዚህ ላይ የነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) አቋም ታዲያ ፍጹም ቁርጥ ያለ ፍንክች የማይል ነበር። ምክንያቱም ይህ አላህ ለሕዝቡ ያደርሱ ዘንድ የተሰጣቸው አምላካዊ መመርያ ነውና። ከዚህም መመርያ ፍንክች ቢሉ አላህ

ይቀጣቸዋልና። እኔኮ ለናንተው መልካምን (በጎን) የማስብ ሰው ነኝ፤ እናንተ ህዝብና ቤተሰቦቼ ናችሁ ነበር ያላቸው። "ወሏሂ! (እናንተ ቤተሰቦቼን) ህዝቡን ሁሉ እንኳ ብዋሽ እናንተን አልዋሻችሁም፤ ህዝቡን ሁሉ እንኳ ላታልለው ብል እናንተን አላታልላችሁም።"

ዳዕዋውን ለማስቆም በሚያደርጉት የማጉላላት ጥረት ምንም ዓይነት ድርድር ውስጥ የማያስገባ መሆኑን እንዳረጋገጡ ቁረይሾች ለመልዕክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እና ለተከታዮቻቸው ያላቸው ጥላቻም ባሰ። ቁረይሾች ነብዩ ሙሓመድን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ይገድሉ ዘንድ አቡ ጧሊብ አሳልፈው እንዲሰጧቸው ለዚህም በምትኩ የፈለጉትን እንደሚሰጧቸው ነገሯቸው፤ ይህን ካልቻሉ ደግሞ ቢያንስ ከመካከላቸው በሃይማኖቱ ወጣ ማለቱን እንዲያስቆሙላቸው፤ ነብዩን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ቢያንስ እንኳ ወደዚህ ሃይማኖት የሚያደርጉትን ዳዕዋ እንዲያስቆሙላቸው አቡ ጧሊብን ጠየቁ።

የአላህ መልዕክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ግን እንዲህ በማለት አፅንኦት ሰጥተው አቋማቸውን ሲገልፁ እንዲህ አሉ፦ "አጎቴ ሆይ! በአላህ ይሁንብኝ ይህንን የማደርገውን ጥሪ እንድተውላቸው ብለው ፀሐይን በቀኝ እጄ ጨረቃን ደግሞ በግራ እጄ ቢያስቀምጡ እንኳ እኔ ወይ አላህ እስልምናን የበላይ አድርጎ እስኪያንሰራፋው አለበለዚያም ደግሞ በዚሁ ጥሪየ ስር ሆኜ እስክሞት ድረስ ዳዕዋውን አልተወውም።" የዚህ ጊዜ አጎታቸውም እንዲህ አሏቸው፦ “እንግዲያውስ የፈለግከውን በል! በአላህ ይሁንብኝ ባንተ በኩል የመጣን ስፋለም ልሞት እችላለሁኝ እንጅ ማንም አይደርስብህም።” አቡ ጧሊብም ሞት አፋፍ ላይ በደረሱበት ጊዜ ከእርሱ ጋር የተወሰኑ ቁረይሾችም ሳሉ ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) መጡ ወደ እስልምና ይገባ ዘንድ እንዲህ እያሉ ይወተውቷቸው ጀመር፦ “አጎቴ ሆይ! ላ ኢላሃ ኢለሏህ ብለህ አላህ ዘንድ መሀርታውን የምለምንልህን ቃል ተናገርልኝ” አሏቸው፤ ቁረይሾችም በፊናቸው “ከዓብዱል ሙጦሊብ (ከአባቶችህና ከአያቶችህ ሃይማኖት) ልትወጣ ነው?!” ይሏቸዋል። የአባቶቹን ሃይማኖት ትቶ ወደ እስልምና ገብቶ መሞት ከባድ አድርጎ አዩትና ሙሽሪክ እንደሆኑ ሞቱ። ነብዩም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) አጎታቸው በሽርክ ላይ እንዳለ መሞቱ ውስጣቸው በሃዘን ተሞላ። የላቀው አላህም እንዲህ በማለት አሳወቃቸው፦ {አንተ የወደድከውን ሰው ፈጽሞ አታቀናም። ግን አላህ የሚሻውን ሰው ያቀናል እርሱም ቅኖቹን ዐዋቂ ነው።} [አልቀሶስ፡ 56]

ከአጎታቸው አቡ ጧሊብ ሞት በኋላ በነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ላይ የሚደርሰው ግፉ በረታ። በካዕባ ዙርያ ሲሰግዱ (የእንስሳት) ቆሻሻ አንስተው በላያቸው ላይ ያጥሉባቸው ነበር።

ከዚያም ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሕዝቦቿን ወደ እስልምና ጥሪ ሊያደርግላቸው ወደ ጧኢፍ ከተማ (ከመካ 70 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ የሚገኝ ከተማ) ሄዱ። የጧኢፍም ሕዝቦች ከመካ ሰዎች በባሰ ሁኔታ ዳዕዋውን የተጋፈጡ ሲሆን ነብዩን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) በሰፈር ዱርየ አስመቷቸው፤ ከጧኢፍም አባረሯቸው፤ ድንጋይ እየወረወሩም ክቡር ተረከዛቸውን እስኪያደሙ ድረስ ድብደቧቸው።

በዚህ ጊዜ ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ዱዓቸውን ወደ እርሱ በማድረግ እርዳታውንም በመማፀን ወደ አላህ ተቅጣጩ። አላህም መላኢካን ወደ እርሳቸው ላከላቸውና ‹‹ጌታህ ሕዝቦችህ ላንተ የሰጡህን ምላሽ ሰምቶአል፤ ስለዚህም ከፈለክ በሁለቱ እንጨቶች -ማለትም በሁለቱ ታላላቅ ተራሮች- ላጣብቃቸው›› አላቸው መላኢካው። እርሳቸውም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) በፍጹም “ይልቁን እኔ የምፈልገው አላህ ከዝርያቸው እርሱን በብቸኝነት የሚያመልኩትና በአምልኮውም የማያጋሩ ባሮችን እንዲያወጣ ነው።” በማለት መለሱለት።

ከዚያም የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ወደ መካ ተመለሱ። (ሙሽሪኮች) በእርሳቸው አማኝ ሆነው የተገኙ ህዝቦች ላይ ጥላቻና ግጭታቸውን ቀጠሉ። ከዚያም ከየሥሪብ -ከዚያ በኋላ መዲና ተብላ ከምትጠራው- ከተማ የሆኑ ጭፍራዎች ወደ መልዕክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ወደ እስልምና ጥሪ (ዳዕዋ) አድርገውላቸው እነርሱም ሙስሊሞች ሆኑ። ከባልደረቦቻቸውም መካከል አንዱ የሆነውን ሙስዓብ ቢን ዑመይር የተባለ ባልደረባቸውን የእስልምናን አስተምህሮት እንዲያስተምራቸው አብረው ላኩት። ከመዲና ሰዎች ብዙዎችም በእርሱ አማካኝነት እስልምናን ተቀበሉ።

በቀጣዩም ዓመት የእስልምናን ቃል ለመግባት ወደ ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) መጡ። ከዚያም በጭንቅ ላይ ያሉትን ባልደረቦቹን ወደ መዲና እንዲሰደዱ (ሂጅራ እንዲያደርጉ) አዘዙ። ባልደረቦቻቸውም በህብረትና በተናጠል እየሆኑ መሰደታቸውን ቀጠሉ። “ሙሃጂሮች” (ስደተኞች) የሚል ስያሜም ተሰጣቸው። የየስሪብ (መዲና) ከተማ ነዋሪዎችም በአክብሮት፣ በደስታና በመልካም ተቀበሏቸው። በቤታቸውም ውስጥ ጭምር ገንዘባቸውንና ቤታቸውንም አካፍለዋቸው ሙሃጂሮቹን ተቀበሏቸው። ከዚያም በኋላ “አንሷሮች” (ረዳቶች) የሚል ስያሜ ተሰጣቸው።

ከዚያም ቁረይሾች ይህንን የነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሂጅራ የማድረግ ውሳኔ በደረሱበት ጊዜ ነቢዩን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የሚያድሩበትን ቤት በመክበብ ልክ ከቤት እንደወጡ በአንድ የብርቱ ወንድ ሰይፍ ለመግደል ወሰኑ። ከዚህም ሴራቸው አላህ መልዕክተኛውን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ጠላቶቻቸው ባላሰቡበት መልኩ ነፃ አዳናቸው። አቡበከር አስ-ሲዲቅም እርሳቸውን ተከትለው ሲሄድ ዓሊይ (አላህ የሁለቱንም መልካም ሥራቸውን ይቀበላቸው) ደግሞ ነብዩ ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም ዘንድ የተቀመጡ የአደራ እቃዎች ለባለቤቶቻቸው ለመመለስ በመካ እንዲቆይ አዘዙት።

በሂጅራ ጉዟቸው ሳሉም ቁረይሾቹ ሙሐመድን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) በሕይወትም ይሁን ገድሎ ለሚያመጣላቸው ሽልማት እንዳዘጋጁ አወጁ። ይሁን እንጂ አላህ መልዕክተኛውን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ከባልደረባቸው ጋር በሰላም ወደ መዲና አደረሳቸው።

የመዲና ሰዎችም የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) በደስታ፣ በጥሩ አቀባበልና በእርካታ ተቀበሏቸው። ሁሉም የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ለመቀበል ከየጓዳቸው ወጥተው “የአላህ መልዕክተኛ መጡ... የአላህ መልዕከተኛ መጡ... ” እያሉ ወጡ።

ነብዩም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ማረፊያቸውን ካገኙ በኋላ። በመዲናም መስጊድ መገንባትን የመጀመርያ ስራቸው አደረጉ። ከዚያም ሰዎችን የእስልምና ሕግጋትን ማስተማር፣ ቁርአንን ማስቀራትና መልካም ሥነ ምግባርን በማስተማር

የእውቀት እንክብካቤ አደረጉላቸው። በዚህም ባልደረቦቻቸው ከእርሱ መመሪያውን ይማሩና ነፍሳቸውም ትጠራ እንዲሁም ስብእናቸው ከፍ ይልም ዘንድ በዙርያቸው ተሰባሰቡ። ለነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ያላቸው ፍቅር ጨመረ፤ በመልዕክተኛው ምጡቅ ስብእናም እጅግ ተማረኩ፤ በመካከላቸው ያለው የእምነት ወንድማማችነትም እጅጉን ተጠናከረ። መዲና በርግጥም በድሃና በሃብታም፣ በነጭና በጥቁር፣ በአረብም አረብ ባልሆነውም ነዋሪዎቿ መካከል ለአላህ ባላቸው ተቅዋ እና ኢማን ካልሆነ በቀር ምንም ልዩነት የሌለባት ፍፁም የበለፀገች ተምሳሌታዊ መዲና ሆነች። ከዚህ ማህበረሰብም ታሪክ በመቼውም ጊዜ ከሚያውቀው የትውልድ ሁሉ አይነታ የሆነው ትውልድ ተፈጠረ።
ከነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሂጅራ የአንድ ዓመት ቆይታ በኋላ በነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)ና ባልደረቦቻቸው እና የቁረይሽ ማህበረሰብንና አምሳዮቻቸው ከሆኑ የእስልምና ጠላቶች መካከል ግጭትና ፍልሚያ ተጀመረ።
በዚህ ጊዜ የመጀመርያው ታላቁ የበድር ጦርነት በመካና በመዲና መካከል በሚገኝ ሸለቆ ውስጥ ተካሄደ። አላህም በሙስሊሞች በኩል የነበሩትን ብዛታቸው 314 የሆኑ ተዋጊዎች በቁረይሽ በኩል የነበሩትን ብዛታቸው 1,000 በሆኑት ጠላቶች ላይ አበረታቸው። በዚህም ሙስሊሞቹ ከአላህ በሆነ ታላቅ እርዳታ ከቁረይሾች 70 ታላላቆቻቸው ገድለው፤ 70ዎቹንም ማርከው የተቀሩት ሸሽተው የሂዱበትን ድል ተቀዳጁ።
ከዚያም በነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እና በቁረይሾች መካከል ሌሎች ፍልሚያዎችም ተካሄዱ። በመጨረሻም ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) መካን (ለቀው ከወጡበት ስምንተኛው አመት በኋላ) ወደ ቁረይሾች ላይ ለመዝመት፣ በየጓሮዋ ገብተው በእነርሱ ላይ የማያዳግም ድልን ለመቀዳጀት፣ እርሱንም ለመግደል የሞከረችውን፣ ባልደረቦቹም ያሰቃየችውን፣ ከአላህ ይዞት የመጣውንም ሃይማኖት ከማሰራጨት ያገተችውን መንደር ለመውረር ወደ እስልምና ሃይማኖት የገቡ 10,000 ሰራዊቶችን አስከትለው ወደ ተከበረችዋ መካ ዘመቱ።
ከዚያም ከዚህ እጅግ የታወቀ ድል በኋላ ሰበሰቧቸውና እንዲህ አሏቸው፦ "እናንተ የቁረይሽ ስብስቦች ሆይ! ምን ያደርገናል ብላችሁ ትገምታላችሁ?” በማለት ሲጠይቋቸው ቁረይሾቹም እንዲህ በማለት መለሱ “ቸር ወንድማችን ነህ፤ የቸር ወንድማችን ልጅም ነህ።” የዛኔ የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) “እንግዲያውስ ሂዱ እናንተ ነፃ ናችሁ!” አሏቸውና ይቅር ብለዋቸው የእስልምና ሃይማኖት የመቀበል ነፃነትን ሰጧቸው።
ይህም ሰዎች ወደ እስልምና ሃይማኖት በገፍ እንዲገቡ ምክንያት ሆነ። መላው ዓረብም በቡድን እየሆኑ ሰለሙ ወደ እስልምና ሃይማኖትም ተቀላቀሉ።
ከዚያም ብዙም ሳይቆይ ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ወደ እስልምና ሃይማኖት በቅርቡ የገቡ 114,000 ሰዎችን ይዘው አብረው ሐጅ አደረጉ።
በመሆኑም በዚህ ታላቁ የሓጅ ቀን የሃይማኖቱ ህግጋትንና የእስልምናን መመርያ ሊያብራሩላቸው ተነስተው ኹጥባ (ዲስኩር) ሲያደርጉ እንዲህም አሉ፦ “ምናልባት ከዚህ አመት በኋላ በመካከላችሁ ላልገኝ እችላለሁ፣ ነገር ግን አብሮኝ የነበረው አብሮኝ ላልነበረው (ሩቅ ላለው) ያድርስ” አሉና መለስ ብለው ህዝባቸውን በመመልከት እንዲህ አሉ፦ “ተልእኮየን አድርሻለሁኝን?!” አሉ፤ ባልደረቦቻቸውም “አዎ” ሲሏቸው የዚህኔ እሳቸውም መልሰው “አላህ ሆይ ምስክር ሁነኝ!” በማለት በድጋሚ “ተልእኮየን አድርሻለሁኝን?!” ብለው ጠይቁ፤ ባልደረቦቻቸውም ደግመው “አዎ” ሲሏቸው የዚህኔ እሳቸውም በድጋሚ “አላህ ሆይ ምስክር ሁነኝ!” አሉ።
ከዚያም ረሱል (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ከሐጅ በኋላ ወደ መዲና ተመለሱ። እናም አንድ ቀን ኹጥባ (ዲስኩር) ሲያደርጉ እንዲህ አሉ፦ “አንድ ባሪያ አምላኩ በዚህ ዓለም መዘውተር ወይስ አላህ ዘንድ ያለው ይሻለው እንደሁ ምርጫ ሰጠው፤ ያ ባርያም አላህ ዘንድ ያለውን መረጠ።” በዚህም ባልደረቦቻቸው ያ ባርያ ተብሎ የተገለፀው ራሳቸውን ለመግለፅ እንደፈለጉበትና ከዚህች አለም ህይወት ወደ አኺራ የሚሸጋገሩበት ጊዜውም እንደደረሰ የተረዱት ተረዱና ያለቀሰውም አለቀሰ። እናም በአስራ አንደኛው አመተ ሂጅራ በሶስተኛው ወር ውስጥ ባለው ሁለተኛው እለተ ሰኞ በነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ላይ ህመም ጠናባቸው። ጣእረ ሞትም ድቅን ባለባቸው ጊዜ የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ወደ ባልደረቦቻቸውን የተሰናባች እይታን እያይዋቸው ሶላታቸው ላይም እንዲጠባበቁ በአደራ አሳሰቧቸው። ክቡር ነፍሳቸውም አረፈችና ወደ ረፊቁል አዕላ (መልዕክተኞች፣ ነብያቶችና ደጋግ የአላህ ባሮች ወዳሉት) በሞት ተሸጋገሩ።
ሶሓቦች (አላህ መልካም ሥራቸውን ለሁሉ ይውደድላቸው) በነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሞት ተደናገጡ፤ ህዘንና ትካዜያቸውም ጥግ ደረሰ፤ የመርዶው ተፅዕኖም ከእነሱ መካከል አንዱ ማለትም ዑመር ኢብኑል ኸጧብ በድንጋጤ ሰይፉን መዞ በማውጣት ማንም ሰው ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሞተዋል ሲል ብሰማው በዚህ ሰይፍ አንገቱ ነው የምቀነጥስለት እስከማለት አደረሰው።
የዚህ ጊዜ አቡበከር አስ-ሲዲቅ ተከታዩን የኋያሉ አላህን ቃል በማውሳት ገሰፀው፦ {ሙሐመድም ከበፊቱ መልክተኞች በእርግጥ ያለፉ የኾነ መልክተኛ እንጅ ሌላ አይደለም። ታዲያ ቢሞት ወይም ቢገደል ወደ ኋላችሁ ትገለበጣላችሁን ወደኋላው የሚገለበጥም ሰው አላህን ምንም አይጎዳም። አላህም አመስጋኞቹን በእርግጥ ይመነዳል።} [አሊ-ዒምራን 144] ዑመር ኢብኑል ኸጧብም ልክ የዚህን አንቀፅ እንደሰሙ ራሳቸውን ስተው ውደቁ፦
እኚህ ናቸው እንግዲህ የነብያቶችም የመልዕክተኞችም መደምደሚያ፣ ወደ መላው የሰው ልጅ አብሳሪና አስጠንቃቂ ተደርገው የተላኩት የአላህ መልዕክተኛ ሙሓመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)። ተልእኳቸውን አደረሱ፤ አደራቸውንም ተወጡ፤ ህዝቡንም በሚገባ መከሩ።
አላህም በተከበረውና ከሰማይ በወረደው የአላህ ቃል በሆነው ቁርኣን አጠነከራቸው፤ ያ... {ከኋላውም ከፊቱም ውሸት አይመጣበትም። ጥበበኛ ምስጉን ከኾነው ጌታ የተወረደ ው።} [ፉሲለት፡ 42] ያ መላ የሰው ልጆች ከፍጥረተ ዓለሙ መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ፍፃሜ ድረስ ያሉት ሰዎች ሁሉ ቢሰበሰቡና አምሳያውንም እንዲያመጡ ቢጠየቁ ከፊሉ ለሌላኛው ረዳት ሆነው እንኳ ብጤውን የማያመጡለት በሆነው ቁርአን አበረታቸው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {እናንተ ሰዎች ሆይ! የፈጠራችሁን እነዚያንም ከናንተ በፊት የነበሩትን (የፈጠረውን) ጌታችሁን ተገዙ፤ (ቅጣትን) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና።} {(እርሱ) ያ ለናንተ ምድርን ምንጣፍ ሰማይንም ጣራ ያደረገ ነው፤ ከሰማይም (ከደመና) ውሃን ያወረደ በርሱም ከፍሬዎች ለናንተ ሲሳይን ያወጣ ነው።

እናንተም (ፈጣሪነቱን) የምታውቁ ስትኾኑ ለአላህ ባላንጣዎችን አታድርጉ።} {በባሪያችንም ላይ ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትኾኑ ከብጤው አንዲትን ምዕራፍ አምጡ። እውነተኞችም እንደኾናችሁ ከአላህ ሌላ መስካሪዎቻችሁን ጥሩ።} {(ይህንን) ባትሠሩ ፈጽሞም አትሠሩትምና ያችን መቀጣጠያዋ ሰዎችና ድንጋዮች የኾነችውን እሳት ተጠበቁ፤ ለከሓዲዎች ተደግሳለች።} {እነዚያን ያመኑትንና መልካሞችንም የሠሩትን ለነርሱ ከሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው ገነቶች ያሏቸው መኾኑን አብስራቸው። ከርሷ ከፍሬ (ዓይነት) ሲሳይን በተመገቡ ቁጥር (ፍሬዎችዋ ስለሚመሳሰሉ) «ይህ ያ ከአሁን በፊት የተገመብነው ነው» ይላሉ። እርሱንም ተመሳሳይ ኾኖ ተሰጡት። ለነሱም በውስጧ ንጹህ የተደረጉ ሚስቶች አሏቸው። እነሱም በውስጧ ዘውታሪዎች ናቸው።} [አል-በቀራህ 21-25]

ይህ ቁርኣን ከ114 ምዕራፎች (ሱራዎች) እና ከ6,000 በላይ በሆኑ አንቀጾች የተዋቀረ ነው። አላህ ለዘመናት የሰው ልጆችን ሁሉ የቁርኣን ምዕራፎችን (ሱራዎችን) የመሰለ አንድ ምዕራፍ (ሱራ) እንኳ ማምጣት ይችሉ እንደሁ ይገዳደራቸዋል። በቁርኣን ውስጥ ካሉት ምዕራፎች አጭር የሚባለው ሱራ ሦስት አንቀጾችን ብቻ የያዘ ነው።

ይህን ማድረግ ከተሳናቸው ይህ ቁርኣን ከአላህ ዘንድ መሆኑን ማወቅ አለባቸው። ይህ ታዲያ አላህ ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ካጠነከረባቸው ታላላቅ ተአምራት መካከል አንዱ ነው። ያው አላህ በሌሎች ድንቅ ተአምራትም እንደደገፋቸው ሁሉ ማለት ነው። ከነዚህም መካከል፦

## ረ- ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ካጠናከረባቸው ተአምራት መካከል፦

1- ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) አላህን ተማፅነው እጃቸውን በአንዳች እቃ ላይ ያሳርፉና ውኃውም ከጣቶቻቸው ፈልቆ ይወጣል፤ ቁጥራቸው ከሺህ የሚበልጥ ሰራዊቶችም ከውሃው ይጠጡ ነበር።

2. ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) አላህን ተማፅነው እጃቸውን በምግብ ማእድ ላይ ያሳርፉትና ይበረክታል፤ ቁጥራቸው ከ1500 የሚበልጥ ባልደረቦቻቸውም ከምግቡ ይበሉ ነበር።

3. ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) አላህ ዝናብ እንዲያወርድላቸው በመማፀን እጃቸውን ወደ ላይ ከፍ ያደርጋሉ፤ ገና ዱዓእ ያደረጉበትን ቦታቸውንም ሳይለቁ የዝናቡ ጠብታ በሚያምር ክቡር ፊታቸው ላይ ኮለል እያለ ሲወርድ ይታይ ነበር። እንዲሁም ሌሎች በርካታ ተአምራቶችም ተሰጥቷቸዋል።

አላህ እርሳቸውንም ሊገድልና ከአላህ ዘንድ የወረደውን ይዘውት የመጡትን ብርሃን ለማጥፋት ከተነሳ ጠላት በሚያደርግላቸው ጥበቃም አጠናክሯቸዋል። ልክ የላቀው አላህ እንዲህ እንዳለን፦ {አንተ መልክተኛ ሆይ! ከጌታህ ወዳንተ የተወረደውን አድርስ። ባትሠራም መልክቱን አላደረስክም። አላህም ከሰዎች ይጠብቅሃል። አላህ ከሓዲዎችን ሕዝቦች አያቀናምና።} [አል-ማኢዳህ: 67]

የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) - ከአላህም ድጋፍ ጋር - በተግባራቸውም ይሁን በአነጋገራቸው ሁሉ መልካም አርአያ ነበሩ። ከአላህ ዘንድ የወረደላቸውም ትእዛዝ በመፈፀም ረገድ ግንባር ቀደም ነበሩ። አምልኮና ታዛዥነትም ላይ ከሰው ሁሉ በላይ ጉጉት የነበራቸው ሲሆን ከሰዎችም ሁሉ የበለጠ ለጋስ ነበሩ። በእጃቸውም ላይ ምንም ነገር ሳያስቀሩ እንዳለ በአላህ መንገድ ላይ ለችግረኞች፣ ለድሆችና ለምስኪኖች ከመስጠት በቀር ርስት እንኳን አላስቀሩም ነበር። ለባልደረቦቻቸው እንዲህ ብለዋቸዋል፦ "እኛ የነብያት ማህበረሰቦች ቁሳዊ ውርስ አንተውም። ከነብረታችን የቀረ ነገር ቢኖር እንኳ ምፅዋት ነው።"(2)

በስነ ምግባርም በኩል ማንም አይደርስባቸውም ነበር። የትኛውም ሰው ሲቀርባቸው ከጥልቅ ልቡ (እጅግ በጣም) ነው የሚወዳቸው፤ ብሎም መልዕክተኛውን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ከልጁ፣ ከአባቱና ከሰው ልጆችም ሁሉ አብልጦ ነው የሚወዳቸው።

የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሲያገለግላቸው የነበረው አነስ ኢብኑ ማሊክ (አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸው) እንዲህ ይላል፦ "ከአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) መዳፍ የተሻለ ወይም የለሰለሰ ወይም ይበልጥ የሚያውድ መዳፍ ነክቼ አላውቅም። ለአስር አመታት ያክል አገልግያቸዋለሁ ስላደረግኩትም ነገር ለምን አደረግከው ስላደረግኩት ነገርም ለምን አላደረግከም ብለውኝ አያውቁም።"[1]

እኚህ ናቸው የአላህ መልዕክተኛ ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ያ የላቀው አላህ ደረጃቸውን በአለማቱ ሁሉ ከፍ ያደረገላቸው፤ ማንኛውም ሰው ድሮም ዘንድሮም የእርሳቸውን ያክል ስሙ የተወሳ የለም። ከ ሺህ አራት መቶ አመታት በፊት ጀምሮ በአለም የሚገኙ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አዛን አድራጊዎች በየቀኑ አምስት ጊዜ "አሽሀዱ አነ ሙሓመደን ረሱሉሏህ" በማለት ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን ሲመሰክሩ እናም በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ምዕመናንም በየለቱ በሶላታቸው ቢያንስ በአስራዎቹ ለሚቆጠሩ ጊዜያት ያክል ደጋግመው "አሽሀዱ አነ ሙሓመደን ረሱሉሏህ" ይላሉ።

## ሰ- የተከበሩት ሶሓቦች (የነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ባልደረቦች)

ከመልዕክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ህልፈት በኋላ የተከበሩት ሶሓባዎች የእስልምናን ጥሪ ኃላፊነት ተሸክመው ወደ ምድሪቱ ምሥራቅና ምእራብ በመጓዝ ዳዕዋ አደረጉ፤ እነርሱ በርግጥም የሃይማኖቱ ትክክለኛ ተጣሪዎች ነበሩ፤ ምክንያቱም ከማንኛውም ሰው በላይ እውነት ተናጋሪዎች፣ ይበልጥ ፍትሃዊ፣ ይበልጥ አደራን ጠባቂዎችና ለሰዎችም መልካምን ነገር በማካፈልም ይሁን ለሰዎች ቀናነት ይበልጥ ጉጉት የነበራቸው ሰዎች ነበሩና።

በነብያት ስነምግባር የተኮተኮቱ፤ የነብያቶችንም ኮቴ የሚከተሉ ነበሩ። ይህ ውብ ስነ ምግባራቸውም የምድሪቱ ማህበረሰቦች ዘንድ ይህንን ሀይማኖት እንዲቀበሉ የጎላ ተጽእኖ አሳድሯል። በመሆኑም ሰዎች ይህንን ሃይማኖት ከመውደድ አኳያ ያለምንም ማስገደድና አሸናፊና ተሸናፊነት ከምዕራቡ አፍሪካ እስከ ምስራቁ ኢስያ እስከ መካከለኛው አውሮፓ ክፍል ድረስ በቡድን በቡድን እየሆኑ ወደ አላህ ሃይማኖት ተከታትለው ገብተዋል።

[1] አል-ቡኻሪ ዘግበውታል (4/230)

እነርሱ የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ባልደረቦች፤ ከነብያት በኋላ ከሰዎችም ሁሉ በላጭ የሆኑት ናቸው። ከእነሱ መካከል እጅግ ዝነኛ የሆኑት ከመልዕክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ህልፈት በኋላ ኢስላማዊውን ሀገራትን ሲያስተዳድሩ የነበሩት አራቱ ቅን ከሊፋዎች (ምትኮች) ናቸው። እነርሱም፦

1- አቡበከር አስሲዲቅ
2- ዑመር ኢብኑል ኸጧብ
3- ዑሥማን ኢብኑ ዓፋን
4- ዐሊይ ኢብኑ አቢ ጧሊብ

ሙስሊሞች ሰሓቦችን አስመልክቶ ታላቅ እውቅናና አድናቆት ነው የሚሰማቸው። መልዕክተኛውን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እና የመልዕክተኛውን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ወንድ እና ሴት ባልደረቦችን በመውደድ፣ በማላቅ፣ የሚገባቸውንም ደረጃ በመስጠት ወደ ኃያሉ አላህም ይቃረባሉ።

ሙስሊም ነኝ ብሎ ቢሞግት እንኳ በእስልምና ሃይማኖት ያስተባበለ ከሀዲ ካልሆነ በቀር ሰሓቦችን የሚጠላና የሚያነውር የለም። የላቀው አላህ እንዲህ ሲል አሞግሷቸዋልና፦ {ለሰዎች ከተገለጸች ሕዝብ ሁሉ በላጭ ሆናችሁ በጽድቅ ነገር ታዛላችሁ፤ ከመጥፎም ነገር ታዛላችሁ፤ በአላህም (አንድነት) ታምናላችሁ።} [አሊ-ዒምራን 110] ለመልእክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ቃልኪዳን በገቡ ጊዜ አላህ ወዶ እንደተቀበለላቸው ጥራት ይገባውና እንዲህ በማለት አረጋገጠ፦ {ከምእምናኖቹ በዛፊቱ ሥር ቃል ኪዳን በሚጋቡህ ጊዜ አላህ በእርግጥ ወደደ። በልቦቻቸውም ውስጥ ያለውን ዐወቀ። በእነርሱም ላይ እርጋታን አወረደ። ቅርብ የኾነንም መከፊት መነዳቸው።} [አል_ፈትሕ፡ 18]

# 4- የእስልምና ምሰሶዎች (ማዕዘናት)

እስልምና እያንዳንዱ ሙስሊም ሙስሊም ለመባል ሊከተላቸው የሚገቡ አምስት ዋና ዋና ማዕዘናት አሉት፦

## የመጀመሪያው ማዕዘን፦ ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ አለመኖሩን እና ሙሐመድም የአላህ መልዕክተኛ ናቸው ብሎ መመስከር።

ይህች ወደ እስልምና ሀይማኖት የሚገባ ሰው ከፍ ብለን በገለፅነው መልኩ በሙሉ መልእክቷ በማመን እንዲህ በማለት የሚናገራት የመጀመርያ ቃሉ ነች፦ “አሽሃዱ አን ላ ኢላሃ ኢለሏህ ወአሽሃዱ አነ ሙሓመደን ዓብዱሏሂ ወረሱሉህ” (ትርጉሙም: ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፤ ሙሐመድም የአላህ ባሪያውና መልእክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለሁ ማለት ነው።)

አላህ አንድና ብቸኛ አምላክ፤ ያልወለደ ያልተወለደ መሆኑን፤ ለእርሱ ብጤ እንደሌለው ፤ እርሱ የሁሉም ፈጣሪ ሲሆን ከእርሱም ውጭ ያሉ ሁሉ ፍጡር እንደሆኑ እና እርሱ ብቻ ሊመለክ የሚገባው አምላክ እንደሆነ ያምናሉ። በመሆኑም ከአላህም ውጭ አምላክ ከእርሱም ውጭ ጌታ የለም። ሙሐመድም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ከሰማይ መለኮታዊ ራእይ የሚደርሳቸው (ወሕይ የሚወርድላቸው) አምላክ ትእዛዙንና ክልከላውን የሚያስተላልፍላቸው የአላህ ባርያና መልእክተኛ መሆናቸውንም ያምናሉ። ስለዚህም የተናገሩትን ማመን፣ ያዘዙትን መታዘዝ፣ የከለከሉትንና ያስጠነቀቁትን መራቅ ከእያንዳንዱ ሙስሊም የሚጠበቅ ግዴታ ነው።

## ሁለተኛው ማዕዘን፡ ሰላትን በአግባቡ መስገድ

በሶላት ዋነኛ የባርያነት እና የአምልኮ መገለጫዎች ለኃያሉ አላህ ብቻ ተለይተው ይኀላሉ። በዚህም አንድ የአላህ አገልጋይ ባሪያ ራሱን ዝቅ አድርጎ ቆሞ የቁርኣን አንቀጾችን እያነበበ አላህንም በሁሉም አይነት ዚክርና ውዳሴ እያወሳ፤ እያጎበደደና በግንባሩም እየተደፋ እየሰገደ ጌታውን አላህን ያዋያል፤ ይማፀነዋልም ከታላቅ ችሮታውም ይለምነዋል። በመሆኑም ሶላት ማለት በባሪያውና በፈጠረው፣ ግልጽንም፣ ሚስጥራዊውንም ተጨባጩን ብሎም በሰጋጆች መካከል ያለውን መገለባበጥም ከሚያውቅለት ጌታው ጋር ያለ ቁርኝት ነው። ሶላት አላህ ባርያውን እንዲወደው፣ ወደ እርሱም እንዲቀርብ፣ ወዶም እንዲቀበልለት ታላቋ ሰበብ ነች። ለአላህ ከመገዛት ተንጠባርሮ ሶላትን በእብሪተኝነት የተወ ሰው አላህ ተቆጥቶበትና ረግሞት ከእስልምና ይወጣል።

መቆምንና ሱረቱል ፋቲሓን መቅራትን (ማንበብ) አጠቃልሎ በቀን አምስት ሶላቶችን መስገድ ግዴታ ነው። «ቢስሚልላሂ-ር-ሯሕማኒ-ር-ሯሒም» [ትርጉሙም: በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው] (1) «አልሓምዱ ሊልላሂ ረቢል ዓለሚን» (ትርጉሙም: ምስጋና ለዓለማት ጌታ ለአላህ የተገባው ነው) (2) «አር-ሯሕማኒ-ር-ሯሒም» (ትርጉሙም: እጅግ በጣም አዛኝ አዛኝ እጅግ በጣም ሩኅሩህ) (3) «ማሊኪ የውሚ-ድ-ዲን» (ትርጉሙም: የፍርዱ ቀን ባለቤት) (4) «ኢይያከ ነዕቡዱ ወኢይያከ ነሰተዒን» (አንተን ብቻ እንገዛለን አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምንሃለን) (5) «ኢህዲና-ስ-ሲሯጦል ሙስተቂም» (ትርጉሙም: ቀጥተኛውን መንገድ ምራን) (6) «ሲሯጦ-ል-ለዚነ አንዓምተ ዓለይሂም ቐይሪል መቕዱቢ ዓለይሂም ወለድዷሊን» (ትርጉሙም: የእነዚያ ፀጋህን የዋልክላቸውን ሰዎች መንገድ በነዚያ የተቆጣህባቸውን እና የተሳሳቱትንም አይደሉም።) (7) [አል_ፋቲሓ፡ 1_7] እንዲሁም የተወሰነ የቁርአን አንቀፆችን ማንበብ፤ ሩኩዕ (ማጎብደድ)፣ ሱጁድ (በግንባር መደፋት)፣ አላህን መማፀንና “አሏሁ አክበር” ብሎ አላህን ማላቅ፣ ሩኩዕ ላይ “ሱብሓነ ረቢየል ዓዚም” በማለት ሱጁድ ላይ ደግሞ “ሱብሓነ ረቢየል አዕላ” በማለት አላህን ማጥራትንም አካትታለች።

ሰጋጅ ሶላትን ከማከናወኑ በፊት አስቀድሞ አካሉም ልብሱም ይሁን የሚሰግድበት ቦታ ሁሉ ከነጃሳ (ሽንትና ሰገራ መሰል) መፅዳት፤ ፊቱንና ሁለት እጆቹን በማጠብ፣ ራሱ ላይ በማበስና ከዚያም ሁለት እግሮቹንም በማጠብ በውኃ ውዱእ ማድረግ አለበት።
(በባልና ሚስት ግብረ ስጋ ግንኙነት) ጀናባ ሆኖ ከነበረ ደግሞ መላ ሰውነቱን በመታጠብ መፀዳዳት አለበት።

## ሐ- ሶስተኛው ማእዘን: ዘካ

ለድሆች እና ለሚስኪኖች እንዲሁም ሌሎች ለሚገባቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ተሰጥተው ችግራቸውን ያቃልሉበት ዘንድ አላህ በሃብታሞች ላይ የደነገገው የተወሰነ የገንዘብ መጠን ነው። የገንዘቡ መጠን ከአጠቃላይ ሀብቱ ሁለት ነጥብ አምስት (2.5%) ከመቶ ነው። የሚሰጠውም ለሚገባቸው ሰዎች ነው።

ይህ ምሰሶ በህብረተሰቡ መካከል ፍቅር፣ መግባባት እና መተጋገዝን በመጨመር ገንዘብበ የሌላቸው ሰዎች ተመቻችተው በሚኖሩ ሃብታሙ የህብረተሰብ ክፍል ላይ ከሚያሳድሩት ምቀኝነትና ቂምም በመታደግ ማህበራዊ ትብብርን የሚያሰራጭ ነው። ለኢኮኖሚ እድገት እና ብልጽግና እንዲሁም ገንዘብን በተስተካከለ አኳኃን ዝውውር እንዲኖረውና ወደ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ተደራሽ ይሆን ዘንድ አይነተኛው ምክንያት ነው። ይህ ዘካ በየትኛውም የገንዘብ አይነት ማለትም በብር፣ በእንስሳ፣ በአዝርእትና ፍራፍሬ እንዲሁም በገበያ ሸቀጦችም ላይ ሁሉ እንደየ አይነቱ በተለያየ መጠን ግዴታ ነው።

## መ- አራተኛው ማእዘን: የረመዷንን ወር መፆም

ፆም: ከፀሃይ መውጣት ጀምሮ ፀሓይ እስከምትጠልቅበት ጊዜ ድረስ አላህን ለመገዛት በማሰብ ከምግብ፣ ከመጠጥና ከግብረስጋ ግንኙነት መታቀብ ነው።

አላህ እንዲፆም ያዘዘበት ወር የሆነው ወርሀ ረመዷን በጨረቃ ተኮር የጊዜ አቆጣጠር (በሂጅሪ) ዘጠነኛው ወር ነው። ይህ ወር ማለት አላህ በመልዕክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ላይ ቁርአኑን ማውረድ የጀመረበት ወር ነው።

የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {(እንድትጾሙ የተጻፈባችሁ) ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ ከቅን መንገድና (እውነትን ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች (አንቀጾች) ሲኾን ቁርኣን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው። ከእናንተም ወሩን ያገኘ ሰው ይጹመው።} [አል-በቀራህ: 185] ፆም ከሚያስገኛቸው ታላላቅ ፋይዳዎች መካከል ትዕግስትን መለማመድ እንዲሁም ተቅዋን (አላህን መፍራትን) እና የልብ እምነትን ማጠናከር ይገኝበታል። ምክንያቱም ጾም በአላህና በባርያው መካከል ያለ ምስጢራዊ ቁርኝት እንደመሆኑ መጠን ማንም ሰው ሳያውቅበት ከሰዎች ተደብቆ መብላትና መጠጣት እንደሚችል እያወቀ አላህን ለመገዛትና ትእዛዙንም ከመፈፀም አኳያ መታቀቡ ለአላህ ያለው ተቅዋ (ፍራቻ) እና እምነቱን እንዲጨምር ምክንያት ይሆንለታል። ስለዚህም ነው ፆመኞች አላህ ዘንድ ያላቸው ምንዳም ከፍ ከማለቱ በተጨማሪ በጀነት ውስጥ አር-ረያን የሚባል ልዩ በር የተመደበላቸው። በተጨማሪም የትኛውም ሙስሊም በራሱ ፈቃድ ከወርሀ ረመዷን ውጭ በማንኛውም ወር የዓመቱን ቀናት የዒድ አል-ፈጥርንና ዒድ አል-አድሐን ሲቀር ሊፆም ይችላል።

## ሠ - አምስተኛው ማዕዘን፡- ወደ ተቀደሰው ቤት ሐጅ ማድረግ

ሐጅ ማድረግ የሚችል የትኛውም ሙስሊም በህይወት ዘመኑ አንድ ጊዜ የመፈፀም ግዴታ ያለበት ሲሆን ከዛ በላይ የሚጨምር ከሆነ ደግሞ በውዴታው ነው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ "ለአላህም በሰዎች ላይ ወደርሱ መሄድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ አለባቸው።" [አሊ-ዒምራን 97] ሓጅ በሚደረግባቸው ማለትም በሂጅሪ አቆጣጠር የመጨረሻዎቹ ወራት ሙስሊሙ በተከበረችዋ መካ ወደሚገኙ ልዩ የአምልኮ ቦታዎች የሚጓዝ ሲሆን ሙስሊሙ መካ ከመግባቱ በፊት ልብሶቹን አወላልቆ የኢሕራም ልብሱን ይለብሳል። ይህም እነዚያን በሞተ ጊዜ የሚለብሳቸውን ሁለት ነጫጭ ከፈኖች የሚጠቁም አንድምታ አላቸው።

ከዚያም የተለያዩ የሐጅ ሥራዎችን ማለትም በተከበረው ካዕባ ዙርያ ጠዋፍ ማድረግ፣ በሰፋ እና መርዋ መካከል መሮጥ፣ በአረፋ ሜዳ ላይ መቆም፣ በሙዝደሊፋ ማደር፣ ወዘተ ያከናውናል።

ሐጅ በምድር ላይ ካሉ የሙስሊሞች ስብስብ ትልቁ ሲሆን በመካከላቸውም ወንድማማችነት፣ መተዛዘንና መመካከርን ያሰፍናል። አለባበሳቸው አንድ አይነት፤ የአምልኮ ስርአታቸውም አንድ አይነት ነው። አንዳቸውም ከሌላው ለአላህ ካላቸው ፍራቻ (ተቅዋ) ካልሆነ በቀር አይበላለጡም። የሐጅ ስርአት ምንዳው ታላቅ ነው። ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡- (ያለ ጾያፍ ድርጊትና ያለ አመፅ ሐጅ ያደረገ ልክ እናቱ እንደወለደችው ቀን ከኃጢአቱ ይጠራል።)[2]

# 5- የእምነት ማዕዛናት

የእስልምና ማዕዘናት ሙስሊሙ የሚላበሳቸው ውጫዊ መገለጫዎች መሆናቸውን እና እነርሱን መተግበሩም የእስልምናን ሃይማኖት መቀበሉን የሚያመለክቱ እውነታዎች መሆናቸው ካወቅን ዘንዳ ሙስሊሙ የእስልምናው ትክክለኝነት እውን ሊሆን ዘንድ ልቡ ውስጥ ሊያምንባቸው የሚገቡ “አርካኑል ኢማን” የሚባሉ ማዕዘናትም አሉ። እነኝህ ማዕዘናት ይዘታቸው በሙስሊሙ ልቦና ውስጥ በጨመሩና በተሟሉ ቁጥር በኢማን ያለውም ደረጃም እየላቀ በአላህ ሙእሚን ባርያዎች ውስጥ ለመጠቃለል ይበልጥ የተገባ እየሆነ ይሄዳል። ይህች (የሙእሚኖች) ደረጃ ታዲያ ከሙስሊሞች ደረጃ ከፍ ያለች ነች፤ ምክንያቱም የሙእሚንነት ደረጃ የደረሰ ሁሉ ሙስሊም ነውና፤ ሙስሊም የሆነ ሁሉ ግን የሙእሚንነት ደረጃ ላይ ደርሷል ማለት አይደለም።

በእርግጥ በመሰረታዊነት የኢማን መሰረቱ አለው፤ ነገር ግን በተሟላ መልኩ ላይሆን ይችላል።

የእምነት ማዕዘናት ስድስት ናቸው:

(በአላህ፣ በመላዕክቱ፣ በመጻሕፍቱ፣ በመልክተኞቹ፣ በመጨረሻው ቀን ማመን እና በቀደር መልካምም ሆነ መጥፎ በሆነ (የአላህ ቅድመ ውሳኔ) ማመን ነው)።

የመጀመሪያው ማዕዘን፡- በአላህም ልታምን እና ልቦናህም አላህን በመውደድ፣ እርሱንም በማላቅ፣ እርሱ ዘንድም ራስህን የተዋረድክ መሆንህንና ተሸናፊነትህንም ልታጎላ፣ ለእርሱም ትእዛዛት ያለምንም ተጋሪ ታዛዥ በመሆን ልቦናህን ልትሞላ እንዲሁም እርሱን በመፍራትና እርሱም ዘንድ ያለውን በመከጀል ልቦናህ የተሞላ ሊሆን እንደሚገባው ሁሉ ማለት ነው። በዚህ ሁኔታም አላህን ከሚፈሩትና የእርሱን ቀና ጎዳና ከሚጓዙት የአላህ ባርያዎች ይሆናል።

ሁለተኛው ማዕዘን፡- በመላእክት ማመን ሲሆን እነርሱም ከብርሃን የተፈጠሩ የአላህ ባሮች መሆናቸውን፤ ከአላህ በቀር ቁጥራቸው ያማያውቅ፣ በሰማይና በምድር ያሉ ተቆጥረው የማይዘለቁ፤ አላህን በማምለክ፣ በማወደስና ከማይገባው በማጥራት (ተስቢሕ በማድረግ) ማንነት ተደርገው እንደተፈጠሩና ሌትም ቀንም ሳይሰለቹ እርሱን ተስቢሕ የሚያደርጉ መሆናቸውን ማመን ነው። {አላህን ያዘዛቸውን ነገር (በመጣስ) አያምጹም። የሚታዘዙትንም ሁሉ ይሠራሉ።} [ተሕሪም፡ 6] ለእያንዳንዳቸው አላህ በእርሱ ላይ ግዴታ ያደረገበት ኃላፊነት አለባቸው። ከእነርሱም መካከል ዓርሽን ተሸካሚዎች አሉ፤ ከነርሱም ነፍስን የማውጣት ኃላፊነት የተጣለበት አለ፤ ከእነርሱም ከሰማይ የተወረደን ወሕይ (መለኮታዊ ራእይ) ይዞ የመውረድ ኃላፊነት ያለበት አለ ይህውም ጂብሪል

---

[2] ሐዲሡን አል-ቡኻሪ (2/164) ኪታቡል ሐጅ: ፈድሉ አልሓጀል መብሩር በሚለው ባብ ስር ዘግበውታል።

(የአላህ ሰላም በእርሱ ላይ ይሁን) ሲሆን ከመካከላቸው በላጪም እርሱው ነው። ከመካከላቸውም የጀነት ጠባቂና የጀሀነም ጠባቂ አሉ። ሌሎችም ደጋግ መላእክቶች አሉ። ከሰዎች መካከል ምእመናን የሆኑትንም ይወዷቸዋል፤ ለምእመናኖቹ ከአላህ መሀርታን መጠየቅንና ዱዓእ ማድረግንም ያበዛሉ።

ሦስተኛው ማዕዘን- ከአላህ በወረዱ ኪታቦች (መጽሐፍት) ማመን፦

በዚህም ሙስሊሙ አላህ ከመልክተኞቹ በሻው ላይ ጥራት ይገባውና ከእርሱ የሆኑ ትክክለኛ መረጃንና ፍትሃዊ መመርያዎችን የያዙ ኪታቦቹን (መጽሐፍት) ያወረደ መሆኑን ያምናል። በሙሳ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ላይ ተውራትን፣ በዒሳ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ላይ ኢንጅልን፣ በዳውድ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ላይ ዘቡርን እና በኢብራሂም (የአላህ ሰላም በእነርሱ ላይ ይሁን) ላይ ደግሞ ሱሑፍን አውርዷል። እነዚህ የተጠቀሱት ኪታቦች (መጽሐፍት) ታዲያ መጀመርያውኑ በወረዱበት ይዘት የሚገኙ አይደሉም። እንዲሁም በነብያቶቹ መደምደሚያ ሙሐመድም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ቁርአንን ማውረዱን እንደሚያምኑ ሁሉ ማለት ነው። አላህ ተከታታይ አንቀጾች ለሃያ ሶስት አመታት ያወረደ ሲሆን ለውጥና መዛባት እንዳያገኘውም ጠብቆታል። {እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው። እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን።} [አል-ሒጅር: 9]

አራተኛው ማዕዘን፡ በመልዕክተኞች ማመን

(በርግጥ ስለነብያቶች ቀደም ብለን በዝርዝር አውርተናል) እናም በጥቅሉ በመላው የሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ላሉ ህዝቦች ሁሉ ሃይማኖታቸው አንድ አይነት አምላካቸውም አንድ የሆነ የሰው ዘር በሙሉ አንዱን አምላክ አላህን እንዲያመልክ፤ ከሽርክ፣ ከክህደትና አመፅም እንዲቆጠቡ በሚል መርህ ዳዕዋ የሚያደርጉ የሆኑ ነብያቶች ተልኮላቸዋል። {ማንኛይቱም ሕዝብ በውስጧ አስፈራሪ ያላለፈባት የለችም።} [ፋጢር፡ 24] ነብያቶች አላህ መልእክቱን ለማስተላለፍ የመረጣቸው ከመሆናቸው ውጭ እንደሌሎች ሰዎች ሁሉ እነርሱም ሰዎች ናቸው። {እኛ ወደ ኑሕና ከርሱ በኋላ ወደ ነበሩት ነቢያት እንዳወረድን ወደ አንተም አወረድን። ወደ ኢብራሂምም፣ ወደ ኢስማዒልም፣ ወደ ኢስሓቅም፣ ወደ ያዕቆብም፣ ወደ ነገዶቹም፣ ወደ ዒሳም፣ ወደ አዩብም፣ ወደ ዩኑስም፣ ወደ ሃሩንና፣ ወደ ሱለይማንም አወረድን። ለዳውድም ዘቡርን ሰጠነው።} {ከዚህም በፊት በአንተ ላይ በእርግጥ የተረክናቸውን መልክተኞች ባንተ ላይም ያልተረክናቸውን መልክተኞች (እንደላክን ላክንህ)። አላህም ሙሳን ማነጋገርን አነጋገረው።} {ከመልክተኞቹ በኋላ ለሰዎች በአላህ ላይ አስረጅ እንዳይኖር አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች የኾኑን መልክተኞች (ላክን)። አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው።} [ኒሳእ: 163-165] ሙስሊሞች በሁሉም ነብያቶች ያምናሉ፤ ይወዷቸዋልም፤ ለሁሉም ደጋፊያቸውም ናቸው፤ በመካከላቸውም ልዩነትን አይፈጥሩም። በመሆኑም ከመነብያቶቹ በአንዳቸው እንኳ የካደ ወይም የዘለፋቸው አልያም ክብራቸውን ያጎደፈ ወይም ደግሞ አስቸጋሪ ሆኖ የተገኘ ሁሉ በሁሉም እንደካደ ነው።

ከመካከላቸውም በላጪና አላህ ዘንድም በማዕረግ ታላቁ የነብያት መደምደሚያ የሆኑት ነብዩ ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ናቸው።

አምስተኛው ማዕዘን፡ በመጨረሻው ቀን ማመን

አላህም ባሮቹን ከመቃብራቸው እንደሚቀሰቅሳቸው ሁሉንም በእለተ ትንሣኤ በቅርቢቱ ሕይወት ለሠሩት ሥራ ሊተሳሰባቸውም እንደሚሰበስባቸው ማመን ነው። {ምድር በሌላ ምድር የምትለወጥበትን ሰማያትም (እንደዚሁ) አንድ አሸናፊ ለኾነው አላህም (ፍጡራን ሁሉ) የሚገለጹበት ቀን (አስታውሱ)።} [ኢብራሂም: 48] {ሰማይ በተሰነጠቀች ጊዜ፤} {ከዋክብትም ተበታትነው በወደቁ ጊዜ፤} {ባሕሮችም በተከፈቱና በተደበላለቁ ጊዜ፤} {መቃብሮችም በተገለባበጡና (ሙታን) በተነሱ ጊዜ፤} {ማንኛይቱም ነፍስ ያስቀደመችውንና ያቆየችውን ታውቃለች።} [አል-ኢንፊጧር: 1-5] {ሰውየው እኛ ከፍቶት ጠብታ የፈጠርነው መኾናችን አላወቀምን? ወዲያውም እርሱ (ትንሣኤን በመካድ) ግልጽ ተከራካሪ ይኾናልን?} {ለእኛም ምሳሌን አደረገልን። መፈጠሩንም ረሳ። «አጥንቶችን እነርሱ የበሰበሱ ሲኾኑ ሕያው የሚያደርጋቸው ማነው?» አለ።} {«ያ በመጀመሪያ ጊዜ (ከኢምንት) ያስገኛት ሕያው ያደርጋታል። እርሱም በፍጡሩ ሁሉ (ኹኔታ) ዐዋቂ ነው» በለው።} {ያ ለእናንተ በእርጥብ ዛፍ እሳትን ያደረገላችሁ ነው። ወዲያውኑም እናንተ ከእርሱ ታቀጣጥላላችሁ።} {ያ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ ብጤያቸውን በመፍጠር ላይ ቻይ አይደለምን? ነው እንጅ። እርሱም በብዙ ፈጣሪው ዐዋቂው ነው።} {ነገሩም አንዳችን በሻ ጊዜ ኹን ማለት ነው። ወዲያው ይኾናልም።} {ያ የነገሩ ሁሉ ስልጣን በእጁ የኾነው ጌታ ጥራት ይገባው። ወደእርሱም ትመለሳላችሁ።} [ያሲን: 77-83] {በትንሣኤም ቀን ትክክለኛ ሚዛኖችን እናቆማለን። ማንኛይቱም ነፍስ ምንንም አትበደልም። (ሥራው) የሰናፍጭ ቅንጣት ያክል ቢኾንም እርሷን እናመጣታለን። ተቆጣጣሪዎችም በኛ በቃ።} [አል-አንቢያእ 47] {የብናኝ ክብደት ያክልም መልካምን የሠራ ሰው ያገኘዋል። (8) የብናኝ ክብደት ያክልም ክፉን የሠራ ሰው ያገኘዋል።} [አዝ-ዘልዘላህ 7-8] የጀሀነም ደጆች በእርሱ ላይ የአላህ ቁጣና ጥላቻ ላለበት ለአሳማሚ ቅጣቱም የተገባ ለሆነ ሰው የሚከፈቱ ሲሆን የጀነት በሮችም በጎ ሰሪ ለሆኑ ምእመናን ይከፈታሉ። {መላእክትም ይህ ያ ትቀጠሩ የነበራችሁት ቀናችሁ ነው፤ እያሉ ይቀበሏቸዋል።} [አልአንቢያእ፡ 103 {እነዚያ የካዱትም የተከፋፈሉ ጭፍሮች ኾነው ወደ ገሀነም ይንነዳሉ። በመጧትም ጊዜ ደጃፎችዋ ይከፈታሉ። ዘበኞችዋም «ከእናንተ የኾኑ መልክተኞች የጌታችሁን አንቀጾች በናንተ ላይ የሚያነቡላችሁ የዚህንም ቀን መገናኘት የሚያስጠነቅቋችሁ አልመጡዋ ችሁምን?» ይሏቸዋል። «የለም መጥተውናል፤ ግን የቅጣቲቱ ቃል በከሓዲዎች ላይ ተረጋገጠች» ይላሉ።} {እነዚያም ጌታቸውን የፈሩት የተከፋፈሉ ጭፍሮች ኾነው ወደ ገነት ይንነዳሉ። በመጧትም ጊዜ ደጃፎችዋ የተከፈቱ ሲኾኑ ዘበኞችዋም ለእነርሱ «ሰላም በናንተ ላይ ይኹን። ተዋባችሁ። ዘውታሪዎች ኾናችሁ ግቧት» በሏቸው ጊዜ (ይገቧታል)።} {«ምስጋና ለአላህ ለዚያ ተስፋ ቃሉን ለሞላልን። የገነትን ምድር በምንሻው ስፍራ የምንሰፍር ስንኾን ላወረሰን ይገባው» ይላሉም። የሠሪዎችም ምንዳ ምን ያምር!} [ዙመር፡ 71_75] ይህች ጀነት፤ ዓይን ያላየውን፣ ጆሮ ያልሰማውን፣ በሰው ልብ ውል ብሎ የማያውቅን ፀጋ ያለባት ነች። {ይሠሩትም በነበሩት ለመመንዳት ከዓይኖች መርጊያ ለእነርሱ የተደበቀላቸውን (ጸጋ) ማንኛይቱም ነፍስ አታውቅም።} {አማኝ የሆነ ሰው አመጸኛ እንደ ሆነ ሰው ነውን? አይስተካከሉም።} {እነዚያ ያመኑና መልካሞችን የሰሩማ ለእነርሱ ይሠሩት በነበሩት ምክንያት መስተንግዶ ሲሆኑ መኖሪያ ገነቶች አሏቸው።} {እነዚያ ያመጹትማ፤ መኖሪያቸው እሳት ናት። ከእርሷ መውጣትን በፈለጉ ቁጥር በእርሷ ውስጥ ይመለሳሉ። ለእነርሱም «ያንን በእርሱ ታስተባብሉበት የነበራችሁትን የእሳት ቅጣት ቅመሱ» ይባላሉ።} [ሰጅዳህ፡ 17_20] {የዚያች ጥንቁቆቹ ተስፋ የተሰጧት ገነት ምስል በውስጧ ሺታው ከማይለውጥ ውሃ ወንዞች፣ ጣዕሙ ከማይለወጥ ወተትም ወንዞች፣ ለጠጪዎች ሁሉ ጣፋጭ ከኾነች የወይን ጠጅም ወንዞች ከተነጠረ ማርም ወንዞች አልሉባት። ለእነርሱም በውስጧ ከፍሬዎች ሁሉ (በያይነቱ) ከጌታቸው ምሕረትም አልላቸው። (በዚች ገነት ውስጥ ዘውታሪ የኾነ ሰው) እርሱ በእሳት ውስጥ ዘውታሪ እንደኾነ ሰው፣

ሞቃትንም ውሃ እንደተጋቱ፣ አንጀቶቻቸውንም ወዲያውኑ እንደቆራረጠው ነውን? (አይደለም)።} [ሙሓመድ፡ 15] {አላህን ፈሪዎቹ በእርግጥ በገነቶችና በጸጋ ውስጥ ናቸው።} {ጌታቸው በሰጣቸው ጸጋ ተደሳቾች ኾነው (በገነት ውስጥ ናቸው)። የገሀነምንም ስቃይ ጌታቸው ጠበቃቸው።} {«ትሠሩት በነበራችሁት ምክንያት ተደሳቾች ኾናችሁ ብሉ፤ ጠጡም፤» (ይባላሉ)።} {በተደረደሩ አልጋዎች ላይ ተደጋፊዎች ኾነው (በገነት ይኖራሉ)። ዓይናማዎች በኾኑ ነጫጭ ሴቶችም እናጠናዳቸዋለን።} [ጡር፡ 17_20]

አላህ ሁላችንንም የጀነት ሰዎች ያድርገን።

ስድስተኛው ማዕዘን፡ መልካምም ሆነ መጥፎ በአላህ ቀደር (ቅድመ ውሳኔ) መሆኑን ማመን

እያንዳንዱ የዓለም እንቅስቃሴ ባጠቃላይ ልዕለ ኃያል በሆነው አላህ የተጻፈ ውሳኔ ነው። {በምድርም በነፍሶቻችሁም መከራ (ማንንም) አትነካም ሳንፈጥራት በፊት በመጽሐፍ የተመዘገበች ብትኾን እንጅ። ይህ በአላህ ላይ ገር ነው።} [አልሓዲድ፡ 22] {እኛ ሁሉን ነገር በልክ ፈጠርነው።} [አል ቀመር፡ 49] {አላህ በሰማይና በምድር ውስጥ ያለን ሁሉ በእርግጥ የሚያውቅ መኾኑን አታውቅምን ይህ በመጽሐፍ ውስጥ (የተመዘገበ) ነው። ይህ በአላህ ላይ ገር ነው።} [አልሓጅ፡ 70] እነኝህን ስድስቱ ማእዘናት አሟልቶ በትትክል ያመነባቸው ማንኛውም ሰው ሙእሚን ከሆኑ የአላህ ባሮች ይመደባል። ፍጥራታቱ ታዲያ በእምነት ደረጃ አንዱ ከሌላው ይለያያሉ። ከደረጃዎች ሁሉ ከፍተኛው የእምነት ደረጃ የኢሕሳን ደረጃ ሲሆን ይኸውም "አላህን አንተ ባታየው እንኳ እሱ ያይሀልና ልክ እንደምታየው ሆነህ ልታመልከው" ወደምትችልበት ደረጃ መድረስ ነው። እነዚህ በጀነት ውስጥ በፊርደውስ ካሉ ደረጃዎች ታላላቆቹን ደረጃዎች በመጎናፀፍ የስኬት ባለቤት የሆኑ የፍጥረታቱ ምርጦች ናቸው።

# 6- የእስልምና አስተምህሮቶች እና ስነ-ምግባር

## ሀ - ትእዛዞች

እነዚህ እስልምና የሙስሊሙን ማህበረሰብ ስነምግባር ስርአት ከማስያዝ አኳያ ሊጠቀሱ ከሚችሉ አስትምህሮቶች ጥቂቶቹን አጠር ባለ መልኩ ተውጣጥተው የሚገለፁት ናቸው። እነዚህ ስነ ምግባሮች የተውጣጡትም ቁንጮ ከሆኑት ሁለቱ የእስልምና አስተምህሮት ምንጮች ማለትም ከአላህ ኪታብ (ቁርአን) እና ከነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሓዲሶች ነው።

### አንደኛ፡ በንግግር እውነትኝነት፡-

እስልምና ሙስሊም የሆኑ ተከታዮቹን በንግግራቸው እውነተኞች እንዲሆኑ ግዴታ አድርጎባቸዋል። በምንም አይነት ሁኔታ እውነተኛ ከመሆን እንዳይወገዱም ከእነርሱው ጋር የተቆራኘ መገለጫ አድርጎታል። እንዲሁም ከውሸት ደግሞ እጅጉን ከልክሏቸዋል፤ በመጠቀ አገላለፅና በተብራራ መልኩም ከውሸት ያስጠነቅቃቸዋል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ፤ ከእውነተኞቹም ጋር ኹኑ።} [አት-ተውባህ: 119] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦ "(እናንተ ሰዎች) እውነተኝነት ላይ አደራችሁን! ምክንያቱም እውነተኝነት ወደ መልካምነት ይመራል፤ መልካምነት ደግሞ ወደ ጀነት ይመራልና። እናም አንዳችሁ እኮ እውነተኛ በመሆንና እውነትን በመምረጥ ላይ ከቀጠለ አላህ ዘንድ እውነተኛ ተብሎ ይመዘገባል። ውሸትን ተጠንቀቁ! ምክንያቱም ውሸታምነት ወደ አመፀኝነት ይመራል፤ አመፀኝነት ደግሞ ወደ ጀሀነም ይመራልና። እናም አንዳችሁ እኮ ውሸታም በመሆንና ውሸትንም በመምረጥ ከቀጠለ አላህ ዘንድ ውሸታም ተብሎ ይመዘገባል።"

ውሸት ከሙእሚን ባህሪያት መካከል አይደለም። ይልቁንም ከሙናፊቅ(7) ባህሪያት መካከል ነው። የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡- "የሙናፊቅ ምልክቱ ሶስት ነው፤ ሲናገር ይዋሻል፣ ቃል ሲገባ ቃሉን ያፈርሳል፣ ሲታመን ይክዳል።"

ለዚህም ነው ከመካከላቸው አንዱ "በአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ዘመን መዋሸት የሚባልን ነገር አናውቀውም ነበር" እስኪል ድረስ የተከበሩ ሶሓቦች በእውነተኛነት ላይ ጥብቅ አቋም የነበራቸው።

### ሁለተኛ፡ አደራን መወጣት፣ ቃል ኪዳኖችን መሙላት እና በሰዎች መካከል ፍትህን ማስፈን

የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {አላህ አደራዎችን ወደ ባለቤቶቻቸው እንድታደርሱ ያዛችኋል። በሰዎችም መካከል በፈረዳችሁ ጊዜ በትክክል እንድትፈርዱ (ያዛችኋል)።} [ኒሳእ: 58] አላህ -ጥራት ይገባውና- እንዲህም ይላል፦ {በኪዳናችሁም ሙሉ። ኪዳን የሚጠየቁበት ነውና።} {በሰፈራችሁም ጊዜ ስፍርን ሙሉ። በትክክለኛው ሚዛንም መዝኑ። ይህ መልካም ነገር ነው። መጨረሻውም ያማረ ነው።} [አልኢስራእ፡ 34_35] ምእመናኑንም እንዲህ በማለት አወድሷቸዋል፦ {እነዚያ በአላህ ቃል ኪዳን የሚሞሉ የጠበቀውንም ኪዳን የማያፈርሱ ናቸው።} [አር-ራዕድ: 20]

### ሦስተኛ፡ ትሕትና እና አለመኩራራት፡-

ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እጅግ በጣም ትሁት ከሆኑ ሰዎች መካከል አንዱ የነበሩ ሲሆን ከሶሃቦቻቸው መካከል እንደ አንዱ ሆነው የሚቀመጡ፤ መጡ ተብለው ሰዎች እንዲቆሙላቸው እንኳ የሚጠሉ ነበሩ። ሙስሊሞችንም ትሁት እንዲሆኑ እንዲህ በማለት አዘዋቸዋል፡- (አላህ አንዱ በሌላው ላይ እንዳይኮራበትና አንዱ በሌላው ላይ ድንበርን እንዳያልፍበት እርስ በእርሳችሁ እንድትናነሱ ወሕይ (ራእይ) አውርዶልኛል[3]።)

### አራተኛ፡ ልግስና፣ ቸርነት እና በበጎ አድራጎት ጉዳዮች ላይ ገንዘብን ማውጣት፡-

የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {ከገንዘብም የምትለግሱት (ምንዳው) ለነፍሶቻችሁ ነው። የአላህንም ፊት (ውዴታውን) ለመፈለግ እንጂ አትለግሱም። ከገንዘብም የምትለግሱት ሁሉ (ምንዳው) ወደናንተ ይሞላል። እናንተም አትበደሉም።} [አልበቀራህ፡ 272] አላህ ምእመናንን እንዲህ ሲል አሞግሷቸዋል፦ {ምግብንም ከመውደዳቸው ጋር ለድኻ፣ ለየቲምም፣ ለምርኮኛም ለእስረኛም ያበላሉ።} [አልኢንሳን፡ 8] ልግስና እና ቸርነት የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እና የእርሳቸውን ፈለግ የተከተሉ ምእመናን ባህሪ ናቸው። በዚህ ረገድ ምንም ገንዘብ ቢኖራቸው ለበጎ አድራጎት ከማዋል አይሰስቱም ነበር። ከነብዩ

---

[3] ሐዲሱን በሙስሊም (17/200) ኪታቡል ጀናህ: የጀነት ሰዎች የሚታወቁባቸው ባህሪያት በሚል ባብ ስር ዘግበውታል።

(የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ባልደረቦች አንዱ ጃቢር (አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸው) ስለሳቸው እንዲህ ብለዋል፦ "የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ምንም ነገር ተጠይቀው እምቢ ብለው አያውቁም።" እንግዳ ማክበርን በማስመልከትም እንዲህ ሲሉ አነሳስተዋል፦ {"በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ ጎረቤቱን አያስቸግር፤ በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ እንግዳውን ያክብር፤ በአላህና በመጨረሻው ቀን መልካምን ይናገር አሊያም ዝም ይበል።"

## አምስተኛ: ትዕግስት እና ችግርን መቋቋም:

የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {በሚያገኝህም መከራ ላይ ታገስ። ይህ በምር ከሚያዙ ነገሮች ነው።} [ሉቅማን፡ 17] አላህ -ጥራት ይገባውና- እንዲህ ብሏል፦ {እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በመታገስና በሶላት ተረዱ። አላህ (በእርዳታው) ከታጋሾች ጋር ነውና።} [አልበቀራህ፡ 153] የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {እነዚያንም የታገሱትን ይሠሩት በነበሩት በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን።} [ነሕል፡ 96] ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እጅግን ታጋሽ እና ችግርን የሚቋቋሙ እንዲሁም የማይበቀሉ ነበሩ። ህዝባቸውን ወደ እስልምና ሲጣሩ ህዝባቸው ግን እስኪደሙ ድረስ ደብድበዋቸዋል። እርሳቸው ግን የፊታቸውን ደም እያበሱ እንዲህ ነበር ያሉት፦ (አላህ ሆይ! ህዝቦቼ ባለማወቃቸው ነውና ይቅር በላቸው።)[4]

## ስድስተኛ፡ ሓያእ (አይናፋርነት)፦

ሙስሊሙ ጥብቅ እና አይናፋር ነው። አይናፋርነትም ከእምነት ቅርንጫፎች አንዱ ሲሆን ሙስሊምን ለመልካም ባህሪያት ሁሉ ያነሳሳዋል፤ ለሓያኡ ባለቤትም በቃልም ሆነ በተግባሩ ከብልግና እና ጸያፍ ነገሮች ያቅበዋል። በርግጥ የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦ "ሓያእ ይዞ የሚመጣው ኸይርን (መልካምን) ብቻ ነው።"[5]

## ሰባተኛ፡ ለወላጆች በጎ መዋል፦

ወላጅን ማክበር፤ ለነርሱ በጎን መዋል፤ በመልካም ሁኔታ መኗኗር እና የመዋረድ ክንፍን ለእነርሱ ዝቅ ማድረግ በእስልምና ሀይማኖት ውስጥ ካሉ መሰረታዊ ግዴታዎች መካከል ናቸው። ወላጆች ወይንም አንዳቸው እርጅና ሲጫጫናቸው እና የልጃቸውንም ይበልጥ ፈላጊ ሲሆኑ ደግሞ ይህ ግዴታ ይበልጥ አፅንኦት የተሰጠው ይሆናል። በእርግጥም የላቀው አላህ በታላቁ ኪታቡ (በቁርአን) ለእነርሱ በጎ መዋልን አዟል እንዲሁም የነርሱን ሓቅ ታላቅነትንም አፅንኦት ሰጥቶታል። ጥራት ይገባውና እንዲህ ብሏል፦ {ጌታህም (እንዲህ ሲል) አዘዘ፦ እርሱን እንጂ ሌላን አትገዙ። በወላጆቻችሁም መልካምን ሥሩ። በአንተ ዘንድ ኾነው አንዳቸው ወይም ሁለታቸው እርጅናን ቢደርሱ ፎህ አትበላቸው። አትገላምጣቸውም። ለእነርሱም መልካምን ቃል ተናገራቸው።} {ለሁለቱም ከእዝነትህ የመዋረድን ክንፍ ዝቅ አድርግላቸው። «ጌታዬ ሆይ! በሕፃንነቴ (በርኅራኄ) እንዳሳደጉኝ እዘንላቸውም» በል።} [አልኢስራእ፡ 23_24] አላህ -ጥራት ይገባውና- እንዲህ ብሏል፦ {ሰውንም በወላጆቹ (በጎ እንዲያደርግ) በጥብቅ አዘዝነው። እናቱ ከድካም በላይ በሆነ ድካም አረገዘችው። ጡት መጣያውም በሁለት ዓመት ውስጥ ነው። ለእኔም ለወላጆችህም አመስግን በማለት (አዘዝነው)። መመለሻው ወደኔ ነው።} [ሉቅማን:14] አንድ ሰው ነቢዩን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፦ “መልካም መስተጋብሬ ይበልጥ የሚገባው ማን ነው?” አላቸው። (“እናትህ” አሉት፤ “ከዚያስ ማን?” አለ፤ “እናትህ” አሉት፤ “ከዚያስ ማን?” አለ፤ “እናትህ” አሉት፤ “ከዚያስ ማን?” ሲላቸው ”አባትህ” በማለት መለሱለት።[6]

ስለዚህም እስልምና እያንዳንዱን ሙስሊም አላህን በማመፅ ጉዳይ ላይ ካልሆነ በቀር ወላጆቹን ያዘዙትን ነገር ሁሉ እንዲታዘዝ ግዴታ አድርጓል። አላህን በማመፅ ጉዳይ ላይ ሲሆን ግን ፈጣሪን በማመፅ ላይ ፍጡርን መታዘዝ የሚባል ነገር የለም። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል: {ለአንተ በእርሱ ዕውቀት የሌለህን ነገር በእኔ እንድታጋራ ቢታገሉህም አትታዘዛቸው። በቅርቢቱም ዓለም፤ በመልካም ሥራ ተወዳጃቸው።} [ሉቅማን: 15] እነሱን ማክበር፣ የመተናነስ ክንፉን ለነርሱ ዝቅ ማድረግ፣ በቃልም በተግባርም አክብሮት መስጠት እንዲሁም መመገብ፣ ማልበስ፣ ሲታመሙ ማሳከም፣ ችግር እንዳያገኛቸው በተቻለ አቅም መጣር በመሳሰሉት ፅድቅ ነገሮችም ሁሉ ለነርሱ በጎ መዋልም ግዴታ ተደርጓል። ለእነርሱ ዱዓእ ማድረግ፣ መሀርታን መለመን፣ ቃል የገባንላቸውን መፈፀምና ጓደኞቻቸውን እንኳ ማክበርም ለነርሱ በጎ መዋል ውስጥ የሚካተቱ ግዴታዎች ናቸው።

## ስምንተኛ፡ ከሌሎች ጋር መልካም ስነምግባር

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦ (ከሙእሚኖች መካከል ይበልጥ ኢማናቸው የተሟሉት በመልካም ሥነ-ምግባር በልጠው የተገኙት ናቸው።)[7]

የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦ "ከናንተ መካከል እኔ ዘንድ በጣም የተወደዳችሁትና በቂያማ ቀንም ለእኔ ይበልጥ ቅርብ የሆነ ደረጃ ያላችሁ ከእናንተ በሥነ ምግባር በላጭ የሆናችሁት ናችሁ።"[8]

አላህ ነብዩን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ሲል ገልጿቸዋል፦ {አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ።} [አል-ቀለም 4] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦ (እኔ የተላክሁት መልካም ስነምግባርን ላሟላ ነው።)[9]ስለዚህም እያንዳንዱ ሙስሊም ከላይ እንደገለፅነው ከወላጆቹ ጋር ባለው መስተጋብሩ መልካም ባህሪን መላበስና መልካም

---

[4] ሐዲሱን አል-ቡኻሪይ ኪታቡል ሙርተዲን በሚለው (5ኛው) ስር (9/20) ዘግበውታል።

[5] ሐዲሱን አል-ቡኻሪይ ኪታቡል አደብ: አልሓያእ በሚለው ባብ ስር (8/35) ዘግበውታል።

[6] ሐዲሱን አል-ቡኻሪ ኪታቡል አደብ መን አሐቁናሲ ቢሑስኒ ሱሕባህ በሚል ባብ ስር(8/2) ተዘግቧል።

[7] ሐዲሱን አቡ ዳውድ በኪታቡ ሱና፣ አድደሊሉ ዓላ ዚያደቲ ወኑቅሷኒህ በሚል ባብ ስር (5/6) እንዲሁም ቲርሚዚይ ኪታቡ ረዷዓህ፣ ማጃአ ፊ ሓቂል መርአቲ ዓላ ዘውጂሃ በሚል ባብ ስር (3/457) ዘግበውታል፤ ቲርሚዚይ ሓዲሱን ሓሰኑን ሶሒሕ ብለውታል፤ አልባኒይ የሰጡትን ደረጃ ለማየት ደግሞ ሶሒሕ አቢ ዳውድ (3/886) መመልከት ይቻላል።

[8] ሐዲሱን ቡኻሪይ ኪታቡል መናቂብ: ሲፈቱን ነቢይ ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም በሚል ባብ ስር (4/230) በሌላ የቃል አጠቃቀም ዘግበውታል።

[9] ሐዲሱን ኢማሙ አህመድ በአል-ሙስናድ (17/80) የዘገበው ሲሆን አህመድ ሻኪርም ኢስናዱ ሶሒሕ ነው ብለዋል፤ ቡኻሪይም በአል-አዳብ ፣ አል-በይሃቂይ ደግሞ በሹዐብ አል- ኢማን፣ እንዲሁም አል-ሀኪም በአል-ሙስተድረክ ላይ ዘግበውታል።

ሊሆንላቸውም ይገባል። ልክ ወላጆችም ከልጆቻቸው ጋር በመልካም ስነምግባር በማነፅ፣ የእስልምና አስተምህሮትንም በማስተማር እንዲሁም በዱንያም ይሁን በአኼራቸው ከሚጎዳቸው ነገርም ሁሉ እያስጠነቀቀ እንዲሁም ከገንዘቡም ሳይሰስትባቸው ራሳቸውን እስኪችሉና የራሳቸው የገቢ ምንጭም እስኪያመቻቹ ድረስ እየለገሰ ማሳደግ እንዳለበት ሁሉ ማለት ነው። በተመሳሳይ መልኩ ከሚስቱ፣ ከወንድሞቹ፣ ከእህቶቹ፣ ከዘመዶቹ፣ ከጎረቤቶቹና ከሁሉም ሰዎች ጋርም መልካም ባህሪ ያለው ለራሱ የሚወደውን ለወንድሞቹ የሚወድ ሊሆን ይገባል። ዝምድናውንም ጉርብትናውንም እየቀጠለ፣ ታላቆቹንም እያከበረ ለታናሾቹም እየራራ፣ ችግርተኞችንም እያፅናና ተከታዩን የአላህ ቃል ከመፈፀም አኳያ ጥሩ ስነምግባርን ይላበስ፦ {በወላጆችና በቅርብ ዝምድና ባለቤትም፣ በየቲሞችም፣ በምስኪኖችም፣ በቅርብ ጎረቤትም፣ በሩቅ ጎረቤትም፣ በጎን ባልደረባም፣ በመንገደኛም መልካምን (ሥሩ)} [አን-ኒሳእ: 36] እንዲሁም ተከታዩን የነቢዩን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ቃልም ከመፈፀም አኳያ፡ (በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምን ጎረቤቱን አያስቸግር።)[10]

## ዘጠነኛ፡ ተበዳይን ለመደገፍ፣ ሓቅን ወደ ባለቤቱ ከመመለስ እና ፍትህ ከማስፈን አኳያ በአላህ መንገድ ጂሃድ ማድረግ

የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {እነዚያንም የሚጋደሉዋችሁን (ከሓዲዎች) በአላህ መንገድ ተጋደሉ። ወሰንንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎን አይወድምና።} [አልበቀራህ፡ 190] ጥራት ይገባውና የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {በአላህ መንገድና ከወንዶች ከሴቶችና ከልጆችም የኾኑትን ደካሞች እነዚያን፦ «ጌታችን ሆይ! ከዚች ባለቤቶችዋ በዳይ ከኾኑት ከተማ አውጣን ከአንተም ዘንድ ለእኛ አሳዳሪን አድርግልን ከአንተ ዘንድም ለእኛ ረዳትን አድርግልን» የሚሉትን (ለማዳን) የማትጋደሉት ለእናንተ ምን አላችሁ} አንኒሳእ፡ 75] የኢስላማዊ ጂሃድ አላማ እውነትን ማግኘት፣ ፍትህን በሰዎች መካከል ማስፈን፣ ሰዎችን የሚጨቁኑ እና የሚያሰቃዩ ሰዎችን መዋጋት እና አላህን ከማምለክ እና የእስልምናን ህይማኖት እንዳይቀበሉ ማድረግ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎችን ማስገደድ የሚለውን ሃሳብ ውድቅ ያደርጋል። በግዳጅ ወደ እስልምና ህይማኖት ስለ መግባት ኃያሉ አምላክ እንዲህ ብሏል፦ {በሃይማኖት ማስገደድ የለም።} [አልበቀራህ፡ 256]

በጦርነት ጊዜ አንድ ሙስሊም፦ ሴትን፣ ትንሽ ልጅን ወይም ሽማግሌን መግደል አይፈቀድለትም፤ ይልቁንም ፍትሃዊ ያልሆኑ ተዋጊዎችን ይዋጋል።

በአላህም መንገድ የተገደለ ሁሉ ሰማዕት ነውና በአላህ ዘንድ ማዕረግ፣ ምንዳና ምንዳ አለው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {እነዚያን በአላህ መንገድ የተገደሉትን ሙታን አድርገህ አትገምታቸው። በእርግጥ እነርሱ እጌታቸው ዘንድ ሕያዋን ናቸው፤ ይመገባሉ።} {አላህ ከችሮታው በሰጣቸው ነገር ተደሳቾች ሲኾኑ (ይመገባሉ)። በነዚያም ከኋላቸው ገና በእነርሱ ባልተከተሉት በእነርሱ ላይ ፍርሃት ባለመኖሩና እነርሱም የማያዝኑ በመኾናቸው ይደሰታሉ።} [አሊ-ዒምራን 169 - 170]

## አስረኛ፡ ዱዓእ፣ ዚክር እና ቁርኣን መቅራት፦

የአንድ አማኝ እምነት በጨመረ ቁጥር ከላቀው አላህ ጋር ያለው ቁርኝት፣ እርሱን መማፀኑ እና በዚህ ዓለም ጉዳዩን እንዲያሟላለት፣ በአኼራው ደግሞ ኃጢአትና ከፋቶቹንም ይቅር እንዲልለት ብሎም ደረጃው ከፍ እንዲልለት በእርሱ ፊት ያለው መተናነስ ይጨምራል። አላህ ጠያቂ ሁሉ ቢጠይቀው የሚወድ ቸር አምላክ ነው። ጥራት ይገባውና እንዲህ ብሏል፦ {ባሮቼም ከእኔ በጠየቁህ ጊዜ (እንዲህ በላቸው)፦ እኔ ቅርብ ነኝ። የለማኝን ጸሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ።} (አልበቀራህ፡186) አላህ ለባሪያው የሚበጀውን ዱዓእ ይቀበለዋል፤ ብሎም ስለለመነውም መልካም ምንዳንም ይቸረዋል። እንደዚሁ ከምእመናን ባህሪያት መካከል ሌትም ቀንም በድብቅም ይሁን በግልጽ ደጋግሞ የላቀው አላህን የሚያወድስ መሆኑ ነው። ስለዚህም በተለያየ የውዳሴና ማላቅ አይነት አላህን ያወድሰዋል ያልቀዋልም፤ ለምሳሌ በሚከተለው አኳኃን፦ ሱብሓነሏህ (ጥራት ለአላህ ይገባው)፣ አልሓምዱሊላህ (ምስጋና ለአላህ ይገባው)፣ ላኢላሃ ኢለሏህ (ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም)፣ አሏሁ አክበር (አላህ ታላቅ ነው) እና ሌሎችም የላቀው አላህ እንዲወሳባቸው የተደነገጉ የውዳሴ አይነቶች ሁሉ አላህን ማወደስና ማላቅ የሙእሚን ባህሪይ ነው። ለዚህም የላቀው አላህ ከፍ ያለ አጅርንና ታላቅ ምንዳን አዘጋጅቷል። የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦ ("`ሙፈሪዶች` ቀድመው ሄዱ" አሉ "ያረሱለሏህ! "ሙፈሪዶች" እነማን ናቸው? በማለት ሰሓቦች ሲጠይቋቸው እሳቸውም "አላህን አብዝተው የሚያወሱ ወንዶችና አብዝተው የሚያወሱ ሴቶች ናቸው" በማለት መለሱላቸው።)[11]አላህ -ጥራት ይገባውና- እንዲህም ብሏል፦ {እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ብዙ ማውሳትን አውሱት።} {በቀኑ መጀመሪያና መጨረሻም አጥሩት። አስታውሱኝም፤} [አልአሕዛብ፡ 41_42] {አስታውሳችኋለሁና ለኔም አመስግኑ፤ አትካዱኝም።} [አልበቀራህ፡ 152] የአላህን ኪታብ - የተከበረው ቁርኣንን - መቅራት አላህን ከማውሳት ነው። አንድ ሰው ቁርኣን መቅራቱን እና ማስተንተኑን ባበዛ ቁጥር በአላህ ዘንድ ያለው ደረጃም ይበልጥ ከፍ እያለ ይሄዳል።

ቁርኣንን ሲቀራ ለነበረ ሰው በእለተ ትንሳኤ እንዲህ ይባላል፦ (ቁርአንን ቅራ እና ወደ ላይ ውጣ፤ ልክ በዱንያ ሳለህ ስትቀራ እንደነበርከው አድርገህ ቅራ፤ ዛሬ ደረጃህ መቅራትህን ባቆምክበት አንቀጽ ነውና የሚገደበው።)[12]

## አስራ አንደኛው፡ የሸሪዓን እውቀት መማር፣ ሰዎችን ማስተማር እና ወደዛውም ስለ መጣራት፦

የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦ (እውቀትን ፍለጋ መንገድን የጀመረ አላህ የጀነት መንገድን ያገራለታል። መላኢኮችም ዕውቀት ፈላጊ ለሆነ ሰው በሚያደርገው ነገር ተደስተው ክንፎቻቸውን ዝቅ ያደርጉለታል።) (20)

---

[10] ሐዲሱን ቡኻሪይ በኪታቡል አዳብ፡ መን ካነ ዩእሚኑ ቢላሂ ወል የውሚል አኺር ፈላ ዩእዚ ጃረሁ በሚል ባብ ስር (8/13) ዘግበውታል።

[11] ሐዲሱን ሙስሊም ኪታቡ ዚክሪ ወዱዓእ: አልሓሡ ዓለዚክር በሚለው ባብ ስር (17/4) ዘግበውታል።

[12] በአቡ ዳውድ (1464) የዘገበው ሲሆን ቃላቱ የእሱ ነው፤ ቲርሚዚይም (2914)፣ ነሳኢይም በ (አስ-ሱነን አል-ኩብራ) (8056) እና አህመድ (6799) ዘግበውታል።

የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህም ብለዋል፦ (ከናንተ በላጩ ቁርኣንን ተምሮ እና ያስተማረ ነው።)[13]የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህም ብለዋል፦ (በእርግጥ መላእክት ለሰዎች መልካምን እውቀት ለሚያስተምሩ ሰዎች ሶለዋትን ያወርዳሉ።)[14]የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህም ብለዋል፦ (ወደ ቀናነት ዳዕዋ ያደረገ ሰው በዳዕዋው ምክንያት የሰሩት ሰዎች አምሳያ አጅር አለው፤ የነርሱ ምንዳም ከቶ ምንም ሳይቀነስባቸው።)[15]
አላህ -ጥራት ይገባውና- እንዲህም ይላል፦ {ወደ አላህ ከጠራና መልካምንም ከሠራ፣ «እኔ ከሙስሊሞች ነኝ» ካለም ሰው ይበልጥ ቃሉ ያማረ ማን ነው?} [ፉሲለት፡ 33]

## አስራ ሁለተኛው፡ በአላህና በመልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ፍርድ ስለመርካት፦

አላህ የደነገገውን ትእዛዝ አለመቃወም፤ አላህ ከፈራጆች ሁሉ ጥበበኛ ከአዛኞችም ሁሉ በጣም አዛኝ፤ በምድርም በሰማይም ከርሱ የተደበቀ አንዳችም ነገር የሌለ፤ ፍርዱ በባሪያዎቹ ስሜታዊነትም ይሁን በግፈኞች ስግብግብነት የማይነካ ነውና። ከእዝነቱ መገለጫዎች መካከል ለባሮቹ በቅርቢቱም ሆነ በመጨረሻይቱ ዓለም የሚጠቅማቸውን እና ከአቅማቸው በላይ የማይችሉት የሆነን መመርያ አለማውጣቱ ነው። ለእርሱ ባርያ መሆን ከሚያስፈርዳቸው እውነታዎች መካከል ልባዊ ከሆነ እርካታ ጋር ወደርሱ ህግ መፋረድና በፍርዱም መደሰት ግድ ነው።
የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {በጌታህም እምላለሁ በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስከሚያስፈርዱህ ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከማያገኙና ፍጹም መታዘዝንም እስከሚታዘዙ ድረስ አያምኑም፤ (ምእመን አይኾኑም)።} [አን_ኒሳእ፡ 65] አላህ -ጥራት ይገባውና- እንዲህም ይላል፦ {የማይምንነትን ፍርድ ይፈልጋሉን ለሚያረጋግጡም ሰዎች ከአላህ ይበልጥ ፍርዱ ያማረ ማን ነው?!} [አልማኢዳህ፡ 50]

# ለ - ሐራምና ክልክል ስለሆኑ ነገሮች

## አንደኛ፡- ሽርክ፡ (የትኛውንም አይነት የአምልኮ ዓይነት ከአላህ ውጭ ላለ አካል አሳልፎ መስጠት)

ለምሳሌ ከአላህ ውጭ ላለ አካል የሚሰግድ፣ ወይም ከአላህ ውጭ ያለን አካል የሚለምን እና ጉዳዩንም እንዲያሳካለት ከአላህ ውጭ ያለን አካል የሚማፀን፣ ወይም ከአላህ ውጭ ላለ አካል መስዋእት የሚያደርግ፣ ወይም ከአላህ ላለ አካል ማንኛውንም አይነት አምልኮ የሚያቀርብ ሰው ሁሉ ሽርክ ነው። ያ የሚለመነው ህያውም ይሁን የሞተ፤ ወይም ቀብር፣ ወይም ጣኦት፣ ወይም ድንጋይ፣ ወይም ዛፍ፣ ወይም መላኢካ፣ ወይም ነብይ፣ ወይም ወሊይ ወይም እንስሳ አልያም ሌላ ነገርም ቢሆን ከአላህ ውጭ ያለን አካል መማፀን ሁሉ ሰውየው በተውባ እንደ አዲስ ወደ እስልምናው እስካልተመለሰ ድረስ አላህ ይቅር የማይለው የከባዱ ሽርክ አይነት ነው።
የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {አላህ በእርሱ ማጋራትን በፍጹም አይምርም። ከዚህ ሌላ ያለውንም (ኀጢአት) ለሚሻው ሰው ይምራል። በአላህም የሚያጋራ ሰው ታላቅን ኀጢአት በእርግጥ ቀጠፈ።} [ኒሳእ፡ 48] ሙስሊም አላህን እንጂ ሌላን አያመልክም፤ ከአላህ በስተቀር ሌላ ማንንም አይማፀንም፤ ለአላህም ብቻ ካልሆነ በቀር ለማንም አይዋረድም። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {«ስግደቴ፣ መገዛቴም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው» በል።} {«ለእርሱ ተጋሪ የለውም። በዚህም (በማጥራት) ታዘዝኩ። እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ» (በል)።} [አል_አንዓም 162_163] ከሽርክ አይነቶችም እንዲሁ፦ አላህ -ቀጣፊዎች ከሚቀጥፉት እጅጉን መላቅ ይገባውና- ሚስት ወይም ልጅ እንዳለው ማመን፤ ወይም በዚህ ፍጥረተ ዓልም ውስጥ የተለያየ ነገርን የሚያከናውኑ ከአላህ ሌላ የሆኑ አማልክት እንዳሉ ማመንም እንዲሁ ከከባዱ ሽርክ ነው። {በሁለቱ (በሰማያትና በምድር) ውስጥ ከአላህ ሌላ አማልክት በነበሩ ኖሮ በተበላሹ ነበር። የዐርሹ ጌታ አላህም ከሚሉት ሁሉ ጠራ።} [አልአንቢያእ፡ 22]

## ሁለተኛ፡ ድግምት፣ ጥንቆላ እና የሩቅ ምስጢር አዋቂነትን መሞገት፦

ድግምትና ጥንቆላ ክህደት ነው። ድግምተኛም ከሰይጣናት ጋር ቁርኝት ፈጥሮ፣ ከአላህ ሌላ እነርሱን አምልኮም ካልሆነ በቀር ድግምቱን እውን ሊያደርገው አይችልም። ስለዚህም ነው የትኛውም ሙስሊም ወደ ድግምተኞች መሄድም ይሁን የሩቅን ምስጢር አውቃለሁ በሚለው የውሸት ሙግታቸው አልያም ለወደፊት እንዲህ እንዲህ አይነት ነገር ይከሰታል ወይም ይሆናል ብለው በሚሞግቱት ሟርታቸው እውነት አድርጎ መቀበልም የማይፈቀድለት።
የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {«በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ ሩቅን ምስጢር አያውቅም። ግን አላህ (ያውቀዋል)። መቼ እንደሚቀሰቀሱም አያውቁም» በላቸው።} [አንነምል፡ 65] አላህ -ጥራት ይገባውና- እንዲህም ይላል፦ {«(እርሱ) ሩቁን ምስጢር ዐዋቂ ነው። በምስጢሩም ላይ አንድንም አያሳውቅም።»} {ከመልክተኛ ለወደደው ቢኾን እንጅ (ለሌላ አይገልጽም)። እርሱም ከስተፊቱም ከስተኋላውም ጠባቂዎችን ያደርግለታል።} [አል-ጂን: 26-27]

## ሦስተኛ፡ ግፍ (በደል)፦

በደል በነፍስ ወከፍ ደረጃ ተፅእኖ መፍጠር የሚችል እጅግ ብዙ ክፋቶችና አስቀያሚ ባህርያቶችን የሚያጠቃልል ብዙዎች የሚወድቁበት ሰፊ በር ነው። ግለሰብ ራሱን መበደሉ፣ በዙርያው ያሉትን መበደሉ፣ ማህበረሰቡን መበደሉ፣ ጭራሽ ጠላቶቹንም ቢሆን መበደሉን ሁሉ ያጠቃልላል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡- {ሕዝቦችንም መጥላት ባለማስተካከል ላይ አይገፋፉችሁ። አስተካክሉ። እርሱ (ማስተካከል) ለአላህ ፍራቻ በጣም የቀረበ ነው።} [አል-ማኢዳህ: 8] የላቀው አላህ በዳዮችን እንደማይወድ

---

[13] ሐዲሱን ቡኻሪይ ኪታቡል ፈዷኢል: ኸይሩኩም መን ተዓለመል ቁርአነ ወዓለመህ በሚል ባብ ስር (6/236) ዘግበውታል
[14] ሐዲሱን ቲርሚዚይ ኪታቡል ዒልም: ማ ጃአ ፊ ፈድሊል ፊቅሂ ዓለል ዒባዳህ በሚለው ባብ ስር (5/50) ረዘም ባለ አውድ ዘግበውታል።
[15] ሙስሊም ኪታቡል ዒልም: መን ሰነ ሱነተን ሓሰነተን አው ሰይአተን በሚለው ባብ ስር (16/227) ዘግበውታል።

አሳስቦናል። የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የላቀው አላህ እንዲህ ማለቱን ነግረውናል፦ (ባሮቼ ሆይ በደልን እኔ በራሴ ላይ እርም አድርጌአለሁ በመካከላችሁም እርም አድርጌዋለሁ። በመሆኑም አትበዳደሉ።)[16]የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦ ("ወንድምህን በዳይም ተበዳይም ሲሆን እርዳው፤" ከሶሓቦች መካከል አንዱ እንዲህ አለ፦ "የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሆይ! ተበዳይ ሆኖስ አዎን እረዳዋለሁ፤ እስኪ በዳይ ሆኖ እንዴት እረዳዋለሁ?" አላቸው። እሳቸውም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ አሉት፦ "ሌሎችን ከመበደል ትገታዋለህ ወይም ታቅበዋለህ"።)[17]

## አራተኛ፦ በሐቅ ካልሆነ በቀር መገደሏን እርም ያደረጋትን ነፍስ መግደል:

ነፍስ ማጥፋት በእስልምና ሀይማኖት ውስጥ ከባድ ወንጀል ነው። አላህ ነፍስን ላጠፋ ሰው በዱንያ ሳለ የተገዳዩ ቤተሰቦች ይቅር ካላሉለት በቀር ከባዱን ቅጣት ይኸውም እንዲገደል የፈረደበት ሲሆን በአኼራ ደግሞ አሳማሚ ስቃይ እንደሚጠብቀው የተዛተበት ከባድ ኃጢአት ነው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {በዚህ ምክንያት በእስራኤሌ ልጆች ላይ እነሆ ያለ ነፍስ (መግደል) ወይም በምድር ላይ ያለማጥፋት (ካልሆነ በስተቀር) ነፍስን የገደለ ሰው ሰዎቹን ሁሉ እንደገደለ ነው፤ ሕያው ያደረጋትም ሰው ሰዎቹን ሁሉ ሕያው እንዳደረገ ነው ማለትን ጻፍን።} [አል-ማኢዳህ 32] አላህ -ጥራት ይገባውና- እንዲህም ይላል፦ {ምእመንንም አስቦ የሚገድል ሰው ቅጣቱ በውስጧ ዘውታሪ ሲኾን ገሀነም ናት። አላህም በርሱ ላይ ተቆጣ። ረገመውም። ለእርሱም ከባድ ቅጣትን አዘጋጀ።} [ኒሳእ፡ 93]

## አምስተኛ፡ በሰዎች ገንዘብና ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ

ይህም በስርቆት፣ በዝርፊያ፣ በጉቦ፣ በማጭበርበር ወይም በሌላ መንገድም ቢሆን ከባድ ወንጀል ነው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {ሰራቂውንና ሰራቂይቱንም በሠሩት ነገር ለቅጣት ከአላህ የኾነን መቀጣጫ እጆቻቸውን ቁረጡ። አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው።} [አልማኢዳህ፡ 38] አላህ -ጥራት ይገባውና- እንዲህም ይላል፦ {ገንዘቦቻችሁንም በመካከላችሁ በከንቱ (ያለ አግባብ) አትብሉ።} [አልበቀራህ፡ 188] አላህ -ጥራት ይገባውና- እንዲህም ይላል፦ {እነዚያ የየቲሞችን ገንዘብ በመበደል የሚበሉ በሆዶቻቸው ውስጥ የሚበሉት እሳትን ብቻ ነው። እሳትንም በእርግጥ ይገባሉ።} [አን-ኒሳእ: 10]
እስልምና በሌሎች ገንዘብ ላይ ጥቃት ማድረስን አጥብቆ ይቃወማል፤ ከባድ እንደሆነም አበክሮ ገልጿል። እናም በሌሎች ንብረትና ገንዘብ ላይ ጥቃት በሚፈፅሙ ሰዎችም ይሁን በመሰሎቻቸው ላይ የህብረተሰቡን ስርዓት እና ደህንነት የሚያውኩ በመሆናቸው ከባድ ቅጣትን ጥሏል።

## ስድስተኛ፡ ማጭበርበር፣ ክህደት እና ተንኮል፦

እንደ መግዛትና መሸጥ፣ ውሎች እና በመሰሉ ሌሎችም መስተጋብሮች ላይ ሁሉ እነዚህ ባህርያት እስልምና የከለከላቸውና ያስጠነቀቃቸው የሆኑ ተወቃሽ ባህሪያት ናቸው።
የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {ለሰላቢዎች ወዮላቸው።} {ለእነዚያ ከሰዎች ባስሰፈሩ ጊዜ የሚያስሞሉ።} {ለእነርሱም (ለሰዎቹ) በሰፈሩ ወይም በመዘኑላቸው ጊዜ የሚያጎድሉ (ለኾኑት)።} {እነዚያ እነርሱ ተቀስቃሾች መኾናቸውን አያውቁምን?} {በታላቁ ቀን።} {ሰዎች ሁሉ ለዓለማት ጌታ (ፍርድ)፤ በሚቆሙበት ቀን (ተቀስቃሾች መኾናቸውን)።} [አል-ሙጠፊፊን: 1-5] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦ (የሚያታልለን (ያታለለን) ከእኛ አይደለም)[18]። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {አላህ ከዳተኛ ኃጢአተኛ የኾነን ሰው አይወድምና።} [ኒሳእ፡ 107]

## ሰባተኛ፡ ሰዎች ላይ ድንበር ማለፍ

በስድብ፣ ዘለፋ፣ ሐሜት፣ ነገር ማዋሰድ፣ ምቀኝነት፣ ክፉ ጥርጣሬ፣ ስለላ፣ መሳለቅ፣ ወዘተ. በመሳሰሉ ነገሮች የሰውን ክብር መዳፈር የተከለከለ ነው። እስልምና ፍቅር፣ ወንድማማችነት፣ መተሳሰብና መተጋገዝ የሚመራው ንጹህ እና ፅድት ያለ ማህበረሰብን ለመመስረት የሚጓጓ ሃይማኖት ነው። ስለዚህም ነው ማህበረሰቡን እንዲበታተን እና በግለሰቦቹም መካከል ጥላቻና መቃቃርን እንዲሁም ራስ ወዳድነትን እንዲሰፍን የሚያደርጉ የህብረተሰብ በሽታዎችን ሁሉ በብርቱ የሚቃወመው።
የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወንዶች ከወንዶች አይቀልዱ። ከእነርሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና። ሴቶችም ከሴቶች (አይሳለቁ)። ከእነርሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና። ነፍሶቻችሁንም አታነውሩ። በመጥፎ ስሞችም አትጠራሩ። ከእምነት በኋላ የማመጽ ስም ከፋ። ያልተጸጸተም ሰው እነዚያ እነርሱ በዳዮቹ ናቸው።} {እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከጥርጣሬ ብዙውን ራቁ፤ ከጥርጣሬ ከፊሉ ኃጢአት ነውና። ነውርንም አትከታተሉ። ከፊላችሁም ከፊሉን አይማ። አንደኛችሁ የወንድሙን ስጋ የሞተ ኾኖ ሊበላው ይወዳልን? (መብላቱን) ጠላችሁትም፤ (ሐሜቱንም ጥሉት)። አላህንም ፍሩ። አላህ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ ነውና።} [አልሑጁራት፡ 11_12] ልክ እስልምና በህብረተሰቡ መካከል የሚደርሰውን ዘርና ጎሳን መሰረት ያደረገ መለያየትን አጥብቆ የሚቃወም እንደሆነው ሁሉ ማለት ነው። አረቦች ከአረብ ካልሆኑት፤ ወይም ነጩም ሆነ ጥቁሩ ምናልባት በውስጣቸው ካለው ሃይማኖተኛነትና ፈሪሃ አላህ (ተቅዋ) ካልሆነ በቀር በሰብአዊ ማንነቱ ሁሉም እኩል ነው። ሁሉም በእኩል ደረጃ ለመልካም ስራ ይሽቀዳደማሉ። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ። እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ። አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው። አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነው።} [አል-ሑጁራት: 13]

## ስምንተኛ፡ ቁማር መጫወት፣ አስካሪ መጠጥ መጠጣት እና ዕፆችን መውሰድ፦

የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {እናንተ ያመናችሁ ሆይ! የሚያሰክር መጠጥ ቁማርም ጣዖታትም አዝላምም ከሰይጣን ሥራ የኾኑ እርኩስ ብቻ ናቸው። (እርኩስን) ራቁትም ልትድኑ ይከጀላልና።} {ሰይጣን የሚፈልገው በሚያሰክር መጠጥና በቁማር በመካከላችሁ

---

[16] ሙስሊም ኪታቡል ቢሪ ወሲለቲ ወለአደቢ: ተሕሪሙ ዙልም በሚለው ባብ ስር (16/132) ዘግበውታል።
[17] ቡኻሪይ ኪታቡል መዟሊሚ ወልገሶቢ: አዒን አኻከ ዟሊመን አው መዝሉመን በሚለው ባብ ስር (3/168) ዘግበውታል።
[18] ሐዲሱን ሙስሊም ኪታቡል ኢማን: መን ገሸ ፈለይሰ ሚንና የሚለው የነብዩ ቃል በሚለው ባብ ስር (2/109) ዘግበውታል።

ጠብንና ጥላቻን ሊጥል አላህን ከማውሳትና ከስግደትም ሊያግዳችሁ ብቻ ነው። ታዲያ እናንተ (ከእነዚህ) ተከልካዮች ናችሁን (ተከልከሉ)።} [አል-ማኢዳህ: 90-91]

## ዘጠነኛ፡ የበከተ ሥጋ፣ ደም እና የአሳማ ሥጋ መብላት፦

ለሰው ልጅ ጎጂና ቆሻሻ ነገሮች ሁሉ ሓራም ናቸው። እንዲሁም ከአላህ ውጭ ላለ አካል የሚቃረቡበት መስዋዕትነትም ሓራም ነው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከነዚያ ከሰጠናችሁ ጣፋጮች ብሉ። ለአላህም እርሱን ብቻ የምትገዙ እንደኾናችሁ አመስግኑ።} {በናንተ ላይ እርም ያደረገው በክትንና ደምን፣ የእሪያ ሥጋንም፣ በእርሱም (ማረድ) ከአላህ ስም ሌላ የተነሳበትን ነገር ብቻ ነው። ሸፍታና ወሰን አላፊ ሳይኾን (ለመብላት) የተገደደ ሰውም በርሱ ላይ ኃጢኣት የለበትም አላህ መሓሪ አዛኝ ነውና።} [አልበቀራህ፡ 172_173]

## አስረኛ፡- በዝሙትና ግብረሰዶማዊነት መጨማለቅ፦

ዝሙት ሥነ ምግባርን እና ማህበረሰቦችን የሚያበላሽ እና ለዘር መቀላቀል፣ ለቤተሰብ መጥፋት እና ትክክለኛ አስተዳደግ እንዲጠፋ የሚዳርግ እኩይ ተግባር ነው። የዝሙት ልጆች የሆኑ ሞራላቸው ተጎድተውና ማህበረሰብ ጠል ሆነው ነው የሚያድጉት። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {ዝሙትንም አትቅረቡ። እርሱ በእርግጥ መጥፎ ሥራ ነውና። መንገድነቱም ከፋ!} [አልኢስራእ፡ 32] የህብረተሰቡን ሁኔታ የሚያበላሹ ለሆኑ የአባላዘር በሽታዎች መስፋፋትም ምክንያት ነው። ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡- (ብልግና በሕዝቦች መካከል በይፋ እስከተንሰራፋ ድረስ በቀደምቶቻቸው ዘንድ ያልነበሩ በሽታዎችና ወረርሽኞችም በመካከላቸው መስፋፋታቸው አይቀርም።)[19]

ስለዚህም እስልምና ወደዚያ የሚወስዱ መንገዶች ሁሉ እንዲገቱ አዟል። በዚህም መሰረት ሙስሊሞች ዓይኖቻቸውን ዝቅ እንዲያደርጉ አዟል፤ ምክንያቱም የተከለከለው እይታ የዝሙት መንገድ መንደርደርያ ነውና። ህብረተሰቡ ከሥነ ምግባር ብልሹነትና ብልግና ሊጠበቅ ዘንድ ሴቶችንም እንዲሰተሩ፣ በልብሳቸውም እንዲሸፈኑ እና ጨዋዎችም እንዲሆኑ አዟል። በአንፃሩ ትዳርን አዘዘ፤ የሚጋቡ ሰዎችንም አበረታታ፤ ባልና ሚስት ራሳቸውን በማርካታቸው እንኳ መልካም አጅርንና ምንዳንም እንደሽልማት አዘጋጀ። ይህም የተከበረ፣ ጨዋ ቤተሰብና በቤተሰቡም ውስጥ ኃላፊነት የሚሰማው ማህበረሰብ እንዲፈጠር የሚያስችል የዛሬ እንቡጥ የነገ ጀግና ትውልድ መፍራት ሊችል ዘንድ ነው።

## አስራ አንደኛው፡ አራጣ መብላት

አራጣ ኢኮኖሚን ማውደም እና ንግዱ እንዲጠፋ ማድረግ ለሚችል ነጋዴም ይሁን የለት ጉርሱን ለሚያድን ችግረኛ በገንዘብ ፍላጎቱ መግዛት ነው። አራጣ ብድር ማለት ገንዘብን በሚከፈልበት ጊዜ የተወሰነ ጭማሪ አክሎበት እንዲመልስ በሚል ስምምነት ገንዘብን ማበደር ነው። ስለዚህም አበዳሪው የገንዘብ ፈላጊውን ችግር ለገንዘቡ ማደለቢያ ያደርገውና ተበዳሪን ከካፒታሉ ጭማሪ በሚጭንበት ትርፍ ብድር ሸክሙን ያከብድበታል።

አራጣ አበዳሪ የነጋዴንም፣ የአምራችንም፣ የገበሬንም ወይም ሌሎች የኢኮኖሚው ዝውውር አካላትንም ሁሉ ችግር የራሱን ገንዘብ ማደለቢያ ያደርጋል።

አስቸኳይ የጥሬ ገንዘብ ፍላጎታቸውን ተጠቅሞ የውድቀትና ኪሳራ አደጋ ቢያጋጥማቸው እንኳ ላይጋራቸው በሚያበድራቸው ብድር ላይ ተጨማሪ ጫና ይጥልባቸዋል።

እናም ይህ ነጋዴ ቢከስር እዳው ይከማችበትና አራጣ አበዳሪው በሰጠው ብድር ድባቅ ይመታል። ነገር ግን እስልምና ባዘዘው መልኩ ትርፍ እና ኪሳራ ተጋርተው አንዱ በጥረቱ ሌላኛው ደግሞ በገንዘቡ ቢተጋገዙ ኖሮ የኢኮኖሚው ዝውውር ለሁሉም ጥቅም ዘለቄታዊ ደስታን ያስገኝ ነበር።

የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ። ከአራጣም የቀረውን ተዉ። አማኞች እንደኾናችሁ (ተጠንቀቁ)።} {(የታዘዛችሁትን) ባትሠሩም ከአላህና ከመልክተኛው በኾነች ጦር (መወጋታችሁን) ዕወቁ። ብትጸጸቱም ለእናንተ የገንዘቦቻችሁ ዋናዎች አሏችሁ። አትበድሉም አትበደሉምም።} {የድኻነት ባለቤት የኾነም (ባለዕዳ) ሰው ቢኖር እማግኘት ድረስ ማቆየት ነው። (በመማር) መመጽወታችሁም ለእናንተ በላጭ ነው። የምታውቁ ብትኾኑ (ትሠሩታላችሁ)።} [አል-በቀራህ: 278-279]

## አስራ ሁለተኛው፡ መስገብገብ እና ስስታምነት

እኔ ብቻ የማለትና የራስ ወዳድነት ጠቋሚ ምልክት ነው። ይህ ንፉግ አላህና መልዕክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ያዘዙንን የመተባበርና የወንድማማችነትን መሰረት ገፍትሮ ለሚስኪኖችና ለድሆች የሚሰጠውን የዘካ ግዴታውንም ሆነ በጥቅሉ ማህበረሰቡን ችላ ብሎ ገንዘቡን ማከማቸት ብቻ ነው ኢላማው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {እነዚያም አላህ ከችሮታው በሰጣቸው ገንዘብ የሚነፍጉ እርሱ ለእነሱ ደግ አይምሰላቸው። ይልቁንም፤ እርሱ ለነሱ መጥፎ ነው። ያንን በርሱ የነፈጉበትን በትንሣኤ ቀን (እባብ ኾኖ) ይጠለቃሉ። የሰማያትና የምድርም ውርስ ለአላህ ብቻ ነው። አላህም በሚሠሩት ሁሉ ውስጥ ዐዋቂ ነው።} [አሊ-ዒምራን 180]

## አስራ ሦስተኛው፡ ውሸት እና የሀሰት ምስክርነት፦

የነቢዩን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ተከታዩ ቃል አስቀድመናል፦ "… ውሸትን ተጠንቀቁ! ምክንያቱም ውሸታምነት ወደ አመፀኛነት ይመራል፤ አመፀኛነት ደግሞ ወደ ጀሀነም ይመራልና። እናም አንዳችሁ ውሸታም በመሆንና ውሸትንም በመምረጥ ከቀጠለ አላህ ዘንድ ውሸታም ተብሎ ይመዘገባል።" እጅጉን ከሚጠሉ ውሸቶች መካከል የውሸት ምስክርነት ተጠቃሽ ነው። በእርግጥ ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ነገሩን በመቃወም እና መዘዙንም በማስጠንቀቅ በኩል እጅግ አሳስበዋል። ለሶሓቦቻቸውም በዚህ ረገድ ሲናገሩ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው የሚከተለውን ብለዋል፦ ("ከከባባድ ወንጀሎች መካከል አልጠቁማችሁምን? በአላህ ማጋራት፣ ወላጆችን ማመፅ" ካሉ በኋላ ተጋድመው አረፍ ካሉበት ከፍ ብለው ተቀመጡና

---

[19] ሐዲሱን ኢብኑ ማጃህ ኪታቡል ፊተን: አልዑቁባት በሚለው ባብ ስር (2/1333) ዘግበውታል። አልባኒም በሰሒሕ ኢብኑ ማጃህ) (2/370) ሓዲሡ የሓሰንነት ደረጃ እንዳለው ገልፀዋል።

እንዲህ አሉ: “የውሸት ምስክርነትን ተጠንቀቁ፤ የውሸት ምስክርነትን ተጠንቀቁ።”)[20]ህዝባቸው በዚህ ነገር እንዳይወድቅ ለማሳሰብ በጣም ነበር የደጋገሙት።

## አሥራ አራተኛ፡ ኩራት፣ ትምክህተኝነት፣ በራስ መደነቅ እና ትዕቢት

ኩራት፣ ትምክህተኝነትና ትዕቢት በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ አስቀያሚ፣ የተወገዙና አስጸያፊ ተብለው ከተመደቡት ባህሪያት ናቸው። በርግጥ የላቀው አላህ ኩራተኞችን እንደማይወድም ነግሮናል። ስለ እነርሱ በአኼራ ያላቸው ሁኔታ ሲገልፅልን እንዲህ ብሏል፦ {በገሀነም ውስጥ ለትዕቢተኞች መኖሪያ የለምን?} [ዙመር፡ 60] ኩራተኛ፣ ትምክህተኛና በራሱ የሚደነቅ ሰው አላህ ዘንድም ይሁን ፍጥረታቱ ዘንድ የተጠላ ነው።

## ሐ- ከሓራም ነገሮች ተውባ ማድረግ

እነዚህ ከፍ ብለን የጠቀስናቸው አበይት ወንጀሎችና ክልከላዎች ናቸው። ማንኛውም ሙስሊም በእነርሱ ውስጥ እንዳይወድቅ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት። እያንዳንዱ ሰው ሲሰራው በነበረው ስራ ሁሉ መልካም ከነበረ በመልካምነቱ መጥፎ ከነበረ ደግሞ በመጥፎነቱ በትንሳኤ ቀን ምንዳውን ያገኛል።

የትኛውም ሙስሊም ከእነዚህ ክልከላዎች ውስጥ በአንዱ እንኳ ቢወድቅም ፈጥኖ ይጸጸት በተውባ ወደ አላህ ይመለስና ምህረትንም ይለምነው። ተውባው የምር እስከሆነ ድረስ ደግሞ ድጋሚ ወደ ወንጀሉ መመለስ የለበትም፤ ይልቁን በሰራው ነገር መፀፀት፤ ድጋሚ ላይመለስ ቁርጥ አድርጎ መወሰን ነው ያለበት። ምናልባት የበደለው አካል ከነበረ ደግሞ ከቻለ የበደለበትን መመለስ አለዚያ ደግሞ የተበዳዩን ይቅርታ መጠየቅ አለበት። የዚህኔ ተውባውም የምር ተውባ ይሆንለታል፤ አላህም ተውባ ባደረገበት ጉዳይ ላይቀጣው መሀርታውን ይለግሰዋል፤ ከኃጢአቱ ተውባ ያደረገ ኃጢአቱም ላይ እንዳልወደቀ ነውና።

እናም የአላህን ምህረት አብዝቶ መጠየቅ አለበት። ይልቁንም እያንዳንዱ ሙስሊምም ለሚያውቃቸው ትንንሽም ይሁን ትላልቅ ስህተቶቹ አብዝቶ የአላህን መሀርታ መጠየቅ አለበት። {«አልኳቸውም፦ ጌታችሁን ምሕረትን ለምኑት። እርሱ በጣም መሐሪ ነውና።} [ኑሕ፡ 10] አዘውትሮ ምህረትን መጠየቅ እና ወደ አላህ መመለስ የምርጥ ሙእሚኖች ባህሪ ነው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {በላቸው «እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ። አላህ ኃጢኣቶችን በመላ ይምራልና። እነሆ እርሱ መሓሪው አዛኙ ነውና።} {«ቅጣቱም ወደእናንተ ከመምጣቱና ከዚያም የማትርረዱ ከመኾናችሁ በፊት ወደ ጌታችሁ (በመጸጸት) ተመለሱ። ለእርሱም ታዘዙ።} [ዙመር፡ 53 _ 54]

## መ - ሙስሊሞች ይህንን ሃይማኖት በትትክል እንዲሰራጭ የሰጡት ትኩረት፦

የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ንግግር፣ ድርጊትና ማፅደቅ የአላህን ቃል፣ የእስልምና ሃይማኖት ትእዛዛት እና ክልከላዎችን የሚያብራሩና ግልፅ የሚያደርጉ ማስረጃዎች በመሆናቸው ሙስሊሞች እነዚህን ትውፊቶች (ሓዲሥ) ከመልዕክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) በመልቀሙ ላይም ይሁን የተዘገቡት ሐዲሶች በትክክል ከነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የተገኙና ጭማሪ የሌላቸው የነጠሩ ሓዲሦች መሆናቸውን በማጣራቱም ላይ እንዲሁም ተድበስብሰው ሰርገው የገቡ ቅጥፈቶችን በማብጠሩ ላይም ታላቅ ትግልን አድርገዋል። ለዚህም ይረዳቸው ዘንድ እነዚህ ትውፊቶች ወይም ሓዲሦች ከተውልድ ትውልድ በሚተላለፋበት ጊዜ ሊስተዋሉ የሚገባቸውን ረቂቅ መርሆዎችንና ስርአትን አደረጉ።

እናም ለአንባቢ ምንም እንኳ ጊዜያቶች ቢነጉዱም አላህ ለዚች ሙስሊም ማህበረሰብ ያገራላት ስለሆነው ዲኗን ጥርት ንጥር ባለ መልኩ ውሸትና እንቶ ፈንቶ ሳይቀላቀልበት የነብያቸውን ተውፊቶችና ሓዲሦችን ከትውልድ ትውልድ ስላሸጋገሩበት ብሎም ከሌላው ጎዳናና ኡማ የተለዩበት ስለሆነው በዚህ የእውቀት ዘርፍ (የሐዲስ ጥናት) ዙርያ እጅግ ባጠረ መልኩ እንነጋገራለን።

የአላህ እና የመልዕክተኛውን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) አስተምህሮትና ንግግር መተላለፍ በሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የተመሰረተ ነው።

እነሱም በልቦና መሸምደድ እና በፅሁፍ ማስቀመጥ ናቸው። የመጀመሪያዎቹ ሙስሊሞች ትክክለኛ የመሃፈዝ ችሎታና አስፍቶ የመገንዘብ ችሎታ ነበራቸው። ይህም የሚለዩበት በሆነው አእምሯዊ ጥራት እና የማስታወስ ብርታት አማካኝነት ነው። ይህ ደግሞ ታሪካቸውን ላጠና ስለ እነርሱ ለሚያውቅ ሰው ሁሉ የማይሰወርበትና ግልፅ የሆነ ጉዳይ ነው። ሶሓብዩ ከነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንደበት ሓዲሥን ሰምቶ በደንብ ሸምድዶ ለቀጣዩ የመሸምደድ ችሎታ ያለው ታቢዒይ ያስተላልፋል። እርሱም በተራው ከሱ በኋላ ለነበሩት ያስተላልፈዋል። በዚህ ሂደት ሐዲሶችን ወደሚጽፍ አንድ የሐዲሥ ሊቅ ዘንድ እስኪደርስ ይቀጥልና ይህ ሊቅ በፅሁፍ ያሰፍረዋል። በልቦናውም ሸምድዶ በመፅሃፍ ውስጥም ያሰፍረውና ለተማሪዎቹም ይህንን መጽሐፍ ያነብላቸዋል። እነርሱም ሓዲሦቹን በቃላቸውም ሓፍዘው በፅሁፍም ያሰፍሩታል። ከዚያም እነርሱም ለተማሪዎቻቸው በዛው ሂደት ለቀጣዩ ትውልድ ያስተላልፉታል። በዚህ መልኩና ሂደት (የዘገባ ሰንሰለት) እነዚህ የሓዲሥ ስብስቦች ወደ መላው ትውልድ እየተላለፉ ይገኛል።

በዚህም ምክንያት የትኛውም የረሱል (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሓዲሥ ዘገባው የተላለፈበት ሰንሰለት ሳይጣራ ሓዲሡ ተቀባይነትን አያገኝም።

ይህም የእስልምናን ማህበረሰብ ከሌሎች ማህበረሰቦች የሚለይበት የሆነን ሌላ እውቀት ይዞ መጣ። ይህም የዘገባ ሰንሰለት (ሰነድ) ጥናት ወይም የሰዎች ሓዲሥን ለማስተላለፍ ብቁ መሆንና አለመሆን የሚጣራበት የእውቀት ዘርፍ (ዒልመል ጀርሕ ወተዕዲል) ነው።

የአላህ መልእክተኛ ሰ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሓዲሥን ስለሚያስተላልፉ ዘጋቢዎች ማንነት የሚያጠና የእውቀት ዘርፍ ነው። በሓዲሡ ዘገባ ላይ ያሉ ግለሰቦች በነፍስ ወከፍ ደረጃ የሕይወት ታሪካቸውን፣ የተወለዱበትን እና የሞቱበትን ቀን፣ ሸይኾቻቸውና (መምህሮቻቸው) ተማሪዎቻቸው እነማን እንደነበሩ፣ የዘመኑ ሊቃውንት ዘንድ የነበራቸው የታማኝነት ደረጃ፣ የመሓፈዝ (የመሸምደድ) አቅምና ችሎታቸው፣ አደራ ጠባቂነትና የንግግራቸው እውነተኛነት እንዲሁም መሰል ማንነታቸውን የሓዲሥ አስተላላፊ ሊኖረው ከሚገባው ስብእና አኳያ የሚጠናበት የእውቀት ዘርፍ ነው።

---

[20] ሐዲሱን ኪታቡ ሸሃዳት: ማቂለ ፊ ሸሃደቲ ዙር በሚለው ባብ ስር (3/225) ዘግበውታል።

ይህ እውቀት ህዝበ ሙስሊሙ ከነብያቸው (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ተላልፈዋል የተባሉ ሐዲሦችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከሌላው ማህበረሰብ ሁሉ የተለዩበት እውቀት ነው። እናም ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያንድን አካል ንግግር ትክክለኛነት በማጣራት ረገድ ይህን የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ንግግርን ለማጣራት የተደረገውን ያህል ትልቅ እና ከፍተኛ ጥረት የተደረገበት የታሪክ ክስተት ተከስቶ አያውቅም።
በሐዲስ ዘገባ ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ባደረጉ መፃህፍት የተሰበሰበ ትልቅ እውቀት ነው። እናም እነዚህ መጻሕፍት የረሱል (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሐዲሦችን ከትውልድ ወደ ትውልድ በማስተላለፍ ላይ አስተዋፅኦ በማበርከታቸው ብቻ የብዙ ሰዎችን የህይወት ታሪክ መዝግበዋል። በነዚህ የጥናቱ መፃህፍት ላይ እንደሚዛን የተቀመጡትን ረቂቅ መርሆችን ከመከተል ውጭ በጅምላ ፍረጃ አግበስብሶ ማለፍ የለም። የሚዋሸውን ይዋሻል ነው የሚባለው፤ ለእውነተኛውም እውነተኛ ነው፤ የሽምደዳ ችሎታው ደካማው ደካማ ነው፤ የሽምደዳ ችሎታ ጠንካራ የሆነውን ጠንካራ ሓፊዝ ነው ብለው ለዚህም ያመቻቸው ዘንድ የዘርፉ ሊቃውንት የሚያውቋቸው የሆኑ ረቂቅ መርሆዎችን አስቀምጠዋል።
እናም በዘርፉ ሊቆች መሰረት የሐዲሥ ዘጋቢዎች ሰንሰለት(ሰነድ) እርስ በርሱ የተቀጣጠለ ካልሆነ በቀር ሐዲሱ ሶሒሕ አይደለም። የተቀጣጠለው የሓዲሥ ዘገባ ሰንሰለትም (ሰነድ) ታዲያ እያንዳንዱ ዘጋቢ ለማስተላለፍ የሚያስቸለው ብቁነት፣ የንግግር እውነተኝነት ከጠንካራ የሽምደዳ ችሎታ ጋር ያሟላ ሊሆን ይገባዋል።

## ሌላው በሓዲሥ ጥናት የማይዘነጋው ነገር

ለአንድ ሐዲሥ የዘጋቢዎች ሰንሰለት መብዛትን በተመለከተ ነው። ስለዚህም የተወሰነው ሓዲሥ ከአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የተዘገበበት የዘገባ ሰንሰለት (ሰነድ) ብዛት ከአንድ በላይ በርከት ያለ ሰነድ (ሰንሰለት) የሚሆንበት አጋጣሚ አለ። እናም የአንዱ ሐዲስ የዘገባ ሰንሰለት (ሰነድ) ብዛት ሁለት፣ ሶስት ወይም አራት የኢስናድ ሰንሰለቶች ሊኖሩት ይችላል። አንዳንዴም አስር የዘገባ ሰንሰለቶች አንዳንዴ ደግሞ ከዚያም በላይ የሆነ የዘገባ ሰንሰለት (ሰነድ) ሊኖረው ይችላል።
የዘገባ ሰንሰለቱ (ሰነድ) ብዛቱ በጨመረ ቁጥር የሓዲሱ ታማኝነትም እየበረታ ይመጣና ከረሱል (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) መተላለፉ ይበልጥ ብርቱ ታማኝነት ይኖረዋል። በሁሉም የሓዲስ ሰንሰለት ዘገባ እርከን ላይ ከአስር በላይ ታማኝ ሰዎች የዘገቡት ሁዲስ "ሓዲሡን ሙተዋቲር" ተብሎ የሚጠራ ሲሆን በሙስሊሞች ዘንድ ከፍተኛው የዘገባ አይነት ነው። ጉዳዩ በእስልምና ይበልጥ አሳሳቢ በሆነ ቁጥር -ለምሳሌ እንደ የእስልምና ማዕዘናት አይነቱ - በጉዳዩ የመጡት ሙተዋቲር የሆኑ ሓዲሦችም ይሁኑ የዘገባ ሰንሰሎቶቹም በርከት ያለ ብዛት ይኖራቸዋል። ጉዳዩ እጅግ ቅርንጫፋዊና የሚበረታታ ጉዳይ ብቻ ሲሆን ደግሞ የዘገባ ሰንሰሎቶቹም የሚሰጠው ትኩረትም አነስ ያለ ይሆናል።
ህዝበ ሙስሊሙ ዘንድ በዘገባ ረገድ እጅግ ከፍተኛ ትኩረት የተቸረው የተከበረው ቁርኣን ስርጭት ሲሆን በፅሁፍ በመስፈሩም ይሁን በልቦና በመሓፊዝ (በመሸምደድ) ቃላቶቹን በማበጠርም ይሁን የሆሄያት አወጣጣቸው እንኳ ሳይቀር ብሎም የአቀራር ስልቱም ጭምር ታላቅ ትኩረት ተችሮት ነው የተሰራጨው። ሽዎች ከሽዎች ለተከታታይ ትውልድ የተቀባበሉት ነው። ስለዚህም ነው ላለፉት ክፍለ ዘመናት ምንም አይነት የብረዛም ይሁን የስረዝ ድለዛ እጆች ያላረፉበት። በስተምዕራብ የሚቀራው ቁርአን ራሱ በስተምስራቅ የሚቀራውና በየትኛውም የምድሪቱ ክፍል የሚቀራው ቁርአን ራሱ ነው። ይህም በቁርአን ውስጥ የሚገኘው ቀጣዩን የኃያሉ አላህ ቃል እውነተኝነት የሚያረጋግጥ ተጨባጭ ነው፦ {እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው። እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን።} [አል-ሒጅር: 9]

## ረ- በመቀጠል፦

ይህ ነው እንግዲህ "ላ ኢላሃ ኢለሏህ" በሚል ይፋዊ መርህ ብቸኛው አምላክ ብቻ እንዲመለክ የሚጣራ። ይኸው ነው እስልምና አላህ ለባሮቹ እንደ ሀይማኖት የመረጠላቸው።
{ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ። ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ። ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ።} [አል ማኢዳህ 3] ይህ ነው እስልምና ሃይማኖት! አላህ ከእርሱ በቀር ሌላን ሃይማኖት ከማንም የማይቀበልበት ብቸኛ። {ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም። እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው።} [አሊ-ዒምራን 85] ይህ ነው እስልምና በርሱ አምኖ መልካም የሰራን ሰው በጸጋዎች ሀገር ጀነት ስኬትን የሚያጎናፅፈው። {እነዚያ ያመኑና መልካም ሥራዎችን የሠሩ የፊርደውስ ገነቶች ለእነሱ መስፈሪያ ናቸው።} {በእርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ከእርሷ መዛወርን የማይፈልጉ ሲኾኑ፤ (መስፈሪያቸው ነው)።} [አልከህፍ፡ 107_108] ይህ ነው እስልምና በከፊል የሰዎች ስብስብ ላይ ብቻ ያልተቆራኘው፤ በየትኛውም የሰው ዘርም ያልተገደበው። ይልቁንም በእርሱ አምኖ ሰዎችንም ወደርሱ የተጣራ (ዳዕዋ ያደረገ) ሰው ሁሉ ለእርሱ ከማንም በፊት ቀዳሚ እና የላቀው አላህ ዘንድም እጅጉን የሚከበሩበት ነው። {አላህ ዘንድ የተወደደው ሀይማኖት እስልምና ነው።} [አል-ሑጁራት: 13]
ሰዎችን በእነርሱ እና ወደ እስልምና ሃይማኖት በመግባታቸው መካከል ግርዶሽ የሚሆኑ ጉዳዮችን ውድ አንባቢን መጠቆም አለብን። አንደኛ፦ የእስልምናን ሀይማኖት እምነቱን፣ ድንጋጌውን እና ስነ-ምግባሩን አለማወቃቸው - ሰዎችም ለማያውቁት ነገር ጠላቶች ናቸውና - ነው። ስለዚህም የእስልምናን ሃይማኖት ለማወቅ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ሁሉ ይህንን ሃይማኖት ከመሰረታዊ ምንጮቹ ማወቅ እስኪችሉ ድረስ ማንበብ፣ ከዚያም ማንበብ፣ ከዚያም ማንበብ፣ ከዚያም ማንበብ አለባቸው። ንባቡም ታዲያ ሚዛናዊ በሆነ ገለልተኛ መንፈስና እውነታን ብቻ በመፈለግ ይሁን።
ሁለተኛ፦ ግለሰቡ ያደገበትን ሃይማኖት ትክክለኛነት በጥልቀትና በጥንቃቄ ሳያመዛዝን ላደገበት ሃይማኖት፣ ባህልና ልማድ ወገንተኛ መሆን። ጎጠኝነትም በውስጡ ይቀሰቀስና ከአባቶቹና ከአያቶቹ ውጭ ያለ ጎዳናን ሁሉ ውድቅ ያደርጋል። ወገንተኝነት አይንንም ያውራል፤ መስሚያንም ይደፍናል፤ አእምሮንም ከማሰላሰል ያቅባል። በመሆኑም ሰውየው ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ማመዛዘንም አይችልም፤ ከዚያም ጨለማና ብርሃኑን እንኳ መለየት ይሳነዋል።
ሦስተኛ፡ የነፍስ ዝንባሌ፣ ፍላጎትና ስሜት ከእውነት ከሚያቅቡ ነገሮች መካከል ናቸው። ማመዛዘንንና ማሰብን ወዳሻቸው ይነዱትና ሰው በማያወቀው በኩል ያወድሙታል፤ እውነትንም ከመቀበልና ለእውነት ተከታይ ከመሆን በኃይል ይገቱታል።
አራተኛ፦ በአንዳንድ ሙስሊሞች ላይ የሚገኙ ስህተቶችና መንሻፈፎች እስልምናን እንደማይወክሉ እየታወቀ በቅጥፈትና በግፍ ወደ ሃይማኖቱ ማስጠጋት። ሁሉም ማስተዋል ያለበት እውነታ ቢኖር ለሰው ልጅ ስህተት እስልምና ተጠያቂ እንደማይሆን ነው።

እውነታንና ቀናውን መመርያ ለማወቅ ቀላሉ መንገድ አንድ ሰው ልቦናውን በንስሃ፣ ራሱን ዝቅ አድርጎ፣ በመተናነስ ወደ አላህ በመዞር አላህን አላህ የሚወደውንና የሚደሰትበት የሆነውን ቀናውን መንገድ እንዲመራው፣ ቀጥተኛውን ሃይማኖት እንዲገጥመው አላህን መማፀን ነው። በዚህም ባርያው ከዛ በኋላ እድለቢስ የማይሆንበትን ዘለቄታዊ ደስታና ስኬትን የተጎናፀፈ ህይወት ይኖራል። አላህ ተጣሪ በጠራውና በተማፀነው ጊዜ ዱዓውን እንደሚቀበለው ይታወቅ። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {ባሮቼም ከእኔ በጠየቁህ ጊዜ (እንዲህ በላቸው)፦ እኔ ቅርብ ነኝ። የለማኙን ጸሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ። ስለዚህ ለኔ ይታዘዙ፤ በኔም ይመኑ፤ እነሱ ሊመሩ ይከጀላልና።} (አልበቀራህ፡186)

ምስጋና ለአላህ የተገባ ይሁንና ተጠናቀቀ።

የእስልምና ሃይማኖት
መቅድም
ውድ አንባቢ ሆይ፦
1- የተውሒድ ቃል (ላ ኢላሃ ኢለላህ)
ለ- አላህ ለምን ፈጠረን?
2- ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ ናቸው።
ሀ- የመልእክተኛው ትርጉም ምንድን ነው? ሙሐመድስ ማን ናቸው? ከእርሳቸውስ ሌላ መልክተኞች አሉን?
ለ - ከመልክተኞች የመጀመሪያው የሆኑት አባታችን አደም (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)፦
ሐ- ኑሕ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)፦
መ - ነቢዩ ሁድ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)
ረ - ነቢዩ ሷሊሕ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)
ሰ - ነቢዩ ኢብራሂም (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)
ሸ - ነቢዩ ሉጥ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)
ቀ - ነቢዩ ሹዐይብ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)
በ - ነቢዩ ሙሳ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)
ተ - ነቢዩ ዒሳ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)
3. ሙሐመድ ﷺ የአላህ መልእክተኛ (የነቢያትና የመልዕክተኞች መደምደሚያ)
ዘራቸው እና ማህበራዊ ክብራቸው (ደረጃቸው)
ለ. ባሕርያቸው
ሐ- ቁረይሾች እና ዐረቦች
መ- የነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ተልዕኮ
ረ- ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ካጠናከረባቸው ተአምራት መካከል፦
ሰ- የተከበሩት ሶሓቦች (የነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ባልደረቦች)
4- የእስልምና ምሰሶዎች (ማዕዘናት)
የመጀመሪያው ማዕዘን፦ ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ አለመኖሩን እና ሙሐመድም የአላህ መልዕክተኛ ናቸው ብሎ መመስከር።
ሁለተኛው ማዕዘን፡ ሰላትን በአግባቡ መስገድ
ሐ- ሶስተኛው ማእዘን: ዘካ
መ- አራተኛው ማእዘን: የረመዷንን ወር መፆም
ሠ - አምስተኛው ማዕዘን፦ ወደ ተቀደሰው ቤት ሐጅ ማድረግ
5- የእምነት ማዕዘናት
6- የእስልምና አስተምህሮቶች እና ስነ-ምግባር
ሀ - ትእዛዞች
አንደኛ፡ በንግግር እውነትኝነት፦
ሁለተኛ፡ አደራን መወጣት፣ ቃል ኪዳኖችን መሙላት እና በሰዎች መካከል ፍትህን ማስፈን
ሦስተኛ፡ ትሕትና እና አለመኩራራት፦
አራተኛ፡ ልግስና፣ ቸርነት እና በበጎ አድራጎት ጉዳዮች ላይ ገንዘብን ማውጣት፦
አምስተኛ: ትዕግስት እና ችግርን መቋቋም:
ስድስተኛ፡ ሓያእ (አይናፋርነት)፦
ሰባተኛ፡ ለወላጆች በጎ መዋል፦
ስምንተኛ፡ ከሌሎች ጋር መልካም ስነምግባር
ዘጠነኛ፡ ተበዳይን ለመደገፍ፣ ሓቅን ወደ ባለቤቱ ከመመለስ እና ፍትህ ከማስፈን አኳያ በአላህ መንገድ ጂሃድ ማድረግ
አስረኛ፡ ዱዓእ፣ ዚክር እና ቁርኣን መቅራት፦
አስራ አንደኛው፡ የሸሪዓን እውቀት መማር፣ ሰዎችን ማስተማር እና ወደዛውም ስለ መጣራት፦
አስራ ሁለተኛው፡ በአላህና በመልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ፍርድ ስለመርካት፦
ለ - ሐራምና ክልክል ስለሆኑ ነገሮች
አንደኛ፦ ሽርክ፡ (የትኛውንም አይነት የአምልኮ ዓይነት ከአላህ ውጭ ላለ አካል አሳልፎ መስጠት)
ሁለተኛ፡ ድግምት፣ ጥንቆላ እና የሩቅ ምስጢር አዋቂነትን መሞገት፦
ሦስተኛ፡ ግፍ (በደል)፦
አራተኛ፦ በሐቅ ካልሆነ በቀር መገደሏን እርም ያደረጋትን ነፍስ መግደል:
አምስተኛ፡ በሰዎች ገንዘብና ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ
ስድስተኛ፡ ማጭበርበር፣ ክህደት እና ተንኮል፦
ሰባተኛ፡ ሰዎች ላይ ድንበር ማለፍ
ስምንተኛ፡ ቁማር መጫወት፣ አስካሪ መጠጥ መጠጣት እና ዕፆችን መውሰድ፦
ዘጠነኛ፡ የበከተ ሥጋ፣ ደም እና የአሳማ ሥጋ መብላት፦
አስረኛ፦ በዝሙትና ግብረሰዶማዊነት መጨማለቅ፦
አስራ አንደኛው፡ አራጣ መብላት

አስራ ሁለተኛው፡ መስገብገብ እና ስስታምነት

አስራ ሦስተኛው፡ ውሸት እና የሀሰት ምስክርነት፦

አሥራ አራተኛ፡ ኩራት፣ ትምክህተኝነት፣ በራስ መደነቅ እና ትዕቢት

ሐ- ከሓራም ነገሮች ተውባ ማድረግ

መ - ሙስሊሞች ይህንን ሃይማኖት በትትክል እንዲሰራጭ የሰጡት ትኩረት፦

ሌላው በሓዲሥ ጥናት የማይዘነጋው ነገር

ረ- በመቀጠል፦